## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

**የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር አንብቦ የመረዳትን ችሎታ በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና፤ በአዲስ ዘመን ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት**

**በ**

**ሙሉገበያ ያለው**

ነሀሴ 2009 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ የስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

**የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር አንብቦ የመረዳትን ችሎታ በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና፤ በአዲስ ዘመን ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት**

በ

ሙሉገበያ ያለው

2009 ዓ.ም.

**የፈተና ቦርድ አባላት**

| | | |
|---|---|---|
| **አማካሪ ስም** | **ቀን** | **ፊርማ** |
| ……………………. | ………………… | ………………… |
| **ፈታኝ ስም** | **ቀን** | **ፊርማ** |
| ……………………… | ………………… | ……………… |
| **ፈታኝ ስም** | **ቀን** | **ፊርማ** |

.......................... ....................... .................

# የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር ኦ ረዳትን ችሎታ በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና፤ በአዲስ ዘመን ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፤ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

ድኅረምረቃ መርሀግብር


ለተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

ሙሉገበያ ያለው


ነሀሴ 2009 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# ምስጋና

በቅድሚያ ጥናቱ ከጅማሬው እስከ ፍጻሜው ለስኬት እንዲበቃ ጠቃሚ አስተያየቶችን በመስጠት፣ ስህተቴን በማረም፣ ለስራየ ፈጣን ምላሽ በመስጠት ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ሳይሰስቱ ጥናቱ ትክክለኛውን አቅጣጫ እንዲይዝ ላደረጉልኝ ለአማካሪዬ ዶክተር ጌታቸው እንዳላማው ምስጋናዬ የላቀ ነው።

በመቀጠል ለስራየ መሳካት የጉልበት፣ የሀሳብ፣ የገንዘብ ድጋፍ ላደረጉልኝ ከጎኔ ላልተለዩት እናቴ፣ ባለቤቴ፣ እህቶቼ፣ ወንድሞቼ፣ ልጆቼ እና ጓደኞቼ ምስጋናዬ ወደር የለውም።

የጥናት ወጭዬን በመሸፈን ትብብር ያደረገልኝን የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲን አመሰግናለሁ።

በመጨረሻም ፈተናዎችን በማረም፣ አስተያየቶችን በመስጠት ሙያዊ እገዛቸው ላልተለየኝ ለአዲስ ዘመን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርትቤት የአማርኛ ቀንቋ መምህራንና ለጥናቱ መረጃ በመስጠት የተባበሩኝን የአዲስ ዘመን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን ከልብ አመሰግናለሁ።

# የይዘት ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


**ምስጋና** ........... ..........................................................................................i
**የይዘት ማውጫ**......................................................................................ii
**የሰንጠረዥ ማውጫ** ........ ...........................................................................v
**አጠቃሎ** .......... ..............................................................................vi
**ምእራፍ አንድ**
**መግቢያ** ............ ..........................................................................................1
1.1 **የጥናቱ ዳራ** ...................................................................1
1.2 **የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት**..........................................................3
1.3 **የጥናቱ ዓላማ** ...................................................................5
1.4 **የጥናቱ አስፈላጊነት**...............................................................5
1.5 **የጥናቱ ወሰን** ...................................................................5
**ምዕራፍ ሁለት**
**የተዛማጅ ጽሁፎች ክለሳ** .......... ...............................................................6
2.1 **የጽሁፍ አወቃቀር**.................................................................6
2.2 **የጽሁፍ አወቃቀርና አንብቦ የመረዳት ክሂል ትስስር**..................................8
2.3 **የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት አስፈላጊነትና አተገባበር ስልት**........................10
2.3.1 **የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት አስፈላጊነት**........................................10
2.3.2 **የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት አተገባበር ስልት**....................................13
2.4 **አንብቦ መረዳት** ..................................................................14
2.4.1 **የአንብቦ መረዳት ስልቶች** ......................................................16
2.4.2 **የጥሩ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ባህሪያት** .....................................18
2.4.3 **የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃ አሰጣጥ**..........................................19
2.4.4 **የአንብቦ መረዳት የትምህርት አሰጣጥ ሂደት**...................................21
2.5 **የቀደምት ስራዎች ቅኝት** ........................................................20
**ምእራፍ ሶስት**

የአጠናን ንድፍና ዘዴ........................................................................24
3.1 የጥናቱ ንድፍ .................................................................24
3.2 የመረጃ ምንጮች.............................................................26
3.3 የናሙና አመራረጥ.............................................................25
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ..................................................26
3.4.1 ፈተና .................................................................................26
3.4.2 የጽሁፍ መጠይቅ ......................................................................27
3.5 የመረጃ አተንተን ዘዴ ...........................................................28
ምእራፍ አራት
የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ....... ..........................................28
4.1 የመረጃ ትንተና .................................................................28
4.1.1 ከቅድመ ትምህርት ፈተና የተገኙ መረጃዎች ትንተና.......................................28
4.1.2 ከድህረ ትምህርት ፈተና የተገኙ መረጃዎች ትንተና.......................................28
4.1.3 የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት ፈተና ልዩነት በዳግም ልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት...........................................................31
4.1.4 የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የተገኘ ውጤት ድግግሞሽ ..................31
4.1.5 ከቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና .......34
4.1.5.1 ከቅደመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና .......................34
4.1.5.2 ከድህረ ትምህርት በጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና .......................35
4.1.5.3 የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ በዳግምልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት.........................................................................39
4.2 የውጤት ማብራሪያ ..............................................................38
ምእራፍ አምስት
ማጠቃለያና አስተያየት................................................................41
5.1 ማጠቃለያ.......................................................................41
5.2 አስተያየት .....................................................................42
ዋቢ ጽሁፎች........... ..........................................................44
አባሪ ሀ........... ..................................................................49
አባሪ ለ ........... ...............................................................56

አባሪ ሐ.......................................................................................................61
አባሪ መ .....................................................................................................74
አባሪ ሠ.....................................................................................................76
አባሪ ረ .....................................................................................80
አባሪ ሰ.......................................................................................82

## የሰንጠረዥ ማውጫ

**ሠንጠረዥ** **ገጽ**

ሰንጠረዥ፡-1 የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃዎች ------------------------------- 21

ሰንጠረዥ፡-2 የቅድመ ትምህርት ፈተና ተገኙ ከፍተኛ፣ ዝቅተኛ፣ አማካይ

ውጤትና መደበኛ ልይይት ---------------------------------------- --30

ሰንጠረዥ፡-.3 የድህረ ትምህርት ፈተናን የተገኙ ከፍተኛ፣ ዝቅተኛ፣ አማካይ ውጤትና

መደበኛ ልይይት -------------------------------------------------- 31

ሰንጠረዥ፡-4 የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና አንብቦ የመረዳት ችሎታ

በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ------------------------------------- 32

ሰንጠረዥ፡- 5 ከቅድመ ትምህርት ፈተና የተገኘ የውጤት ድግግሞሽ------------------33

ሰንጠረዥ፡- 6 ከድህረ ትምህርት ፈተና የተገኘ የውጤት ድግግሞሽ---------------------34

ሰንጠረዥ፡-7 የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የተገኘ ውጤት ድግግሞሽ ---- 34

ሰንጠረዥ፡-8 ከቅደመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና -------- 36

ሰንጠረዥ፡-9 ከድህረ ትምህርት በጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና --------- 37

ሰንጠረዥ ፡-10 የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ በዳግም ልኬታ ናሙና

ቲ-ቴስት---------------------------------------------------------- 39

# አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት ዋና አላማ የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር የአንብቦ መረዳትን ችሎታ ለማጎልበት ያለውን ሚና መመርመር ነበር። የጥናቱን ተሳታፊዎች ለመምረጥም እድል ሰጭ ናሙና ዘዴን ተጠቅሟል። ተሳታፊዎቹም በአዲስ ዘመን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት በ2009 ዓ.ም በዘጠነኛ ክፍል ከሚማሩ ተማሪዎች መካከል በተመረጠው የናሙና ዘዴ የተመረጡ 52 ተማሪዎች ናቸው። ጥናቱ ሙከራዊ የምርምር ስልትን የተከተለና አንድ ተጠኚ ቡድን ብቻ የያዘ የአንድ ቡድን ቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተና ንድፍን ተግባራዊ ያደረገ ነው። ለተማሪዎች ቅድመ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷ፣ ለአምስት ሳምንታት በአጥኚዋ ከተማሩ በኋላ የድህረ ትምህርት ፈተናው ከቅድመ ትምህርት ፈተናው በተመሳሳይ መልክ ተዘጋጅቶ እንዲፈተኑ ተደርጓል። ከነዚህ ተማሪዎችም በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት ፈተናዎችና ከጽሁፍ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል። መረጃዎቹም መጠናዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በዳግም ልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልተው በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተተንትነዋል። በሁለቱ መረጃ መሰብሰቢያዎች አማካኝነት የተገኙት መረጃዎች በቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (26.27) እና በድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (33.25) መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት ($p<0.05$) ታይቷል። ይህም የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት አንብቦ መረዳትን እንደሚያጎለብት አመላክቷል። የቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (3.36) እና በድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (3.7) መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት ($p<0.05$) መኖሩን አሳይቷል። ጥናቱ የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት የተማሪዎችን የጽሁፍ አወቃቀር ግንዛቤ እንዳሻሻለ አሳይቷል። በጥናቱ ውጤት መሰረትም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጎልበትና ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ያላቸውን ግንዛቤ ለማሻሻል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ የማጎልበት ሚና እንዳለውና የጽሁፍ አወቃቀር አይነቶችን ለመለየት ጠቃሚ መሆኑን ተገንዝበው ጽሁፉ ለተደራጀበት የጽሁፍ አወቃቀር ትኩረት ቢሰጡ፣ የመጽሀፍ አዘጋጆች በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚካተቱ ምንባቦች የጽሁፍ አወቃቀር አይነቶችን መሰረት ያደረጉ፣ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችም የጽሁፍ አወቃቀሩን መሰረት ያደረጉ እንዲሆኑ በማዲረግ ቢያዘጋጁ፣ ይህ ጥናት ከጽሁፍ አወቃቀር አይነቶች ውስጥ በምክንያትና ውጤት እና በገለጻ ላይ ያተኮረ ነው። ከክሂሎች ደግሞ አንብቦ መረዳትን የተመለከተ በመሆኑ በቀጣይ ሌሎች አጥኚዎች ሁሉንም ጽሁፍ አወቃቀር አይነቶችና ክሂሎች ያካተተ ጥናት ቢካሄድ የተሻለ ግንዛቤ ሊገኝ ይችላል። የሚሉ የመፍትሂ ሀሳቦች ተጠ+ቁመዋል።*

# ምእራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

የጽሁፍ መዋቅር በጽሁፍ ውስጥ በሚገኙ ሃሳቦች መካከል ያለውን ተጠየቃዊ ትስስር ያሳያል። እያንዳንዱ ሀሳብ ቀጥሎ ለሚቀርበው ሀሳብ ያለውን ጠቀሜታ ያሳያል። ሌሎች ንዑሳን ሃሳቦችን መለየት ያስችላል። የጽሁፉ ሃሳቦች ፍሰት፣ የእያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር ቅደም ተከተል በዋናው ሃሳብ ባለው ቅርበት ላይ ይወሰናል። እያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር በጽሁፉ ውስጥ የሚኖረው ዋጋ የሚወሰነው በሌላው ዓረፍተ ነገር መልዕክት ላይ ነው። ይህ ውስብስብ ተጠየቃዊ ትስስር የሚደራጅበት መንገድ ሪህቶሪካላዊ (የሀሳብ ፍሰት) አወቃቀር ይባላል ( Nuttal 1982)።

Sharp (2002) ሪህቶሪካዊ (የሀሳብ ፍሰት) አወቃቀር የጽሁፍ ሰፊ መዋቅር (macrostructure) ሲሆን ደራሲው አስፈላጊውን መልእክት ለማስተላለፍ የተጠቀመበት ጽሁፍ ተጠየቃዊ አወቃቀር በማካተት ያቀርባል በማለት ያስረዳሉ።

ሪህቶሪካዊ (የሀሳብ ፍሰት) አወቃቀር ንድፈ ሀሳብ (rhetorical structure theory) የተመሰረተው በ1980ዎቹ ሲሆን በስፋት እየታወቀ የመጣው በ Mann and Thompson በ1980ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ሪህቶሪካዊ (የሀሳብ ፍሰት) አወቃቀርን በተመለከተ ጥናት ካካሄዱ በኋላ ነው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በተለይ ስነልሳናዊ እሳቤ (Computational Linguistics) ከፍተኛ ተከታይ አግኝቶል። ንድፈ ሀሳቡ የሚያተኩረው የጽሁፍ አወቃቀርን በመለየት ላይ ነው። ትኩረቱም የጽሁፍ ትንተና መሰረት ያደረገ ነው። ንድፈ ሀሳቡ የተመሰረተውም ጽሁፎችን ቅርጸ መዋቅር እንዲይዙ ለማስቻል ሲሆን የቋንቋ አጠቃቀም መዋቅርን በተለይም የተጻፉ ጽሁፎችን ዲስኩራዊ አወቃቀር ይለያል። ዲስኩራዊ ትንተናን ከመስጠትና ጽሁፍን ከማፍለቅ ባለፈ መልኩ ጽሁፍን ማደራጀትና አገልግሎት ላይ ማዋል በዋናነት ይዞ የተነሳና ጽሁፍን አቅዶ ለማዋቀር የሚረዳ ነው ( Mann and Thompson 1987)።

Dymock (2005) እንደሚይስረዱት የጽሁፍ አወቃቀር አንባቢው የጽሁፉን መልእክት እንዲረዳ በየሀሳቦች መካከል ፍንጭ የሚሰጡ ቃላትን የሚያካትት ነው። የጽሁፍ አወቃቀር ማለት ጸሀፊው መረጃውን በጽሁፍ ውስጥ እንዴት እንዳደራጀው የሚያሳይ ነው።

Frey and Lapp (2008) አንባቢው አንድን ጽሁፍ አንብቦ ለመረዳት በጽሁፍ ውስጥ የሚገኙ መረጃዎችን ለማደራጀት ከሚያስችለው መንገድ አንዱ ጸሀፊው ለተጠቀመበት የጽሁፍ  አወቃቀር ትኩረት መስጠት መቻል ነው።

Heydary and Mustapha (2009) እንደሚገልጽት በደራሲ/ ጸሀፊ የሚቀርቡ ጽሁፎች በሁለት የተለያዩ ዝርው ጽሁፎች ይከፈላሉ። እነሱም ተራኪ ዝርውና አስረጅ ዝርው ናቸው። ተራኪ (Narative) ጽሁፍ ልቦለድንና ሌሎች ታሪክ ቀመስ ጽሁፎችን የሚያካትት ሲሆን አስረጅ (Expository) ጽሁፍ ደግሞ ኢ-ልቦለድንና ሌሎች ትምህርታዊ ይዘቶችን ያካትታል። ሁለቱም ጽሁፎች የሚደራጁበት የጽሁፍ አወቃቀር መንገድ አላቸው። ለምሳሌ ተራኪ ጽሁፎች ገጸ ባህሪያትን፣ ክስተቶችን፣ ጭብጥንና ማጠቃለያዎችን የሚያመላክቱ ሞዴሎችን ያካትታል። አስረጅ ጽሁፍ ደግሞ የክስተቶችን፣ ምክንያትና ውጤት፣ ውድድርንና ንጽጽርን፣ የፍጻሜዎችን ተከታታይነት እንዲሁም የሚከሰቱ ችግሮችንና መፍትሄዎችን የሚያመላክቱ መዋቅሮችን ያካትታሉ።

የጽሁፍ መዋቅርን ማስተማርን አስመልክተው Armbuster, Andessen and Ostertage (1987) Engilert and Hibert (1984) እና Meyer (1975) ን ጠቅሰው እንደሚከተለው ይገልጹታል። የጽሁፍ አወቃቀር አይነቶች የሚባሉት አምስት ናቸው።እነርሱም ማወዳደርና ማነፃፀር፣ ገለጻ፣ ችግር- መፍትሄ፣ ምክንያትና ውጤት እንዲሁም ቅደም ተከተል ናቸው።

Dymock (2005) እንደሚያስረዱት በምክንያትና ውጤት የሚቀርብ የጽሁፍ አደረጃጀት በምክንያትና አንድና ከዚያ በላይ በሆኑ ውጤቶች መካከል የሚኖርን ተጠየቃዊ ዝምድና ይተነትናል። አንድ ነገር በአንድ ቦታ ላይ የመገኘቱን ምክንያትና ውጤቱን ለመግለጽ ስለሆነም፣ ከዚህ የተነሳ፣ ምክንያቱም፣ ስለዚህና የመሳሰሉትን አያያዥ ቃላት ይጠቀማል።

ሌላው የጽሁፍ አወቃቀር ማነጻጸርና ማወዳደር ነው። በማነጻጸርና በማወዳደር የሚቀርብ የጽሁፍ አወቃቀር በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ጉዳዬች መካከል የሚኖርን ተመሳሳይነትና ተቃርኖ ያቀርባል። የተሻለው፣ በተመሳሳይ፣ ሲነጻጸር፣ ከዚህ ይልቅ፣ በሌላ በኩል፣

በተቃራኒው እና የመሳሰሉትን ቃላትንና ሀረጋትን በመጠቀም እያነጻጸረና እያወዳደረ ያቀርባል።

ቀጣዩ የጽሁፍ አወቃቀር ገለጻ ሲሆን በአንድ ርእሰ ጉዳይ ላይ ጥልቅ የሆነ ገለጻ የሚያደርግ፣ ገላጭ ቃላትን በመጠቀም በአንባቢው አእምሮ ውስጥ ምእናባዊ ምስል እንዲፈጠር የሚያደርግ የጽሁፍ አወቃቀር ነው።

ችግር መፍትሄ የጽሁፍ አወቃቀር ችግሩን ነቅሶ በማውጣት ችግሩ እንዴት ሊፈታ እንደሚችል ሀሳብ የሚቀርብበት ነው። ችግሩን ዘርዝሮ የመፍትሄ ሀሳቦችን የሚያስቀምጥ ነው። ሀሳቡን ግልጽ ለማድረግ ስለሆነም፣ ይህን ለማድረግ፣ ምክንያቱም እና የመሳሰሉትን ቃላት ይጠቀማል።

ሌላው የጽሁፍ አወቃቀር ቅደም ተከተል ሲሆን የድርጊቶችንና የክስተቶችን ቅደም ተከተል በተፈጸመበት የጊዜና የሂደት ቅደም ተከተል በማደራጀት የሚያቀርብ ነው። ሀሳቡን ግልጽ ለማድረግ ቀጥሎም፣ ከዚህ በፊት፣ እስከ፣ ከዚህ በኋላ፣ በመጨረሻ፣ በመጀመሪያ እና የመሳሰሉትን አያያዦችን ይጠቀማል።

የጽሁፍ አወቃቀር (ማወዳደርና ማነፃፀር፣ ገለጻ፣ ችግር- መፍትሄ፣ ምክንያትና ውጤት እንዲሁም ቅደም ተከተል) በመጠቀም ማስተማር መረጃን ለመለየት፣ የመረዳት አቅምን ለመጨመር፣ ሀሳብን ለማደራጀት፣ የጽሁፉን ሀሳብ ለማስታወስና የጽሁፍ አወቃቀሩን ለመገንዘብ ይረዳል። በአጠቃላይ ስለ ጽሁፍ አወቃቀር መገንዘብ አንብቦ መረዳትን እንደሚያጎለብት ጥናቶቹ ጠቁመዋል ። ይህ ጥናትም የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር አንብቦ መረዳትን ለማጎልበት ያለውን ሚና በመመርመር ላይ ትኩረት ያደርጋል።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

Dymock (2005) እንደገለፁት ዘወትር እንደሚታየው ተማሪዎች ከንባብ ጋር ሳይተዋወቁ፣ ጥሩ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ሳይኖራቸው፣ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቅቃሉ። በመሆኑም በርካታ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ደካማ ነው። የዳበረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ስለሌላቸው የሚያነቡትን ምንባብ በሰፊው እንዳይመለከቱ ከማድረግ ባለፈ በትምህርት ውጤታቸው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

Meyer, Brandt and Bluth (1980)፣ Armbuster, Andessen and Ostertage (1987) Piyonukool (2001) ባካሄዱት ጥናት የጽሁፍ አወቃቀር አንብቦ መረዳትን በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ገልጸዋል። ይሁን እንጅ ይህ ርዕሰ ጉዳይ ተጠንቶ ያልተቋጨ በመሆኑ አጥኚዎቹ በማጠቃለያቸው ተጨማሪ ጥናት እንደ ሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

የዚህ ጥናት አቅራቢም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል አስተምራለች። በዚህም ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች አንደኛው የማንበብ ክሂልን የሚመለከት መሆኑን ተገንዝባለች። ብዙዎቹ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውም ደካማ ስለመሆኑ በየጊዜው ከሚሰሯቸው የክፍል መልመጃዎችና መደበኛ ፈተናዎች ግምገማ በመነሳት ያለባቸውን ክፍተት አጥኚዋ መገንዘብ ችላለች። ከዚህም በመነሳት በተማሪዎች ላይ የተስተዋለው ችግር በትምህርት ማስተማሪያነት የሚዘጋጁ ምንባቦች የጽሁፍ አወቃቀራቸውን ማስተማር በአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ላይ ለውጥ ያመጣ ይሆን? የሚለውን ለማየት አጥኚዋ በዚህ ርእስ ላይ በዋናነት ትኩረት አድርጋለች።

በተጨማሪም አጥኚዋ በምታስተምርበት ትምህርት ቤት አንብቦ መረዳትን ለማስተማር በሚደረገው የመማር ማስተማር ሂደት መምህራን የአንብቦ መረዳት ትምህርትን የሚያከናውኑት ተማሪዎች የቀረበውን ምንባብ አንብበው ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ በማድረግ ነው። ይሁን እንጅ መምህራን በቅድሚያ ጽሁፉ ለቀረበበት የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት ትኩረት ሲሰጡ አይታዩም። ይህም ተማሪዎች በቅድሚያ ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት ቢሰጣቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ይጎለብት ይሆን? የሚል ጥያቄ ፈጥሯል።

የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር አንብቦ መረዳትን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ለመመርመር በተካሄዱ ጥናቶች ማጠቃለያ ላይ ተጨማሪ ጥናት እንደሚያስፈልግ በመጠቆማቸውና አጥኚዋ እስካሁን ባየቻቸው ይህን ርእሰ ጉዳይ በተመለከተ በሀገር ውስጥ ጥናት አለመደረጉ አጥኚዋ በዚህ ርእስ እንድትሰራ ያነሳሳት ሌላው ምክንያት ነው።

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረትም ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማጎልበት ያለውን ሚና መመርመር ነው። በዚህም መሠረት ጥናቱ የሚከተሉትን መላምቶች አስቀምጧል።

1. የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ለውጥ ያመጣል።
2. የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት የተማሪዎችን የጽሁፍ አወቃቀር ችሎታ ያሻሽላል።

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር የአንብቦ መረዳትን ችሎታ ለማጎልበት ያለውን ሚና መመርመር ነው። በዚህም መሠረት ይህ ጥናት የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል።

1. የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ለውጥ ያመጣ እንደሆነ መመርመር፤
2. የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት የተማሪዎችን የጽሁፍ አወቃቀር ችሎታ ማሻሻሉን
3. መፈተሽ።

## 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

የጽሁፍን አወቃቀር የመለየትና የመተንተን ችሎታ ለአንባቢዎች ጽሁፉን በቀላሉ የመረዳትና ሀሳቡን ለረጅም ጊዜ ማስታዎስ አቅም ይሰጣል። በንባብ ጥሩ ውጤት ላይ ለመድረስ የጽሁፉ መዋቅር በምን አይነት እንደተዋቀረ ማወቅ ጠቀሜታ አለው Dymock (2005)።

ይህ ጥናት ቀጥሎ ያሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታሰባል፤

1. መምህራን በጥናቱ ውጤት መሰረት የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማጎልበት የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር የሚሰጠውን ጠቀሜታ ተገንዝበው ትኩረት ሰጥተው እንዲያስተምሩ ያግዛል፤
2. መጽሀፍ ለሚያዘጋጁ ባለሙያዎች በመማሪያና በማስተማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ለጽሁፍ አወቃቀር ትኩረት በመስጠት እንዲያዘጋጁ ለማድረግ ይረዳል፤
3. ለወደፊት ተመራማሪዎች እንደ መነሻ ሰነድ ሁኖ ሊያገለግል ይችላል።

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የተከናወነው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በደቡብ ጎንደር ዞን በሊቦ ከምከም ወርዳ ከሚገኙ አራት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በአዲስ ዘመን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ብቻ ነው።

ጥናቱ ትኩረት ያደርገው በ2009 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመማር ላይ ባሉ የዘጠነኛ ''D'' ክፍል ተማሪዎች ነው። የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ለብሄራዊ ፈተና ዝግጅት ላይ ስለሆኑ ትክክለኛ መረጃ መስጠት አይችሉም በሚል ስጋት በዚህ ጥናት አልተካተቱም። ጥናቱ ትኩረት ያደረገው አንብቦ መረዳት ላይ ብቻ ስለሆነ ሌሎች ክሂሎችን አይመለከትም።በተጨማሪም ከጽሁፍ አወቃቀሮች ውስጥ በገለጻና በምክንያትና ውጤት ላይ ብቻ ትኩረት ያደረገ ነው።

# ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ጽሁፎች ክለሳ

### 2.1 የጽሁፍ አወቃቀር

Meyer, Brandt and Bluth (1980) የጽሁፍ አወቃቀር በጽሁፉ ውስጥ በሚገኙ ሀሳቦች መካከል ያለውን ተጠየቃዊ ትስስርና አንዳንድ ሀሳቦች ቀጥሎ ለሚቀርበው ሀሳብ ያላቸውን ጠቀሜታ ያሳያል።

እንደ Hess (2006) ማብራሪያ የጽሁፍ አወቃቀር አንድ ጸሀፊ መረጃን በጽሁፉ ውስጥ የሚያቀናጅበት መንገድ ነው። የጽሁፍ አወቃቀር አንባቢ የጽሁፉን መልእክት እንዲረዳ በየሀሳቦች መካከል ፍንጭ የሚሰጡ ቃላትን ያካትታል። የጽሁፍ አወቃቀር ከጽሁፉ አይነትና አላማ አንጻር በአንድ አንቀጽ ወይም ከአንቀጽ በበለጠ መዋቅር የሚደራጅ የመዋቅር ቅንጅት ነው።

Meyer and Ray (2011) የጽሁፍ አወቃቀርን እንደሚከተለው ይገልጹታል። የጽሁፍ አወቃቀር በጽሁፍ ውስጥ የሚገኙ እጅግ ጠቃሚ ሀሳቦች እርስ በርሳቸው ያላቸውን ትስስር አጉልቶ ከማሳየቱም በተጨማሪ የአንባቢውን የጽሁፉን ትርጉም የመስጠት አቅም ያሳድጋል። የጽሁፍ አወቃቀር እውቀት ያላቸው አንባቢዎች ቅደም ተከተል፣ ማወዳደርና ማነፃፀር፣ ምክንያትና ውጤት እንዲሁም ችግርና መፍትሄን የሚያሳዩ ፍንጮችን በመጠቀም በጽሁፍ ውስጥ ያሉ ሃሳቦች እንዴት እርስ በርስ የተያያዙ እንዲሆኑ መገመት ይችላሉ።

Padua (2008)፣ Meyer, Brandt and Bluth (1980) እንደገለፁት፣ የጽሁፍ አወቃቀር ፀሀፊው በጽሁፍ ውስጥ መረጃን ለማቅረብ የሚጠቀምበት የሀሳብ ማደራጃ መንገድ ነው። አደረጃጀቱም በገለፃ፣ በማወዳደርና በማነፃፀር፣ ችግር-መፍትሔ፣ ቅደምተከተል፣ በምክንያትና ውጤት ሊሆን ይችላል። አብዛኛዎቹም ትምህርታዊ ይዘት ያላቸው ጽሁፎች የሚቀርቡት በገለፃ፣ በማወዳደርና በማነፃፀር፣ ችግር-መፍትሔ፣ በምክንያትና ውጤት የጽሁፍ አወቃቀር ነው። በመጀመሪያና በከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ተማሪዎች ትምህርታዊ ይዘት ያላቸውን ጽሁፎች ያነባሉ። ተማሪዎች እነዚህን የአደረጃጀት መንገዶች ማወቃቸው የጽሁፉን መልዕክት እንዲለዩ ይረዳቸዋል። በትምህርታቸውም ላይ ለውጥ በማምጣት ውጤታማ እንዲሆኑ ያግዛቸዋል።

Haydari and Mustapha (2009) እንደሚያስረዱት በደራሲ የሚቀርቡ ጽሁፎች በሁለት የተለያዩ ዝርው ጽሁፎች ይከፈላሉ። እነሱም ተራኪና አስረጅ ናቸው። ተራኪ ጽሁፍ ልቦለድንና ሌሎች ታሪክ ቀመስ ጽሁፎችን የሚያካትት ሲሆን አስረጅ ጽሁፍ ደግሞ ኢ-ልቦለድንና ሌሎች ትምህርታዊ ይዘቶችን ያካትታል። ሁለቱም ጽሁፎች የሚደራጁበት የጽሁፍ አወቃቀር መንገድ አላቸው።

በምክንያትና ውጤት የጽሁፍ አወቃቀር የሚቀርብ ጽሁፍ በምክንያትና ውጤቶች መካከል የሚኖርን ተጠየቃዊ ዝምድና ይተነትናል። ይህ የጽሁፍ አደረጃጀት አስቀድሞ ምክንያቱን

በመግለጽ የተደረሰበትን ውጤት ያቀርባል። ወይም የተደረሰበትን ውጤት አስቀድሞ በማቅረብ ለዚያ ውጤት መነሻ የሆኑ ምክንያቶችን ይዘረዝራል። ይህንን የምክንያትና ውጤት ትስስር ለመግለጽ ስለሆነም፣ ከዚህ የተነሳ፣ ምክንያቱም፣ ስለዚህና የመሳሰሉትን አያያዥ ቃላት ይጠቀማል።

ገለጻ የጽሁፍ አወቃቀር አንድ ርእሰ ጉዳይ በማቅረብ ስለ ርእሰ ጉዳዩ መገኛ ቦታ መለያ ባህሪ በማቅረብ በጥልቀት በመተንተን በአንባቢው አእምሮ ውስጥ ምእናባዊ ምስል እንዲፈጠር የሚያደርግ የጽሁፍ አወቃቀር ነው።

በደራሲ የሚቀርቡ ጽሁፎች ተራኪና አስረጅ በሆነ መንገድ ይቀርባሉ። እነዚህ ጽሁፎች ተደራጅተው የሚቀርቡት በተለያዩ የጽሁፍ አወቃቀሮች ነው። የጽሁፍ አወቃቀር ጸሀፊው መረጃን በጽሁፍ ውስጥ የሚያደራጅበት መንገድ ነው። ፍንጭ ሰጭ ቃላትን በመጠቀም የሀሳቡን ትስስር በማሳየት ጽሁፉ ተደራጅቶ የሚቀርብበት ነው።

## 2.2 የጽሁፍ አወቃቀርና አንብቦ የመረዳት ክሂል ትስስር

ከአራቱ ክሂሎች መካከል አንዱና አስፈላጊው ክሂል የማንበብ ክሂል ነው። የማንበብ ክሂል አስፈላጊነትና ጠቃሚነት በመምህራን፣ በተማሪዎች፣ በወላጆችና በቀጣሪ መስሪያ ቤቶች የታመነ ቢሆንም ተማሪዎች አንብቦ መረዳትን በተመለከተ ዘርፈ ብዙ ችግሮች እንዳሉባቸው ያመለከቱ ጥናቶች አሉ (Armbuster, Andessen and Ostertage 1987)። በጥናቶቹ ውጤት መሰረት ብዙዎቹ ተማሪዎች በሚያነቧቸው ፅሁፎች ውስጥ አስፈላጊና አላስፈላጊ በሆኑ ሀሳቦች መካከል ያለውን ልዩነት አይረዱም፤ አንብበው ማጠቃለያ መፃፍ አይችሉም።

የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ የተለያዩ ችግሮች ይታዩባቸዋል። በአንብቦ መረዳት ጊዜ የሚታዩት ችግሮችም በርካታ ቢሆኑም ጠቅለል ባለ መልኩ በችግርነት የሚጠቀሱት ውስን የቃላት እውቀት፣ በትክክል አለማንበብ፣ ከሚነበበው ፅሁፍ ጋር ቅርበት አለመኖር፣ የፅሁፉ ተገቢነት ወይም የክብደት ደረጃ፣ መረጃን በማግኘት ሂደት ላይ ችግር መኖር፣ ካነበቡ በኋላ መረጃ በመመዝገብ ላይ ችግር መኖር፣ በቂ ያልሆኑ ወይም ስኬታማ የማያደርጉ የማንበብ ብልሀቶችን መጠቀም የሚጠቀሱ ናቸው (Lauterbach and Bender 1995)።
Meyer and Ray (2011) የጽሁፍ አወቃቀርን የሚጠቀሙ አንባቢያን የራሳቸውን የጽሁፍ አወቃቀር ግንዛቤ ለማስፋት የጸሀፊውን የጽሁፍ አወቃቀር መለየትና መጠቀም ይችላሉ። ተማሪዎች የጽሁፍን አወቃቀር ካልተረዱ የሚያነቡትን ምንባብ ትርጉም ሊያገኙ አይችሉም።

በአንብቦ መረዳትና በጽሁፍ አወቃቀር መካከል ጥብቅ ቁርኝት እንዳለ በርካታ ጥናቶች ይጠቁማሉ።

Hess (2006) አራትና አምስት አንቀፅ ያለው ጽሁፍ ለአንብቦ መረዳት ትምህርት ማስተማሪያነት ቢቀርብ የመጀመሪያው አንቀፅ ስለችግሩ ይጠቅሳል፤ ሁለተኛው፣ ሶስተኛው፣ አራተኛው የችግሩን መፍቻ መፍትሔ ይጠቁማል። ይህ አይነት አደረጃጀት ለአንባቢው ስለሚነበበው ጽሁፍ ጥቆማ ስለሚሰጥ የሚያነቡትን የማደራጀትና የማቀናጀት ችግር ላለባቸው ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው እንዲሻሻል ያደርጋል።

Gentry (2006)፣ Piyonukool (2001) እንደገለፁት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ንባብ አንዱና በጣም ወሳኝ ክሂል ነው። ሰዎች እንደሚያምኑት የበለጠ የሚያነብ የበለጠ ይማራል፤ ወይም ማንበብ በትምህርትም ይሁን በህይወት ዘመን ስኬታማ ለመሆን ይጠቅማል። የማንበብ ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የጽሁፍን ሀሳብ ለመገንዘብ ይቸገራሉ፤ በዋናነትም ቃላትና ፅንሰ ሀሳቦችን የመረዳት ችግር፣ ጠቃሚ የሆነ አንብቦ የመረዳት ብልሃት ያለመጠቀም፣ በቂ ያልሆነ እውቀትና የሚያነቡትን ሙሉ በሙሉ አለመረዳት ችግር ይታይባቸዋል። ተማሪዎች የቀረበላቸውን መማሪያ መፅሀፍ አንብበው እንዲረዱ በአነበቡት ጽሁፍ ሀሳብ ላይ ተመስርተው ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ይጠበቃል። በጥልቀት የማንበብ ችሎታ የጽሁፉን ሀሳብ እንዲያወጡና በስራቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ አስፈላጊ ነው። የቀደሙትና የቅርብ ጊዜ ጥናቶች እንደጠቆሙት በየትኛውም የችሎታ ደረጃ ያሉ ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚጠቀሙባቸውን በተለያየ የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጁ ጽሁፎችን አንብበው ለመረዳት ይጥራሉ። ይሁንና አንባቢዎች ባላቸው ዝቅተኛ የማንበብ ችሎታ ሁሉንም ነገር ሊማሩ፣ ሊያስታውሱ አይችሉም። በዚህ ምክንያት ከብዙ ሀሳብ የተወሰነ መረጃን ብቻ ይወስዳሉ። ይህንን ችግር ለመፍታት አንዱና ዋጋ ያለው አንብቦ የመረዳት ችሎታን የሚያሻሽለው የመማር ብልሃት ስለጽሁፍ አወቃቀር ለተማሪዎች ግንዛቤ መፍጠር ነው።

Yochum (1991) ፣ Dole and Others (1991) እንደሚያስረዱት አንብቦ መረዳት በአንባቢው የቀደመ እውቀትና በጽሁፍ ውስጥ በቀረበው መልእክት መካከል የሚፈጠር ውህደት ውጤት ነው። ስለዚህም ማንበብ በጽሁፍ ውስጥ የሚገኙ ሀሳቦችንና አንባቢው ያለውን የቀደመ እውቀት የማስተሳሰር ብቃትን የሚጠይቅ ነው። የዳራዊ እውቀትና የጽሁፍ አወቃቀርን በማጣመር ጽሁፉን ለመረዳት የተማሪዎች የንባብ ችሎታ መዳበር ይኖርበታል።

Nuttl (2000) ፣ Grellet (1981)፣ Harmer (1991) ጨምረው እንዳብራሩት፣ ማንበብ ፀሀፊው በፅሁፍ ውስጥ ያሰፈረውን ሀሳብ በተቻለ መጠን ለመረዳት፣ ለመለየት የሚደረግ ጥረት ነው። በመሆኑም አንባቢው በንባብ ሂደት የፅሁፉን መልዕክት ለመገንዘብና ከውስጡ አስፈላጊ መረጃዎችን ለይቶ ለማውጣት ጠቃሚ የንባብ ብልሃቶችን መጠቀም ያስፈልገዋል። ከሚነበበውም ጽሁፍ ፍሬ ሀሳብ ነቅሶ ማውጣት፣ የጽሁፉን ዝርዝር ሃሳብ መረዳት፣ የጽሁፉን መልዕክት መገንዘብ፣ የጽሁፉን አወቃቀርና አደረጃጀት መለየት ይጠበቅበታል።

Meyer, Brandt and Bluth (1980) የጽሁፍ አወቃቀርን መጠቀም የአንብቦ መረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና በሚል ርእስ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ባደረጉት ጥናት የፀሐፊውን የጽሁፍ አወቃቀር መረዳት ለመማርና ለማስታወስ ጠቃሚ እንደሆነና የአንብቦ መረዳት ችሎታና የጽሁፍ አወቃቀር ጥብቅ ቁርኝት እንዳለቸው በጥናታቸው አሳይተዋል።

Armbuster, Andessen and Ostertage (1987) የጽሁፍ አወቃቀር ከንባብ መማርን ያቀላጥፍ እንደሆነ በአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ጥናት አካሂደዋል። የጽሁፍ አወቃቀርን በቀጥታ ማስተማር የጽሁፉን ዋና ሃሳብ እንዲያወጡ የሚያስችል፣ አንብቦ የመረዳትንና መልሶ የማስታወስ ችሎታን እንደሚያጎለብት በጥናታቸው አመላክተዋል።

በአጠቃላይ በጥናቶቹ ውጤት እንደተገለጸው የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጎልበት የጽሁፍ አወቃቀርን መጠቀም አስፈላጊነቱ የጎላ እንደሆነና የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከጽሁፍ አወቃቀር ጋር አወንታዊ ግንኙነት እንዳለው መገንዘብ ይቻላል።

## 2.3 የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት አስፈላጊነትና አተገባበር ስልት

### 2.3.1 የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት አስፈላጊነት

Padua (2008) የጽሁፍ መዋቅር ትምህርት በአንድ ጽሁፍ ይዘት ስር ወሳኝ የሆኑ መዋቅሮችን በማካተት ተማሪዎች ቁልፍ የሆኑ እሳቤዎች ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ቀጥሎ የሚከተለውን ነገር እንዲተነብዩ ያግዛል።

Haydari and Mustapha (2009) እንዳመላከቱት፣ የጽሁፍ አወቃቀር፣ በጽሁፍ አማካይነት ፀሀፊው መረጃ ለመስጠት፣ ለመግለፅ፣ ለማብራራት፣ ለማግባባት የሚጠቀምበት ነው። አብዛኛዎቹ ትምህርታዊ ይዘት ያላቸው ጽሁፎች የሚቀርቡት አንዱን የጽሁፍ

አወቃቀር በመጠቀም ነው። ተማሪዎች ስለተለያዩ የጽሁፍ አወቃቀሮች ማወቃቸው ከጽሁፉ ውስጥ መለየት ያለባቸውን ሀሳቦች ለመለየት፣ የችግር መፍትሔ ተዛምዶን ለመገንዘብ፣ ጽሁፉ የተዋቀረበትን አደረጃጀት በመለየት፣ ወዘተ ሀሳቡን እንዲለዩ ያግዛቸዋል። የምክንያትና ውጤት ተዛምዶን ለመገንዘብና የጽሁፉን ሙሉ መልዕክት ለማስታወስ ይጠቅማቸዋል። ልክ እንደ ሌሎቹ የማንበብ ብልሀቶች የጽሁፍ አወቃቀር እውቀት ለተማሪዎች በጣም ጠቃሚ ስለሆነ ትምህርቱ በግልፅና በዘዴ ሊሰጣቸው ይገባል።

እንደ Garner and Gillingham (1987) ገለጻ አንባቢው ስለጽሁፍ አወቃቀር እውቀት ከሌለው በየትኛውም የአነባበብ እቅድ ስለማይጠቀም ድክመት ይታይበታል። ነገር ግን አንባቢዎች ከጽሁፍ አወቃቀር ጋር ከተዋወቁ ጽሁፉ የቀረበበትን መንገድ ያውቃሉ። ጽሁፉ የተደራጀበት መንገድ ማወቅም በጽሁፍ ውስጥ የቀረበውን መረጃ ለመለየት ያስችላቸዋል። የመረዳት አቅምንም ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲጨምር ያደርጋል። ጽሁፉ የተዋቀረበትን አደረጃጀት የሚለዩ ተማሪዎች የአነበቡትን ጽሁፍ ሀሳብ በበለጠ የማስታወስ አቅም ይኖራቸዋል።

Meyer, Brandt and Bluth (1980) እንደሚያስረዱት የጽሁፍ አወቃቀርን መለየት በማንበብ ክሂል ላይ ተመርኩዘው ለሚካሄዱ ጥናቶች ትልቅ ጠቀሜታ አለው። ይኸውም አንደኛ የጽሁፍ አወቃቀር ገጽታዎች በምንባቦች ውስጥ ያሉትን ተመሳስሎዎችና ልዩነቶች ከመገምገም አኳያ ትርጉም አዘል ገጽታ ያቀርባል። ሁለተኛ የጽሁፍ አወቃቀርን መለየት አንባቢው ከቀረበው ጽሁፍ ውስጥ ምን ያህል የመረጃ መጠንና አይነት ማስታዎስ እንደሚችል ለማወቅ ያስችለዋል። ሶስተኛ በጽሁፉና በአንባቢው የጽሁፍ ግንዛቤ መካከል የሚፈጠርን ልዩነት ለማወቅ ያስችላል። ስለሆነም የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር አንብቦ መረዳትን ለማጎልበት ወሳኝ ሚና ይኖረዋል።

Grabe (2002) ባካሔዱት ጥናት ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት ሶስት ሀሳቦችን ይጠቅሳሉ የመጀመሪያው ተማሪዎች በቀጥታ ስለ ጽሁፍ አወቃቀር በመማር የሚያገኙት እውቀት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው እንዲሻሻል ያደርጋል። በዚህም ስለ እያንዳንዱ የጽሁፍ አወቃቀር ያላቸው ግንዛቤ በቀላሉ ይጨምራል። ሁለተኛው ነጥብ የተማሪዎችን የጽሁፍ አወቃቀር ግንዛቤ ለማሳደግ አቀራረቡ በግራፍ፣ በቃላት፣ በአረፍተ ነገር፣ ካርታዎች፣ በዛፍ ምስል፣ የተደራጀ ማጠቃለያን በመስጠት መሆን አለበት። ጥናቱ እንደሚያሳየው የተማሪዎች ጽሁፍን የመረዳት ችሎታ የተሻለ የሚሆነው እንዴት መረጃው በጽሁፍ ውስጥ እንደተደራጀ ማየት

ሲቻል ነው። መረጃዎቹና ሀሳቦቹ እንዴት እንደተደራጁ የሚያሳዩ የተለያዩ አመላካቾች አሉ።ተማሪዎች የእነዚህን አመላካቾች ተግባር ከለዩ ቀጣይነትና ትርጉም ባለው ሁኔታ የንባብ ችሎታቸው ይሻሻላል። ሶስተኛው የሚሰጠው ትምህርት የንባብ ብልሃትን የተከተለ መሆን አለበት። ምክንያቱም አብዛኛው የንባብ ብልሃት ትኩረት የሚያደርገው የጽሁፉን መዋቅር መገንዘብ፣ የጽሁፉን ዋና ሀሳብ መለየትና አጠቃላይ የጽሁፉን ሀሳብ ማጥናትን ነው። ትምህርቱም ማጠቃለልን፣ መተንበይን፣ ዋናና ንዑስ ሀሳብን መለየትን ያካትታል። የንባብ ብልሃት ትምህርት አላማም የጽሁፍ አወቃቀሩንና ጽሁፉን ለመረዳት ያለ ግንዛቤን ማሻሻል ነው። ትምህርቱም የሚያተኩረው በጽሁፍ አወቃቀር አንብቦ የመረዳት ችሎታንና መማርን ለማሳደግ ነው።

Dymock (2005) የአንብቦ መረዳትን ብልሃት ማስተማር የተማሪዎችን ጽሁፍ የመረዳት ችሎታ በጥሩ ሁኔታ የሚያሻሽል ቢሆንም ከልምድ እንደሚታየው ብዙ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችግር አለባቸው። አንባቢው የሚያነበው ጽሁፍ የሚያምታታ ከሆነ ችግሩን ለማስወገድና ትርጉሙን ለመለየት የጽሁፍ አወቃቀሩን ማወቅ እንደ ብልሃት በመሆን ያገለግላል። መምህራን ይህን ችግር ለማስወገድ ዋናውን ሚና ይጫወታሉ። ጥሩ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ማሻሻያ ትምህርት የአንብቦ መረዳትን ችግር ያስወግዳል። የአንብቦ መረዳት ብቃትን በከፍተኛ ሁኔታ ያሳድጋል። ጥሩ አንባቢዎች የቀደመ ዕውቀታቸውን በመጠቀም፣ በማፍለቅ፣ ጥያቄዎችን በመመለስ፣ መረጃን በማጣቀስ ምናባዊ ምስል በመፍጠር፣ ማጠቃለያዎችን በመስጠትና ፀሀፊው የተጠቀመበትን አወቃቀር በመለየት የተለያዩ ብልሀቶችን ይጠቀማሉ። ተማሪዎችም ብልሃቱን ቢማሩ፣ ብልሀቱን እንዴት እንደሚጠቀሙ ያውቃሉ፤ ጥሩ የአንብቦ መረዳት ችሎታም ይኖራቸዋል። ምክንያቱም ስለ ጽሁፍ አወቃቀር እውቀት ያላቸው ተማሪዎች እውቀት ከሌላቸው ተማሪዎች በተሻለ የፀሀፊውን አወቃቀር በመለየት የጽሁፉን ሀሳብ ለማስታወስ ይሞክራሉ። በተጨማሪ ደካማ አንባቢዎች ያለባቸውን ጽሁፍን አንብቦ የመረዳት ችግር ለማቃለል የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት መሰጠቱ አስፈላጊ ነው።

እንደ Tinajero (n.o) አገላለፅ ንባብን የማስተማር አንዱ ጠቀሜታ ጽሁፎች ስለተፃፉበት አወቃቀር ግንዛቤን ለማዳበር ነው። ምክንያቱም የተማሪዎች የክፍል ደረጃ እየጨመረ ሲሔድ የትምህርቱ ይዘት ረጅም የተወሳሰበና ፅንሰ ሀሳባዊ እየሆነ ይሔዳል። አብዛኛዎቹ ጥናቶች በንባብ ዙሪያ ትኩረት የሚያደርጉት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ሊጨምር በሚችል ውጤታማ ብልሃት ላይ ነው። በዚህ ላይ የመምህሩ ሚና የንባብ ፍላጎትን ለማነሳሳት ጥሩ የሆኑ ጽሁፎችን

መምረጥና ማቅረብ ነው። ተማሪዎች የተለያዩ ጽሁፎች ከተደራጁበት የጽሁፍ አወቃቀር ጋር ከተዋወቁ፣ የነገሮችን ቅደም ተከተል ይለያሉ። በጽሁፍ ውስጥ ያለውን ሀሳብ በማወዳደርና በማነፃፀር ተመሳስሎና ልዩነት ያወጣሉ፤ በጽሁፍ ውስጥ ለቀረቡ ችግሮች መፍትሔ ሀሳቦችን ይፈልጋሉ፤ የጽሁፉን መልዕክት ይገነዘባሉ፤ የንባብ ፍላጎታቸው ይጨምራል፤ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውም ይጎለብታል።

Rapheel and Kirshner (1985) የማወዳደርና ወይም ማነፃፀር የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት በስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታ ላይ ባካሔዱት ጥናት እንዳመላከቱት የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት የጽሁፍ አወቃቀሩን እንዲለዩ፣ አደራጅተው እንዲፅፉ አስችሏቸዋል። የማስታወስ ችሎታቸውንም አሻሽሎታል።

በተመሳሳይ Garner and Gillingham (1987) የአምስተኛና የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የጽሁፍ አወቃቀር እውቀት በሚል ርእስ ጥናት ያካሄዱ ሲሆን የጥናቱ ውጤትም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ያላቸው ግንዛቤ መሻሻሉን አሳይቷል።

ከጥናቶቹ ውጤት ለመገንዘብ እንደሚቻለው የጽሁፍ አወቃቀር እውቀት የጽሁፍን ሀሳብ ለመገንዘብ ያስችላል። አብዛኛዎቹ ትምህርታዊ ይዘት ያላቸው ጽሁፎች የሚቀርቡት የጽሁፍ አወቃቀርን መሰረት በማድረግ ነው። ስለዚህ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት መስጠት አስፈላጊና ጠቃሚ መሆኑን የውጭ አገር ጥናቶች ያረጋግጣሉ። ይሁን እንጅ ይህ ንድፈ ሀሳብ በአገራችን የሚኖረው እንድምታ ግን የታወቀ አይመስልም።

### 2.3.2 የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት አተገባበር ስልት

Nikki (2010) ማንበብ በማንኛውም የትምህርት ዘርፍ ውጤታማነትን የሚያጎናጽፍ ወሳኝ የቋንቋ ክሂል ነው። ይሁን እንጅ የቋንቋ መምህራን አንብቦ መረዳትን ለማስተማር በሚጥሩበት ወቅት በርካታ ፈተናዎች ያጋጥሟቸዋል። ከፈተናዎቹ ውስጥ አንዱና ዋነኛው የአንብቦ መረዳት ክሂልን እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው ነው። በርግጥ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ መፈተሽ ቀላል ነው። ይሁን እንጅ ቀድሞ እንዴት አንብቦ መረዳት እንደሚችሉ ማስተማር ያስፈልጋል። ውጤታማ ንባብ ሁልጊዜ ችግርን ከመፍታት ጋር ይያያዛል። አንድን ጽሁፍ ከማንበባቸው በፊት፣ በማንበብ ወቅት እያሉና ከማንበብ በኋላ የተማሪዎችን ግንዛቤ መቃኘት አንባቢዎቹ ጽሁፉን ምን ያህል እንደተረዱትና ምን ዓይነት

ክትትልና ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው መረጃ የሚሰበሰብበት መንገድ በመሆኑ መምህራን ይህንን ዘዴ ቢጠቀሙ ውጤታማ ይሆናሉ።

Gentry (2006) ከጽሁፍ ውስጥ ትርጉም ያለው ትምህርት ለመማር ሶስት መሰረታዊ ሂደቶችን ማለፍን ይጠይቃል መምረጥ፣ ማቀናጀትና መረጃን ማዋሀድ ናቸው። መምረጥ ማለት፤ በተማሩት ተግባር መሰረት መረጃን በበቂ ሁኔታ ማውጣት፣ ማቀናጀት፣ የየአንቀፆቹን ሀሳብ በትክክል መለየት፣ በቅደም ተከተል ማደራጀት፣ መረጃን ማዋሃድ፣ በጽሁፍ የቀረበውን መረጃ በአንባቢው ውስጥ ካለመረጃ ሀሳብ ጋር ማያያዝን ይመለከታል።

Akhondi, Malayeri and Samod (2011) እንደገለፁት፣ ተማሪዎች እንዲገነዘቧቸው የሚፈለጉት የጽሁፍ አወቃቀር አይነቶች ቅደም ተከተል፣ ገለፃ፣ ማወዳደርና ማነፃፀር፣ ምክንያትና ውጤት፣ ችግር-መፍትሔ ናቸው። እነዚህን የጽሁፍ አወቃቀሮች መለየት ከቻሉ በንባብ ወቅት ሀሳቡን ለመረዳት በጣም ቀላል ይሆንላቸዋል። ተማሪዎች የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርትን ሲተገብሩ የጽሁፍ አወቃቀሩን ከማስተማር በፊት ተማሪዎቹን ማነቃቃት፤ ፀሀፊው መረጃውን ለማደራጀት ስለተጠቀመበት የጽሁፍ አወቃቀር ከተማሪዎች ጋር ውይይት ማድረግ፣ የጽሁፍ አወቃቀሮችን በቅደም ተከተል ማስተዋወቅ። በየትኛውም የቅድመ ንባብ ተግባራት የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በማቅረብ የጽሁፍ አወቃቀሩን እንዲተነብዩ ማድረግ፤ የጽሁፍ አወቃቀሮቹ የሚጠቀሙባቸውን ፍንጭ ሰጭ ቃላትና ሀረጋት ማስተዋወቅ፤ አመላካቾችን መቸና እንዴት እንደሚጠቀሙ በግልፅ ማሳየት፤ ጽሁፎቹን በሚያነቡበት ወቅት አስፈላጊ በሆነ ቦታ ላይ ከንባብ በማረፍ ሀሳቡን መረዳታቸውን መከታተል፤ የጽሁፍ አወቃቀሩን ትኩረት አድርገው የተዘጋጁ ጥያቄዎችና መልመጃዎችን ማቅረብ፤ ሀሳባቸውን በአንድ የጽሁፍ አወቃቀር ተጠቅመው እንዲገልፁ ማድረግ፤ ማንበብና መፃፍን ማቀናጀት፣ የተዘጋጀውን ጽሁፍ በቅድመ ንባብ፣ በንባብ ወቅትና በድህረ ንባብ ጥያቄዎችና ተግባራት አደራጅቶ ማስተማር በማንኛውም ጊዜ እንዲያነቡና እንዲፅፉ ማበረታታት ናቸው።

ከላይ ለማየት እንደተሞከረው የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርትን በክፍል ውስጥ ለመተግበር መምህራን ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ምንነት፣ ስለሚጠቀሟቸው ፍንጭ ሰጭ ቃላትና ሀረጋት ከተማሪዎች ጋር ውይይት በማድረግ፣ የማንባብ ትምህርት የሚቀርብባቸውን ደረጃዎች በመጠቀም ክሂሎችን አቀናጅቶ በማስተማር ተግባሩን ማከናወን ይቻላል።

2.4 አንብቦ መረዳት

አንብቦ መረዳትን በተመለከተ Grellet በመጥቀስ አለም (1991) እንደሚከተለው ይገልጹታል። አንብቦ መረዳት ማለት ከአንድ አሀድ ውስጥ ተፈላጊውን መረጃ በብቃት መሰብሰብ መቻል ማለት ነው። በዚህ አይነት ሂደት ውስጥ አንባቢው የማይፈልገውን መረጃ እያንገዋለለ በመተው የሚፈልገውን አይነት ብቻ ሊመርጥ ይችላል። በዚህም አንዱን መሰረታዊ አሀድ ከመረዳቱም ባሻገር የአሀዱን ዝርዝር በብቃት የሚገነዘብበት ሁኔታ የሚጠቃለለው እዚሁ ውስጥ ነው። በማለት ይገልጻሉ።

Smith (1985) በበኩላቸው አንብቦ መረዳት አንባቢው ቀድሞ ይዟቸው ለተነሳቸው ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ማለት ነው። ጥያቄ መጠየቅ የአንብቦ መረዳት ትምህርት ባህሪ ነው። አንባቢው ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች መልስ ካገኘ በአንባቢውና በጸሀፊው መካከል ተግባቦት ይፈጠራል። ተግባቦት የሚኖረው ደግሞ መረዳት ሲኖር ነው።

ሰለሞን (2003) የተለያዩ ምሁራንን ዋቢ በማድረግ አንብቦ መረዳት የሚከተሉትን ነጥቦች እንደሚያካትት ይገልጻሉ።

ሀ. የቃላትን ፍቺ መገንዘብ አንባቢው በጽሁፉ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት አውዳዊ ፍች ሊረዳ ይችላል ይሁን እንጅ የጽሁፉን መልእክት ለመረዳት የእያንዳንዱን ቃል ፍች ማወቅ የግድ ስላልሆነ አንባቢው በጽሁፉ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት አንድ በአንድ መመርመር አይጠበቅበትም።

ለ. የጽሁፉን ግልጽ መልእክት መገንዘብ አንባቢው በጽሁፉ ውስጥ በግልጽ የተቀመጠውን መልእክትና ይህንን መልእክት ለማጎልበት ሆነ ለማጠናከር የገቡትን ዝርዝር ሀሳቦች መረዳት የሚመለከት ነው።

ሐ. የጽሁፉን ውስጣዊ መልእክት መገንዘብ በጽሁፉ ውስጥ በግልጽ የቀረበውን መልእክት መገንዘብ የአንብቦ መረዳት ዋነኛ አካል ቢሆንም አንባቢው በዚህ ብቻ ተወስኖ መቅረት የለበትም። በግልጽ የተመለከተውን መልእክት መነሻ በማድረግ በመገንዘብና በመመርመር የሚደርስበትን ውስጣዊ መልእክት መረዳት ይጠበቅበታል።

መ. የአያያገሮችን ሰዋስዋዊ አገባብና ትርጉም መገንዘብ አንድ አንባቢ በሚያነበው ጽሁፍ ውስጥ የሚገኙትን አገባብ፣ አገልግሎትና ትርጉም መገንዘብ ይጠበቅበታል። እነዚህን መገንዘቡ የጽሁፉን መልእክት ለመረዳት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክትለታል።

የጽሁፉን ቅደም ተከተል የሀሳብ ፍሰት መገንዘብ አንባቢው በጽሁፉ ውስጥ ያሉትን አረፍተ ነገሮች ተናጠላዊ መልእክት መረዳቱ ብቻ በቂ አይደለም። ከዚህ ባሻገርም የጽሁፉን ቅደም ተከተላዊ የሀሳብ አገላለጽ አንዱ አረፍተ ነገር ከፊተኛው ጋር ያለውን የሀሳብ ግንኙነት የተለይዩ አንቀጾች ያላቸውን የእርሰስ በርስ ግንኙነት ሊረዳ ይገባዋል። የሚሉት ነጥቦች የአንብቦ መረዳት አካላት ናቸው።

አንብቦ መረዳት የአንድን ጽሁፍ ሀሳብ መረዳትንና በሚገባ መጨበጥን የሚገልጽ እሳቤ እንደሆነና የጸሀፊውን ሀሳብ ወይም መልእክት መለየትን፣ አውዳዊ ፍችዎችን መገንዘብንና ከአውዱ ውጭ የሆኑ ፍችዎችንም መረዳትን የሚያጠቃልል እንደሆነ Shanehan (2006) ይገልጻሉ።

Shanehan (2006) አንብቦ መረዳትን በሁለት ይከፍሉታል። አንደኛ በምንባቡ ውስጥ በግልጽ የሰፈሩ ሀሳቦችን አንብቦ መረዳት ነው። በዚህ ስርም በጽሁፍ ውስጥ የቀረቡትን ዋና ዋና ሀሳቦች መገንዘብ፣ በግልጽ የተቀመጡ ድርጊቶች፣ ክስተቶችና ቅደም ተከተል ማስታወስ፣ በጽሁፍ ውስጥ የሰፈሩ ተመሳሳይና ልዩነቶችን መለየትና የምክንያትና ውጤት ትስስር መግለጽን ያካትታሉ። ሁለተኛ ተማሪዎች ተጠየቃዊ እውቀትንና ግምትን በመጠቀም በምንባቡ ውስጥ በግልጽ ያልሰፈሩ ሀሳቦችን አንብበው የሚረዱበትን ሁኔታ ይጠቁማል። ይህ አይነት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደግሞ ካሉት መረጃዎች በመነሳት የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ መለየትንና ደጋፊ ሀሳቦችን ለይቶ ማወቅን ከምክንያትና ከውጤት ትስስር የተነሳ ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለውን ነገር መገመትን የሚመለከት ነው።

Nuttal (1996) እንደገለጹት አንብቦ መረዳት ማለት ለንባብ የቀረበውን ጽሁፍና የአንባቢውን አእምሯዊ እውቀት እንዲሁም ስነ ልሳናዊ ችሎታ በሂደት በማገናኘት ለተጻፈው ጽሁፍ ትርጉም መስጠት ነው።

ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት እንደተቻለው አንብቦ መረዳት ከጽሁፍ ውስጥ መረጃ መሰብሰብ መቻልን፣ የቃላትን፣ የጽሁፍን መልእክት፣ የአያያዦችን ሰዋስዋዊ አገባብ፣ የጽሁፍን ቅደም ተከተልና የሃሳብ ፍሰትን መገንዘብን፣ በተጨማሪም አንባቢው ቀድሞ ይዞት ለተነሳው ጥያቄ ምላሽ መስጠትን በውስጡ የሚያካትት በአጠቃላይ በግልጽ የሰፈሩና ያልሰፈሩ ሀሳቦችን መረዳት መቻል ነው።

### 2.4.1 የአንብቦ መረዳት ስልቶች

Harmer (1991) እንደገለፁት የተለያዩ ፅሁፎች ለተለያዩ አላማዎች ሲነበቡ አንባቢዎች የተለያዩ ስልቶችን መጠቀማቸው የግድ ነው። እነዚህም የንባብ ስልቶች የግርፍ (የምልከታ) ንባብ፣ የአሰሳ ንባብ፣ ሰፊ ንባብ እና ጥልቅ ንባብ በማለት በአራት ተከፍለዋል። የግርፍ ንባብ በአጠቃላይ የተፃፈውን ጽሁፍ ሀሳብ ለማግኘት የሚነበብበት ስልት ነው። ይህ ስልት ከሚነበበው ጽሁፍ የየአንቀፁን መንደርደሪያ ዐረፍተ ነገር ለመረዳት የምንጠቀምበት ነው። ሁለተኛው የንባብ ስልት ደግሞ የአሰሳ ንባብ የሚባለው ሲሆን፤ በፍጥነት የሚነብበበት ስልት ሆኖ ከቀረበው ፅሁፍ ውስጥ አንድ የተወሰነ መረጃን ነጥሎ ለማውጣት እና ለመረዳት የምንጠቀምበት ነው። ለምሳሌ ቁጥርን፣ ዓመተ ምህረትን እና ስምን ለመለየት ያገለግላል። ሶስተኛው ሰፊ ንባብ የሚባለው ደግሞ ብዙውን ጊዜ በቦታ እና በጊዜ ሳይወሰን አንባቢው ለመዝናናት ሲፈልግ የሚገለገልበት ስልት ነው። የሚነበበው ፅሁፍ ሰፊ በመሆኑ የፅሁፉን አጠቃላይ መልዕክት ለመገንዘብ የአንባቢውን ንቁ ተሳትፎ ይጠይቃል። የመጨረሻው ደግሞ ጥልቅ የንባብ ስልት የሚባለው ፅሁፉን በጥልቀት ለመገንዘብ ሲባል የፅሁፉ መጠን እንደሰፊ ንባብ ያልሰፋ በጊዜ እና በቦታ የተገደበ ሆኖ በንባብ ጊዜ ከፍጥነት ይልቅ በእርጋታ፣ በትኩረት እና በጥንቃቄ መከወንን የሚጠይቅ ነው። በጥልቀት ንባብ ጊዜ በፅሁፉ ውስጥ በግልፅ የሰፈሩ መረጃዎች ላይ ከማተኮር አንስቶ በፅሁፉ ውስጥ በግልፅ ያልሰፈሩ ሀሳቦችን አንድምታ እስከመስጠት የሚደረስበት የንባብ ስልት ነው ።

አንባቢው ከሚያገኘው ጠቀሜታ አንፃር ደግሞ ማንበብ ላዕላይ፣ ታህታይ እና አልቦ (ዜሮ) ንባብ በማለት በሶስት የንባብ ደረጃዎች የሚከፋፍሉዋቸው እንዳሉ ማረው (1998) Peyit (1998) ን በመጥቀስ ያስረዳሉ። ላዕላይ ንባብ አንባቢው ትኩረት በመስጠት የሚያነብበት ሆኖ አላማው የተሰጠውን ፅሁፍ በፍጥነት አንብቦ ለመጨረስ እና ሁሉንም ለመረዳት የሚሞከርበት ነው። ታህታይ የንባብ ደረጃ ደግሞ አንባቢው በሚያነበው ፅሁፍ ላይ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ዋናውን መልዕክት መረዳት እና ከተገለፀው ሀሳብ በተጨማሪ ያሉ ጉዳዮችን መመልከት፣ የነገሮችን ዝምድና መፈተሽ ወዘተ ተግባራትን ለማከናወን የምንገለገልበት ነው። በሌላ በኩል አልቦ (ዜሮ) የንባብ ደረጃ ያለምንም ትኩረት ፅሁፉን በፍጥነት አንብቦ መጨረስን የሚመለከት ነው (ማረው፣1998) ።

የንባብ ትምህርት የተለያዩ ስልቶችን እንደሚጠቀም ተገልጿል። እነሱም የግርፍ፣ የአሰሳ፣ ሰፊ እና ጥልቅ ንባብ ናቸው። ከአንባቢው ጠቀሜታ አንፃር ደግሞ ላዕላይ፣ ታህታይ እና አልቦ (ዜሮ) ንባብ በማለት በሶስት ይከፈላሉ። እነዚህ ስልቶች የየራሳቸው የአነባበብ መንገድ

አላቸው። ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው ጥልቅ የንባብ ስልትን ነው። ምክንያቱም ይህ የንባብ ስልት በጊዜ እና በቦታ የተገደበና በእርጋታ፣ በትኩረት እና በጥንቃቄ ስለሚከወን ነው።

### 2.4.2 የጥሩ አንብቦ የመረዳት ጥያቄ ባህሪያት

በአንድ በተወሰነ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመመዘን የሚያገለግለው ዋና መሳሪያ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና እንደሆነ Madson (1983) ይገልጻሉ። Nuttal (1996) እና Madson (1983) የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በማዛመድ፣ ትንበያ እንዲሰጡ በማድረግ፣ በአጭር መልስ ስጥ፣ በፃፍ፣ በምርጫ፣ በክፍት ቦታ ሙላ መጠየቅ እንደሚቻል ያስረዳሉ።

Hughes (1997) እንደገለጹት የአንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ሲዘጋጁ ከግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለባቸው ዋና ዋና ነጥቦች እንደሚከተለው ይገልጿቸዋል።

ሀ. ከሁሉም በፊት ጥያቄዎቹ በቀረበው ምንባብ ላይ መመስረት አለባቸው። የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልሶች ለማግኘት የግድ ምንባቡን ማንበብና መረዳት ያስፈልጋል። በፈተናው ውስጥ ተፈታኞቹ ጥያቄዎቹ የተመሰረቱበትን ምንባብ ሳያነቡና ሳይረዱ የሚመልሷቸው ጥያቄዎች መካተት የለባቸውም። ይሁን እንጅ አልፎ አልፎ አንብቦ መረዳትን ለመለካት የሚዘጋጁ ፈተናዎች ይህ ባህሪ ይኑሯቸዋል። ተፈታኞቹ ጥያቄዎቹ የተመሰረቱበትን ምንባብ ሳያነቡ ጥያቄዎቹን በትክክል ይመልሷቸዋል። የዚህም ምክንያቱ ጥያቄዎቹ በምንባቡ ላይ ባለመመስረታቸውና ቅድመ እውቀትን ስለሚጠይቁ ሊሆን ይችላል።

ለ. በተቻለ መጠን የፈተናው ጥያቄዎች የተጻፉባቸው ቃላት ሀረጋትና አረፍተ ነገሮች በቀጥታ ከምንባቡ የተወሰዱ ባይሆኑ ይመረጣል። ይህም ተፈታኞቹ ምንባቡን ሳይረዱ ቃላቱን ሀረጋቱን አረፍተ ነገሮቹን በማስታወስና ከምንባቡ በማገናዘብ ብቻ የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልሶች እንዳያገኟቸው ለመከላከል ያስችላል።

አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመመዘን የሚያገለግለው ዋና መሳሪያ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ሲሆን ለፈተና የሚቀርቡ ጥያቄዎች ሲዘጋጁ የቀረበውን ንባብ መሰረት ያደረጉ ፈተናው የሚጠቀማቸው ቃላትና ሀረጋት ከንባቡ በቀጥታ የተወሰዱ ባይሆኑ ፈተናው የተማሪዎችን ችሎታ የሚለካ ይሆናል።

### 2.4.3 የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃ አሰጣጥ

Nuttal (1982) እንደሚገልጹት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃ የሚታወቀው በአንብቦ መረዳት ፈተና በሚያስመዘግቡት ውጤት ነው። ለዚህም የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ፈተና በማቅረብ ከፈተናው በተገኘው ውጤት በቂ ደረጃ ላይ ደርሰዋል የሚባለው 70% ውጤት ማስመዝገብ ሲችሉ ነው።

ማስተዋል (1989) Narayanaswamy (1975)፣ Fry ( (1963)፣ እና kavale  (1979) በመጥቀስ  የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ እንደሚከተለው ይገልጹታል።።

Narayanaswamy (1975) እንደሚገልጹት በቂ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አለው የሚባል ተማሪ በተለመደው ፍጥነቱ በማንበብ በሚሰራው አንብቦ የመረዳት ፈተና 70% ሊያገኝ ይገባዋል። ውጤቱ 70% በላይ ከሆነም ጥሩ ችሎታ አለው ሊባል ይችላል። የተፈታኙ ውጤት 50% ወይም ከዚያ በታች ከሆነ ችሎታው በጣም ዝቅተና ደረጃ ላይ ይገኛል።

Fry (1963) እንደሚገልጹት ተማሪው በተሰጠው ፈተና ያገኘው ውጤት ከ70-80 % ከሆነ በቂ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አለው። ከ50-60% ወይም ከ5-6 ከአስር ውጤት ካገኘ ችሎታው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል።

kavale (1979) እንደገለጹት በአንብቦ መረዳት ፈተናው 90% ወይም ከዚያ በላይ ያገኘ ተማሪ ችሎታው በቂ ከሚባሉት ደረጃ ላይ ይገኛል። ውጤቱ ከ75% በታች ከሆነ ግን ችሎታው ዝቅተኛ ነው።

አንድ በአፍ መፍቻ ቋንቋው በቂ ችሎታ አለው የሚባል ተማሪ በሚሰጠው አንብቦ የመረዳት ፈተና ማግኘት ያለበትን ውጤት በተመለከተ Nuttal እና Narayanaswamy (በተመሳሳይ ውጤት ይስማማሉ። Fry እና kavale የሚስማሙበት ተመሳሳይ ውጤትም ቢሆን ከላይኞቹ ጋር የጎላ ልዩነት የለውም።

ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን ከሰጡት አስተያየት በመነሳት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል።

ሰንጠረዥ 1 የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃዎች

| ውጤት | ደረጃ |
|---|---|
| ከ100 | |
| 100-90 | ከፍተኛ |
| 80-70 | በቂ(መካከለኛ) |
| 60-50 | ዝቅተኛ |
| ከ50በታች | በጣም ዝቅተኛ |

(Nuttal (1982፣ 37)፣ ማስተዋል (1989፣ 13) )

## 2.4.4 የአንብቦ መረዳት የትምህርት አሰጣጥ ሂደት

ጥናቱ ሙከራዊ ስለሆነ ለተጠኚ ቡድኑ የጽሁፍ አወቃቀርን በማስተማር የአንብቦ መረዳት ክሂላቸውን ለማጐልበት ሶስት በምክንያትና ውጤት ሶስት በገለጻ የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጁ የማስተማሪያ ጽሁፎች በአጥኚዋ ተዘጋጅቷል ። ጽሁፎቹ የተዘጋጁትም Meyer, Brandt and Bluth (1980) Armbuster, Andessen and Ostertage (1987) የተጠቀሙባቸውን መሰረት በማድረግ ነው። በማስተማሪያ ፅሁፉ ውስጥ ተማሪዎች አንብበው የተረዱትን ሀሳብ በቃልና በፅሁፍ ምላሽ እንዲሰጡ ለማድረግ የቅድመ ማንባብ፣ የማንበብ ሂደትና የድህረ ማንበብ ተግባራት እንዲካተቱ ተደርጓል። ከምንባብ ውስጥ ዋና እና ዝርዝር ሃሳብን መለየት፣ የምንባብን ሃሳብ ማሳጠር፣ በገለጻና በምክንያትና ውጤት የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጁ ጽሁፎችን መለየት በምንባቡ ውስጥ ምክንያትና ውጤትን የያዘ ሀሳብ መዘርዘር፣ ምስል ከሳች የሆኑ በአእምሮ ውስጥ ምስል የፈጠረን ሀሳብ ማውጣት የሚያስችሉ አንብቦ የመረዳት ተግባራትን ለማከናወን ያስችል ዘንድ ተዘጋጅቷል። የማስተማሪያው ፅሁፍ በጥናቱ አማካሪና በዚሁ ትምህርት ቤት በሚገኙ ሁለተኛ ዲግሪ ባላቸው በሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተገምግሞ በትምህርት ሶስት የማንበብ ሂደት ጥያቄዎች በመብዛታቸው እንዲቀነሱ፣ ለትምህርት አምስት ለገለጻ የጽሁፍ አወቃቀር የቀረበው ጽሁፍ ከአደፍርስ የተወሰደ ምንባብ በመሆኑ በጽሁፉ ውስጥ የተካተቱት ቃላት በዚህ ክፍል ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች ለመረዳት አስቸጋሪ ናቸው። በሚሉት አስተያየት መሰረት እንደገና ተሸሽሎ ተዘጋጅቷል። (አባሪ "ሐ" ይመልከቱ)።

የጽሁፍ አወቃቀርን በማስተማር አንብቦ መረዳትን ለማጎልበት የተዘጋጀው ትምህርት የተለያዩ ትእዛዝ ያሉት፡- ምንባቡ የቀረበበትን የጽሁፍ አወቃቀር መለየት፣ ለቃላትና ለሀረጋት አውዳዊ ፍቺ መስጠት ፣ የምንባብን ዋና ዋና እና ዝርዝር ሃሳቦች መግለጽ ለይቶ

ማውጣትና፣ ከምንባቡ ምክንያትና ውጤትን ማውጣትና በአእምሮ ውስጥ ምስል የከሰቱ ነገሮችን መለየት የሚሉ መልመጃዎችን ይዘዋል። ተሳታፊ ተማሪዎች በተቃራኒ ፈረቃ ማክሰኞና ሀሙስ ለአምስት ሳምንታት በቀን ለአንድ ስአት በአጥኚዋ ተምረዋል።

ተግባራቱም ከዚህ በታች ቀርበዋል።

በመጀመሪያው ሳምንት ስለ ጽሁፍ አወቃቀር፣ በጽሁፍ ውስጥ ስለሚገኙ ፍንጭ ሰጪ ቃላትና ሀረጋት የቀደመ እውቀታቸውን በመጠቀም እንዲመልሱ ጥያቄዎች የቀረቡላቸው ሲሆን፣ ተማሪዎች ከጽሁፍ አወቃቀር ጋር እንዲተዋወቁ በተለያዩ የጽሁፍ አወቃቀሮች የተደራጁ ጽሁፎች ለማስተማሪያነት በማቅረብ በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ ፍንጭ ሰጭ ቃላትና ሀረጋት የጽሁፍ አወቃቀሩን ለመለየት እንደሚያስችሉ በመግጽ ተማሪዎች ከጽሁፍ አወቃቀሩ ጋር እንዲተዋወቁና በቂ ግንዛቤ እንዲጨብጡ የጽሁፍ አወቃቀሮችን በመዘርዘር ትምህርቱ ተሰጥቷል። (አባሪ "ሰ" ይመልከቱ)።

የጽሁፍ አወቃቀርን መለየት፣ ከምንባቡ ለወጡ ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍች መስጠት፣ ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች ምላሾችን መስጠት የሚሉት የሁለተኛው ሳምንት የትምህርት ይዘቶች ነበሩ። ለዚህ ሳምንት ለማስተማሪያነት የቀረበው ጽሁፍ በገለጻ የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጀ ነው። ተማሪዎች ጽሁፉን በለሆሳስ በማንበብ የክፍልና የቤት ስራዎችን እንዲሰሩ በግላቸው በሰጡት መልስ በጋራ እንዲወያዩ ተደርጓል። (አባሪ "ሰ" ይመልከቱ) ።

በሶስተኛው ሳምንት በምክንያትና ውጤት የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጀ ጽሁፍ ለማስተማሪያነት በማቅረብ የጽሁፍ ወቃቀሩን እንዲለዩ፣ የጽሁፉን ዋናና ዝርዝር ሀሳብ እንዲገልጹ የሚያደርጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ትምህርቱ ተከናውኗል። (አባሪ "ሰ" ይመልከቱ)።

ለአራተኛው ሳምንት በገለጻና በምክንያትና ውጤት የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጁ ሁለት ጽሁፎች ቀርበዋል። ምንባቦቹን በለሆሳስ በማንበብ አወቃቀራቸውን እንዲለዩ፣ አወቃቀሩን እንዲለዩ ያገዟቸውን ፍንጭ ሰጭ ቃላትና ሀረጋት እንዲዘረዝሩ፣ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን መጀመሪያ በግላቸው ከሰሩ በኋላ በቡድን እንዲወያዩ በማድረግ ትምህርቱ ቀርቧል። (አባሪ "ሰ"ይመልከቱ)።

በአምስተኛው ሳምንት ሁለት ጽሁፎች ለማስተማሪያነት በማቅረብ ከነሱ የወጡ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ በማዘዝና በአምስቱ ሳምንት ትምህርት በተከናወኑ ተግባራት ላይ አስተያት እንዲሰጡ በማድረግ የሙከራ ትምህርቱ ተጠናቋል። (አባሪ "ሰ" ይመልከቱ)።

## 2.5 የቀደምት ስራዎች ቅኝት

ሰለሞን (2003) ልቦለድን በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ በሚል ርእስ በዘጠነኛና በአስረኛ ክፍል ጥናት አካሂደዋል። የጥናቱ አላማም በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ልቦለዶች ከአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብና ከጥሩ ምንባብ ባህሪ አንጻር መፈተሸና መተንተን ነው። ለጥናቱ የተጠቀሙበት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ምልከታ፣ የጽሁፍ መጠይቅና የሰነድ ፍተሻ ናቸው። በጥናታቸው ማጠቃለያም መምህራን የአንብቦ የመረዳት ትምህርቱን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ የአንብቦ መረዳት ደረጃዎችንና ስልቶችን እንደማይጠቀሙ ጠቁመዋል። ይሁን እንጅ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ስራዎች ወጥ፣ ሳቢ፣ ግልጽነትና ተገቢነት ያላቸው መሆኑን ገልጸዋል።

የሰለሞን ጥናት አንብቦ መረዳት ላይ ትኩረት ማድረጉ ከዚህ ጥናት ጋር ሲያመሳስለው በመምህራን የአንብቦ መረዳት ትምህርት አተገባበር፣ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ በሚገኙ የልቦለድ ስራ ላይ ማተኮሩ፣ በተጨማሪም በተጠቀመው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የሰለሞን ጥናት ከዚህ ጥናት ይለያል።

ነብዩ (2005) በግጥም አማካኝነት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ የአንብቦ መረዳትና የጽህፈት ችሎታ ማዳበር በሚል ርእስ ያካሄዱት ጥናት አላማ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ የአንብቦ መረዳትና የጽህፈት ችሎታ ለማዳበር ግጥም ያለውን ሚና በሙከራ ማረጋገጥ ነው። የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹም ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ናቸው። የጥናቱ ውጤትም በፈጠራ ጽሁፎች አማካኝነት ቋንቋን ማስተማር የቋንቋ ክሂሎችን እንደሚያዳብር ገልጿል።

ይህ ጥናት ሙከራ ያደረገው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ መፈታ ላይ በመሆኑ ከነብዩ ጥናት ጋር ሲመሳስል ተማሪዎች የቀረበውን ጽሁፍ ብቻ አንብበው እንዲረዱ ሳይሆን በጽሁፉ አወቃቀር ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ በማድረጉ ልዩነት አሳይቷል።

አማረ (2003) በስነ ጽሁፍ የንባብ ክሂልን የማስተማር አተገባበር በሚል ርእስ በአስረኛ ክፍል ጥናት አድርገዋል። አላማውም የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በስነ ጽሁፍ የንባብን ክሂል እንዴት እንደሚያስተምሩ ማጥናት ነው። ከጥናቱ የተገኘው ውጤትም በስነ ጽሁፍ አማካኝነት ቋንቋን ማስተማር አተገባበሩ ዝቅተኛ መሆኑን አሳይቷል።

የአማረ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ያለው ተመሳሳይነት በአንብቦ መረዳት ላይ የተሰራ መሆኑ ነው። ይህ ጥናት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንጅ የመምህራንን አተገባበር ያላየ መሆኑ ልዩ ያደርገዋል።

ማስተዋል (1989) በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ጥናት አካሂደዋል። የጥናቱ አላማም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማጥናት ነው። ጥናቱ በመረጃ መሰብሰቢያነት ፈተና፣ ምልከታና የጽሁፍ መጠይቅን ተጠቅሟል። በጥናቱ የተገኘው ውጤት የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆኑን አመላክቷል።

በአንብቦ መረዳት ላይ የተሰራ መሆኑ ከማስተዋል ጋር ሲመሳሰል፣ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመፈተሽ የተጠቀመበት መንገድና በተጠቀማቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ልዩነት አሳይቷል።

ጌትነት (2001) በረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር ያለው ውጤታማነት በሚል ርእስ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ጥናት አካሂደዋል። የጥናቱ አላማ በረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር ያለው ውጤታማነት መመርመር ነው። ከክሂሎች እውቀት በተጨማሪ ሌሎች በርካታ ጥቅሞች እንዳሉት የተገኘው መረጃ ጠቁሟል።

ቅንጫቢን በመጠቀም ቋንቋን ማስተማሩ ከዚህ ጥናት ጋር ሲያመሳስለው ይህ ጥናት በጽሁፍ አወቃቀር ላይ እንጅ በአጠቃላይ ቋንቋን በማስተማር ላይ የተሰራ አለመሆኑ ከጌትነት የተለየ አድርጎታል።

የኔሰው (1990) በኦሮሞኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪ ሞዴልን በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋጽኦ በሚል ርእስ ያካሄዱት ጥናት አላማ አማርኛ ቋንቋ ኢ. አፍ መፍቻ ቋንቋ ለሆናቸው ተማሪዎች በተለይም በኦሮሞኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር የሚያስችላቸውን የንባብ ክሂል

ማስተማሪያ ሞዴል መፈለግ ነው። ጥናቱ ፈተናን በመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀመ ሲሆን የጥናቱ ውጤትም ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪ ሞዴል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ መሻሻልን ያሳየ መሆኑን ጠቁመዋል።

የየኔሰውን ጥናት በአንብቦ መረዳት ላይ የተሰራ መሆኑና በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያው ከዚህ ጥናት ጋር ሲመሳሰል ይህ ጥናት በአፈፊት ተማሪዎች ላይ የተሰራ መሆኑ ልዩ ያደርገዋል።

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ሁሉም ድርሳናት የአንብቦ መረዳት ችሎታን መፈተሻቸውና በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የተካሄዱ መሆናቸው ከዚህ ጥናት ጋር ሲያመሳስላቸው፣ ጥናቶቹ የጽሁፍ አወቃቀር አንብቦ ለመረዳት ያለውን ጠቀሜታ ስላልዳሰሱ ይህንን ክፍተት ለመሙላት የተካሄደ ጥናት በመሆኑ ጥናቱን አዲስና ልዩ ያደርገዋል። በተጨማሪም በዘመን፣ በቦታ፣ በተጠኚዎች ብዛት ከጥናቶቹ ልዩነት አሳይቷል።

# ምእራፍ ሶስት

## የአጠናን ንድፍና ዘዴ

### 3.1 የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት የተከናወነው ሙከራዊ (Experimental) የምርምር ስልትን ተከትሎ ሲሆን ጥናቱ አንድ ተጠኚ ቡድን ብቻ የያዘና የአንድ ቡድን ቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተና ንድፍን (one group pre test post test design) ተግባራዊ ያደረገ ነው። በቅደመና በድህረ ፈተናዎቹና በጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ መጠናዊ በሆነ መንገድ በቲቴስት በማነጻጸርና

በድምዳሚያዊ ስታትስቲክስና በገላጭ ዘዴ ተተንትኗል። ይህም ሳይማሩና ከተማሩ በኋላ በተሰበሰቡት መረጃዎች አማካኝነት የተገኘውን የችሎታ ልዩነት ለመለካት የሚያስችል ነው።

## 3.2 የመረጃ ምንጮች

የዚህ ጥናት የመረጃ ምንጮች በደቡብ ጎንደር ዞን በሊቦ ከምከም ወረዳ በአዲስ ዘመን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ የ9ኛ "D" ክፍል ተማሪዎች ናቸው።

## 3.3 የናሙና አመራረጥ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማጎልበት ያለውን ሚና መመርመር ሲሆን ጥናቱ ያተኮረው በደቡብ ጎንደር ዞን በሊቦ ከምከም ወረዳ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በአዲስ ዘመን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው። ትምህርት ቤቱ የተመረጠው አመች ናሙና ዘዴን በመጠቀም ነው። ምክንያቱም አጥኚዋ በዚህ ትምህርት ቤት ለዘጠኝ አመታት የሰራችና አሁንም በመስራት ላይ ያለች በመሆኑ መረጃን በቀላል መንገድ ለመሰብሰብ አመች በመሆኑ ነው።

በዚህ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ እና የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ይገኛሉ። በጥናቱ የተካተቱት በ2009 ዓ.ም በ9ኛ ክፍል በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች ናቸው። በዚህም የክፍል ደረጃ 1052 ተማሪዎች በመማር ላይ ይገኛሉ። በአንድ የመማሪያ ክፍል ደግሞ በአማካይ 55 ተማሪዎች ይማራሉ። ሁሉንም ተማሪዎች በጥናቱ ማካተት ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ እና ጊዜ ስለሚጠይቅ፣ ጥናቱ በሙከራ ላይ የተመሠረተ በመሆኑና የጥናቱን አስተማማኝነትና ተገቢነት ለመጠበቅ የተማሪዎችን ቁጥር መወሰን የግድ ነው። በዚህ ምክንያት ሁሉንም የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተሳታፊ ማድረግ አልተቻለም። በዚህም መሠረት የአንድ ክፍል ተማሪዎች ተጠኝ ለማድረግ በመጀመሪያ የሁሉም የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የችሎታ ስብጥር ተመሳሳይ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ የክፍል ድልድሉ ውጤትን መሠረት ያደረገ መሆኑን አጥኚዋ ከትምህርት ቤቱ ባገኘችው መረጃ አረጋግጣለች። ስብጥሩ ከተረጋገጠ በኋላ ሁሉንም የመማሪያ ክፍሎች እጣ ውስጥ በማስገባት በዕድል ሰጪ ናሙና ዘዴ የ9ኛ "D" ክፍል ተማሪዎች ተመርጠዋል። በዚህ ክፍል 55 ተማሪዎች የተመዘገቡ ሲሆን 3ቱ ተማሪዎች ትምህርቱን በማቋረጣቸው በመማር ላይ የሚገኙት 52 ተማሪዎች ናቸው። የትምህርት ቤቱ አስተዳደርና የተማሪዎቹ ሙሉ ፈቃድና ይሁንታ ተጠይቆ ጥናቱ ተካሂዷል። ጥናቱም በአንድ ቡድን ላይ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ ሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች በጥናቱ በተሳታፊነት ተካተዋል።

### 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ መረጃ እንዲያስገኙ የተመረጡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ፈተና እና የጽሁፍ መጠይቅ ናቸው።

#### 3.4.1 ፈተና

በዚህ ጥናት ፈተና ዋናው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው። ዓላማውም የጥናቱን ተሳታፊዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት ነው። ለተማሪዎች የቅድመ እና የድህረ ትምህርት ፈተና በአጥኚዋ ተዘጋጅቷል። ለቅድመ ትምህርት ፈተናው በምክንያትና ውጤት እና በገለጻ የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጁ ሁለት ምንባቦች ተመርጠዋል። ከሁለቱ ምንባቦች የተዘጋጀው ፈተና ሶስት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው ክፍል ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለቃላት ፍቺ መስጠትን የሚጠይቁ ስድስት ጥያቄዎችን አካቷል፤ ሁለተኛው ክፍል የሀረጋትን አውዳዊ ፍቺ የሚጠይቁ አራት ጥያቄዎችን ይዟል፤ ሶስተኛው ክፍል ደግሞ የምንባቡን አጠቃላይ መልዕክት የሚጠይቁ 12 ጥያቄዎች አካቷል። (አባሪ "ሀ" ን ይመልከቱ)። ፈተናው የታረመው ከ60 ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል ጥያቄዎች 12፣ ሁለተኛው 12፣ የሦስተኛው ክፍል 36 ነጥብ ይዘዋል። ፈተናው ተማሪዎቹ ጽሁፉ የተደራጀበትን የጽሁፍ አወቃቀር የመለየት አቅማቸውን፣ የቃላትን አገባባዊ ፍቺ እንዴት እንደሚገነዘቡ፣ በምንባብ ውስጥ ሀረጋት የሚያስተላልፉትን መልዕክት የመረዳት ችሎታቸው ምን ያህል እንደሆነ፣ ከምንባብ ውስጥ ዋና ዋና ሃሳቦችን ማውጣትና አጠቃላይ የምንባቡን መልዕክት የመረዳት ችሎታቸው እስከምን ድረስ እንደሆነ ለመለካት አስችሏል።

የፈተናውን አስተማማኝነትና ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሲባል በአጥኚዋ አማካሪና ጥናቱ በተካሄደበት ትምህርት ቤት በሚያስተምሩ ሁለተኛ ዲግሪ ባላቸው ሁለት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራን ተገምግሞ ለፈተናው የቀረበው ጽሁፍ ረጅም በመሆኑ እንዲያጥርና የጥያቄዎቹ ብዛት ከሰላሳ ወደ ሀያ ሁለት ዝቅ እንዲል የማሻሻያ አስተያየት ተሰጥቶበት ተሻሽሎ ተዘጋጅቷል። ከዚህ በመቀጠል ተሳታፊዎች የቅድመ ትምህርት ፈተናውን እንዲፈተኑ ተደርጓል።

ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ 1፡30 ሰዓት ነው። ተማሪዎቹ ፈተናውን ሰርተው እንደጨረሱ የፈተናው የመልስ ወረቀት በአጥኚዋ ተሰብስቧል። ከዚያም በተዘጋጁት የማረሚያ መልሶች መሰረት ፈተናው በሶስት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ታርሟል። (አባሪ "ረ"

ይመልከቱ)። ውጤት አሰጣጡ ሶስት የተለያዩ አራሚዎች ለአንድ ተማሪ የሰጡት ውጤት ተደምሮና ተካፍሎ የተገኘው አማካይ ነጥብ ዋና ውጤት ተደርጐ ተወስዷል።

ከዚህም በመቀጠል የጥናቱ ተሳታፊዎች በገለጻ እና በምክንያትና ውጤት የጽሁፍ አወቃቀር በተዘጋጀው የማስተማሪያ ፅሁፍ ለአምስት ሳምንታት በሳምንት ሁለት ቀን በየቀኑ ለአንድ ስዓት ከተማሩ በኋላ የድህረ ትምህርት ፈተናው ከቅድመ ትምህርት ፈተናው ጋር በተመሳሰለ መልኩ ተዘጋጅቶ በአጥኚዋ አማካሪና ጥናቱ በተካሄደበት ትምህርት ቤት በሚያስተምሩ ሁለተኛ ዲግሪ ባላቸው ሁለት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራን ተገምግሞ ተሰጥቷል። (አባሪ "ለ" ይመልከቱ)። እርማቱም የቅድመ ትምህርት ፈተናውን ባረሙት የ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን ተከናውኗል።

### 3.4.2 የጽሁፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቅ ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ሲሆን፣ አላማውም የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት በተማሪዎች የጽሁፍ አወቃቀር ግንዛቤ ላይ ለውጥ ማምጣቱን ለመፈተሽ ነው። የጽሁፍ መጠይቁ Piyonukool (2001) የጽሁፍ አወቃቀርን ተመርኩዞ ማንበብን ማስተማር የሚኖረውን ተጽእኖ አስመልክተው ባካሄዱት ጥናት የተጠቀሙበትን መጠይቅ መሰረት በማድረግ ለጥናቱ በሚያመች መንገድ ማሻሻያ ተደርጐ በአጥኚዋ የተዘጋጀ ነው። የጥያቄዎች ብዛት 10 ሲሆኑ በአይነታቸው ዝግ ሆነው የቀረቡ ናቸው። እያንዳንዳቸውም አራት አማራጮች አሏቸው። እነሱም፡-

1. በጣም አልስማማም
2. አልስማማም
3. እስማማለሁ
4. በጣም እስማማለሁ የሚሉ ናቸው።

የጽሁፍ መጠይቁ ለተሳታፊ ተማሪዎች ከመሰጠቱ በፊት በአጥኚዋ አማካሪና ጥናቱ በተካሄደበት ትምህርት ቤት በሚያስተምሩ ሁለተኛ ዲግሪ ባላቸው ሁለት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራን ተገምግሞ የጥናቱ አላማ የማንበብ ፍላጎትን የማይመለከት በመሆኑ ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ አራት ጥያቄዎች ተቀንሰው እንደገና ተሻሽሎ ተዘጋጅቷል። አባሪ "ሐ" ይመልከቱ። የተዘጋጁት ጥያቄዎች ትኩረትም ተማሪዎች ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ያላቸውን ግንዛቤ ለመፈተሽ ነው። የተማሪዎችን ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ያላቸውን ግንዛቤ ለመለካት የተዘጋጀው የፅሁፍ መጠይቅ ከቅድመ ትምህርት ፈተናው ጋር አብሮ ለተሳታፊ ተማሪዎች

ተሰጥቷል። የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በምክንያትና ውጤት እና በገለጻ የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጁ ጽሁፎችን ከመማራቸው በፊት በቅድመ ትምህርቱ ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ያላቸውን ግንዛቤ ለመለካት በቅድሚያ ፈተናውን በመቀጠል የፅሁፍ መጠይቁን ሞልተው እንዲሰጡ ተደርጓል (አባሪ "ሠ"ን ይመልከቱ)። በመጨረሻም ይኸው የፅሁፍ መጠይቅ የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ያላቸውን ችሎታ አሻሽሎል የሚለውን ለመፈተሽ ለጥናቱ የተዘጋጀው ትምህርት ሲጠናቀቅ ከድህረ ትምህርት ፈተናው ጋር አብሮ ለተሳታፊ ተማሪዎች ተሰጥቷል።

## 3.5 የመረጃ አተንተን ዘዴ

በቅድመ ትምህርት እና በድህረ ትምህርት በፈተና እና በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት የጥናቱ መረጃዎች በአግባቡ ተደራጅተው የማጣራት ስራ ከተከናወነ በኋላ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመለካትና ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ያላቸውን ችሎታ ለመፈተሽ ቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት ፈተና እና የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ ውጤቶችን ለማነፃፀር ዳግም ልኬታ ቲ ቴስት (Repeated Measures t-test) ቀመር አማካይነት ተሰልቷል። መረጃዎቹም በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተተንትነዋል።

# ምእራፍ አራት

# የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ

## 4.1 የመረጃ ትንተና

የጥናቱ መረጃዎች በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ ተሰብስበዋል። ለአተናተን እንዲሁም ለአቀራረብ ያመች ዘንድ መረጃዎቹ ለሁለት ተከፍለው ትንተና ተካሂዶባቸዋል። የመጀመሪያው የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተናዎች ትንተና የሚቀርብበት ሲሆን ሁለተኛው ክፍል የጽሁፍ መጠይቁ የሚተነተንበት ክፍል ነው።

### 4.1.1.ከቅድመ ትምህርት ፈተና የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ሰንጠረዥ፦2 ከቅድመ ትምህርት ፈተና የተገኙ ከፍተኛ፣ ዝቅተኛ፣ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት

| የፈተና አይነት | የናሙና ብዛት | ዝቅተኛ ውጤት | ከፍተኛ ውጤት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት ፈተና | 52 | 12 | 40 | 26.27 | 6.846 |

በሰንጠረዥ፡-2 እንደተመለከተው የጥናቱ ተሳታፊዎች በቅድመ ትምህርት ፈተናው ያስመዘገቡት ዝቅተኛ ውጤት 12 ሲሆን ከፍተኛ ውጤት ደግሞ 40 ነው። የጠቅላላ ተማሪዎች አማካይ ውጤት (26.27) መደበኛ ልይይቱም (6.846) መሆኑ ተገልጿል።

### 4.1.2 ከድህረ ትምህርት ፈተና የተገኙ መረጃዎች ትንተና

የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጎልበት የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርትን እንደ ብልሀት በመሆን እንደሚያገለግል በተዛማጅ ጽሁፉ 2.3.1 ተገልጿል። ለዚህም የቅድመ ትምህርት ፈተናው ከተሰጠ በኋላ የተከናወነው ተግባር ከሚያዚያ 17/ 8/ 2009 - ግንቦት 17/ 9/ 2009 ዓ/ም ለአምስት ሳምንታት የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በገለጻ እና በምክንያትና ውጤት የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጁ ጽሁፎችን በመጠቀም ማስተማር ነበር።

ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ተማሪዎች በቀረበው ትምህርት ለውጥ ማምጣት አለማምጣታቸውን ለመለካት ድህረ ትምህርት ፈተና እንዲሰጥ ተደርጓል።

**በሰንጠረዥ፡-.3 ከድህረ ትምህርት ፈተና የተገኙ ከፍተኛ፣ ዝቅተኛ፣ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት**

| የፈተና አይነት | የናሙና ብዛት | ዝቅተኛ ውጤት | ከፍተኛ ውጤት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|---|---|
| ድህረ ትምህርት ፈተና | 52 | 18 | 52 | 33.25 | 6.738 |

ከሰንጠረዥ፡-3 መረዳት እንደሚቻለው የጥናቱ ተሳታፊዎች በድህረ ትምህርት ፈተናው ያስመዘገቡት ዝቅተኛ ውጤት 18 ሲሆን ከፍተኛ ውጤት 52 ነው፣ የጠቅላላ ተማሪዎች አማካይ ውጤት ደግሞ (33.25) ነው። መደበኛ ልይይቱም (6.738) መሆኑ ተገልጿል።

የቅድመ ትምህርት ፈተና ዝቅተኛ ውጤት ከድህረ ትምህርት ፈተና ዝቅተኛ ውጤት ያነሰ ሲሆን፣ የድህረ ትምህርት ፈተና ከፍተኛ ውጤት ከቅድመ ትምህርት ፈተና ከፍተኛ ውጤት የበለጠ ሆኗል። ይህም የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ መሻሻል እንዳሳየ ያመላክታል።

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በሁለቱ ፈተናዎች አማካዮች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽም የዳግም ልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር ተግባር ላይ ውሏል። ውጤቱም በሰንጠረዥ 4 ቀርቧል።

### 4.1.3 የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት ፈተና ልዩነት በዳግም ልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት

**ሰንጠረዥ፡-4 የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና አንብቦ የመረዳት ችሎታ በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት**

| የፈተና ዓይነት | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የነፃነት ደረጃ | የቲ- ዋጋ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት ፈተና | 52 | 26.27 | 6.846 | 51 | 7.009* | 0.000 |
| ድህረ ትምህርት ፈተና | | 33.25 | 6.738 | | | |

*P<0.05

በሰንጠረዥ 4 እንደተመለከተው የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (33.25) ከቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (26.27) የሚበልጥ ይመስላል። በመደበኛ ልይይትም በኩል የድህረ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት ከቅድመ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት ያነሰ ቢመስልም ሁለቱም የተማሪዎች ውጤት ከአማካዩ ሰፊ ልዩነት እንዳለው የሚያመላክቱ ናቸው።

ከላይ እንደተገለጸው በሁለቱም አማካዮች መካከል የታየው ልዩነት በስታትስቲክስ ጉልህነት ያለው ስለመሆኑ መረጋገጥ ስላለበት ለዚህ ሲባል የዳግም ልኬታ ቲ- ቴስት ተግባራዊ ተደርጓል። በዚህም መሰረት በ 51 የነፃነት ደረጃ (ቲ = 7.009) የፒ ዋጋ (0.000) ከመቁረጫ ነጥቡ (0.05) አንሶ በመገኘቱ በሁለቱ አማካዮች መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት መኖሩን መረዳት ይቻላል። ይህም ለውጡ በጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት ምክንያት የመጣ መሆኑን ሊጠቁም ይችላል።

### 4.1.4 የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የተገኘ ውጤት ድግግሞሽ

የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃ በአንብቦ መረዳት ፈተናዎች ባገኙት ውጤት ማወቅ እንደሚቻል በ2.4.3 ተገልጿል። የጥናቱን ተተኳሪ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ ማወቅ ይቻል ዘንድ በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት የቀረበው ፈተና በሶስቱ አራሚዎች ከታረመ በኋላ በእያንዳንዱ ጥያቄ የተገኘው ውጤት ተደምሮ ከ60% ተይዟል።

**ሰንጠረዥ፡- 5 ከቅድመ ትምህርት ፈተና የተገኘ የውጤት ድግግሞሽ**

| የተማሪዎች ውጤት | ድግግሞሽ | % |
|---|---|---|
| 12 | 1 | 1.9 |
| 14 | 1 | 1.9 |
| 16 | 2 | 3.8 |
| 18 | 4 | 7.7 |
| 20 | 4 | 7.7 |
| 21 | 1 | 1.9 |
| 22 | 5 | 9.6 |
| 23 | 1 | 1.9 |
| 24 | 4 | 7.7 |
| 25 | 1 | 1.9 |
| 26 | 2 | 3.8 |
| 28 | 8 | 15.4 |
| 29 | 1 | 1.9 |
| 30 | 5 | 9.6 |
| 31 | 2 | 3.8 |
| 33 | 2 | 3.8 |
| 34 | 2 | 3.8 |
| 36 | 1 | 1.9 |
| 37 | 1 | 1.9 |
| 38 | 1 | 1.9 |

| | | |
|---|---|---|
| 39 | 1 | 1.9 |
| 40 | 2 | 3.8 |
| አጠቃላይ | 52 | 100.0 |

## ሰንጠረዥ፦ 6 ከድህረ ትምህርት ፈተና የተገኘ የውጤት ድግግሞሽ

| ተማሪዎች ውጤት | ድግግሞሽ | % |
|---|---|---|
| 18 | 1 | 1.9 |
| 20 | 1 | 1.9 |
| 22 | 3 | 5.8 |
| 26 | 1 | 1.9 |
| 28 | 4 | 7.7 |
| 30 | 10 | 19.2 |
| 32 | 6 | 11.5 |
| 34 | 4 | 7.7 |
| 35 | 4 | 7.7 |
| 36 | 8 | 15.4 |
| 38 | 2 | 3.8 |
| 40 | 2 | 3.8 |
| 42 | 2 | 3.8 |
| 44 | 1 | 1.9 |
| 45 | 1 | 1.9 |
| 50 | 1 | 1.9 |
| 52 | 1 | 1.9 |
| አጠቃላይ | 52 | 100.0 |

በሰንጠረዥ 5 እና 6 የተገለጸው የተማሪዎች ውጤት ድግግሞሽ ለትንታኔ ያመች ዘንድ ወደ 100% ተለውጧል። ይህንንም በሰንጠረዥ 7 ይመለከቷል።

**ሰንጠረዥ፦7 የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የተገኘ ውጤት ድግግሞሽ**

| ውጤት | ቅድመ ትምህርት ፈተና | | ድህረ ትምህርት ፈተና | |
|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 100-90 | 0 | 0 | 2 | 3.85 |
| 80-70 | 5 | 9.6 | 8 | 15.38 |
| 60-50 | 12 | 23.08 | 32 | 61.54 |
| ከ50 በታች | 35 | 67.31 | 10 | 19.23 |

በሰንጠረዥ 7 እንደተመለከተው በቅድመ ትምህርት ፈተናው ተማሪዎች ያስመዘገቡት ከፍተኛ ውጤት (100-90) ያገኙ ተማሪዎች ብዛት 0 (0%)፣ መካከለኛ ወይም በቂ (80-70) 5 (9.6%)፣ ዝቅተኛ (60-50) 12 (23.08%)፣ በጣም ዝቅተኛ ከ50 በታች 35 (67.31%) ናቸው። የአብዛኛዎቹ ተማሪዎች ውጤት አነስተኛ ነው። ይህም የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ያመለክታል።

በድህረ ትምህርት ፈተናው ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡት (100-90) ያገኙ 2 (3.85%)፣ በቂ (80-70) 8፣ (15.38%)፣ ዝቅተኛ (60-50) 32 (61.54%) እና ከ ከ50 በታች 10 (19.23%) ናቸው።

ይህ ውጤት የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ የተሸሻለ መሆኑን ያሳያል። በቅድመ ትምህርት ፈተናው የተመዘገበው በጣም ዝቅተኛ ውጤት 67.31% ከድህረ ፈተናው ውጤት 19.23% የበለጠ ሆኖ ተገኝቷል። በቅድመ ትምህርት ፈተናው ከፍተኛና መካከለኛ (በቂ) ውጤት ያገኙት ተማሪዎች 5 ብቻ ሲሆኑ በድህረ ትምህርት ፈተናው ግን 10 ተማሪዎች ከፍተኛና መካከለኛ ውጤት አግኝተዋል። ይህ የውጤት ልዩነትም በጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት የተገኘ መሆኑን ያሳያል።

### 4.1.5 ከቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

የጥናቱ ሁለተኛው መሰረታዊ ጥያቄ የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት የተማሪዎችን የጽሁፍ አወቃቀር ግንዛቤ ያሻሽል ይሆን? የሚል ነው። ይህንንም ጥያቄ ለመመለስ የዋለው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ዘዴ በተማሪዎች የሚሞላ ጽሁፍ መጠይቅ ሲሆን ተማሪዎች የቅደመ ትምህርት ፈተናውን ሲሰጡ መጀመሪያ ፈተናውን በመቀጠል የጽሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል። በጽሁፍ መጠይቅ አማካይነት የተሰበሰቡት መረጃዎች በገላጭና በድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ (በዳግም ልኬታ ቲ-ቴስት) ተተንትነዋል።

#### 4.1.5.1 ከቅደመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

ሰንጠረዥ፡- 8 ከቅደመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

| ተቁ | ጥያቄዎች | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ያለውን የሀሳብ ትስስር እለያለሁ። | 7 | 13.5 | 29 | 55.8 | 12 | 23.1 | 4 | 7.7 |
| 2 | የማነበውን ሁሉ ለመረዳት አልቸገርም። | 5 | 9.6 | 11 | 21.2 | 21 | 40.4 | 15 | 28.8 |
| 3 | የማነበው ጽሁፍ እንዲገባኝ የተለያዩ የማንበብ ብልሀቶችን እጠቀማለሁ፡ | 10 | 19.2 | 20 | 38.5 | 10 | 19.5 | 12 | 23.1 |
| 4 | የምንባቡን ሀሳብ አሳጥሬ መግለጽ እችላለሁ። | 7 | 13.5 | 18 | 34.5 | 15 | 28.8 | 12 | 23.1 |
| 5 | የማነበው ጽሁፍ እንዲገባኝ ጽሁፉ ለቀረበበት የጽሁፍ አወቃቀር ትኩረት እሰጣለሁ። | 7 | 13.5 | 6 | 11.5 | 27 | 51.9 | 12 | 23.1 |
| 6 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦችን ለመረዳት እቸገራለሁ። | 15 | 28.8 | 18 | 34.6 | 9 | 17.3 | 10 | 19.2 |
| 7 | አንብቦ ለመረዳት የጽሁፍ አወቃቀርን መረዳት አስፈላጊ መሆኑን አውቃለሁ ። | 9 | 17.3 | 19 | 36.5 | 11 | 21.1 | 13 | 25.0 |
| 8 | የማነበው ጽሁፍ የተደራጀበትን የጽሁፍ አወቃቀር መለየት እችላለሁ። | 11 | 21.2 | 20 | 38.5 | 9 | 17.3 | 12 | 23.1 |
| 9 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ የማገኛቸውን | 11 | 21.2 | 20 | 38.5 | 9 | 17.3 | 12 | 23.1 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፍንጭ ሰጪ ቃላትና ሀረጋት የምንባቡን መልእክት ለመረዳት ያግዙኛል። | | | | | | | | |
| 10 | እንብቦ ለመረዳት የጽሁፉን አወቃቀር ማወቅ ጠቀሜታ አለው ብዬ አላስብም። | 9 | 17.3 | 5 | 9.6 | 16 | 30.8 | 22 | 42.3 |

ከሰንጠረዥ 8 መረዳት እንደተቻለው መጠይቁን ከሞሉት 52 ተማሪዎች መካከል በአንደኛው ጥያቄ 16 (30.8%)፣ በሶስተኛው ጥያቄ 22 (42.3%)፣ በአምስተኛው ጥያቄ 39 (75.0%)፣ በሰባተኛው ጥያቄ 24 (46.2%)፣ በስምንተኛው ጥያቄ 21 (40.4%)፣ በዘጠነኛው ጥያቄ 34 (65.4%)፣ በአስረኛው ጥያቄ 38 (73.1%)፣ ተማሪዎች ስምምነታቸውን ገልጸዋል። ይህም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

በተጨማሪም በሁለተኛው ጥያቄ 16 (30.8%)፣ በአራተኛው ጥያቄ 25 (48.1%)፣ በስድስተኛው ጥያቄ 33 (63.4%)፣ ተማሪዎች አለመስማማታቸውን ገልጸዋል። ይህ ውጤት የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዳለ ያመለክታል።

### 4.1.5.2 ከድህረ ትምህርት በጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

**ሰንጠረዥ፡-9 ከድህረ ትምህርት በጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና**

| ተቁ | ጥያቄዎች | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ያለውን የሀሳብ ትስስር እለያለሁ። | 3 | 5.8 | 16 | 30.8 | 25 | 48.1 | 8 | 15.4 |
| 2 | የማነበውን ሁሉ ለመረዳት አልቸገርም። | 5 | 9.6 | 9 | 17.3 | 22 | 42.3 | 16 | 30.8 |
| 3 | የማነበው ጽሁፍ እንዲገባኝ የተለያዩ የማንበብ ብልሀቶችን እጠቀማለሁ፡ | 8 | 15.4 | 10 | 19.2 | 14 | 26.9 | 20 | 38.5 |
| 4 | የምንባቡን ሀሳብ አሳጥሬ መግለጽ እችላለሁ። | 6 | 11.5 | 9 | 17.3 | 18 | 34.6 | 19 | 36.5 |
| 5 | የማነበው ጽሁፍ እንዲገባኝ ጽሁፉ ለቀረበበት የጽሁፍ አወቃቀር ትኩረት እሰጣለሁ። | 9 | 17.3 | 8 | 15.4 | 24 | 46.2 | 11 | 21.2 |
| 6 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦችን ለመረዳት እቸገራለሁ። | 15 | 28.8 | 27 | 51.9 | 5 | 9.6 | 5 | 9.6 |
| 7 | አንብቦ ለመረዳት የጽሁፍ አወቃቀርን መረዳት አስፈላጊ መሆኑን አውቃለሁ ። | 7 | 13.5 | 4 | 7.7 | 12 | 23.1 | 29 | 55.8 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | የማነበው ጽሁፍ የተደራጀበትን የጽሁፍ አወቃቀር መለየት እችላለሁ። | 4 | 7.7 | 7 | 13.5 | 15 | 28.8 | 26 | 50.0 |
| 9 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ የማገኛቸውን ፍንጭ ሰጪ ቃላትና ሀረጋት የምንባቡን መልእክት ለመረዳት ያግዙኛል። | 6 | 11.5 | 4 | 7.7 | 14 | 26.9 | 28 | 53.8 |
| 10 | እንብቦ ለመረዳት የጽሁፉን አወቃቀር ማወቅ ጠቀሜታ አለው ብዬ አላስብም። | 21 | 40.4 | 4 | 7.7 | 8 | 15.4 | 19 | 36.5 |

ከሰንጠረዥ 9 እንደተመለከተው በጥያቄ አንድ ላይ ለቀረበው ጥያቄ የስምምነት ምላሽ የሰጡት 33 (63.5%)፣ ጥያቄ ሶስት 34 (65.4%)፣ ጥያቄ አምስት 35 (67.4%)፣ ጥያቄ ሰባት 41 (78.8%)፣ ጥያቄ ስምንት 41 (78.8%)፣ ጥያቄ ዘጠኝ 42 (80.7%)፣ እንደሆኑ ተገልጿል። ይህም ያልተስማሙት ተማሪዎች አነስተኛ ቁጥር እንደያዙ ያመላክታል። በሌላ በኩል በተራ ቁጥር አስር ለቀረበው ጥያቄ ስምምነታቸውን የገለጹት 27 (51.9%) ናቸው። ይህም ከላይ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ከሰጡት መልስ ጋር የሚስማማ ነው።

ጥያቄ ሁለት 38 (73.1%)፣ በጥያቄ አራት 37 (71.1%)፣ ተማሪዎች ስምምነታቸውን ሲገልጹ፣ በጥያቄ ስድስት የስምምነት ምላሽ የሰጡት 10 (19.2%) ብቻ ነበሩ። ይህም የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ መሻሻል እንዳሳየ ያመላክታል።

በአጠቃላይ ከሰንጠረዥ 8 እና 9 መመልከት እንደተቻለው በቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቁ በተራ ቁጥር 3 ላይ ለቀረበው ጥያቄ መጠይቁን ከሞሉት 52 ተማሪዎች መካከል 22 (42.3%) ስምምነታቸውን ሲገልጹ በድህረ ትምህርት መጠይቁ መስማማታቸውን የገለጹት ተማሪዎች ቁጥር 34 (65.4%) ናቸው። ይህም የተማሪዎች አንብቦ የመረዳትን ብልሀት የመጠቀም ችሎታ በድህረ ትምህርት መጠይቁ የተሻለ መሆኑን ያሳያል።

በቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቁ በተራ ቁጥር 8 ቀረበው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ ወደ አሉታ ያዘነበለ ነው። ምክንያቱም 31 (59.7%) አለመስማማታቸውን ሲገልጹ በድህረ ትምህርት መጠይቁ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 41 (78.8%) ስምምነታቸውን ገልጸዋል። በሌላ በኩል በተራ ቁጥር 9 አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 42 (80.7%) ስምምነታቸውን የገለጹት በድህረ ትምህርት መጠይቁ ነው። ይህም የጽሁፍ አወቃቀሩን ለመለየት ፍንጭ ሰጭ ቃላት እንደሚያግዙ ያሳያል።

በቅድመ ትምህርት መጠይቁ ለተራ ቁጥር ሰባት የተሰጠው ምላሽ 24 (46.2%) በድህረ ትምህርት መጠይቁ 41 (78.8%) ስምምነታቸውን ገልጸዋል። በሌላ በኩል በተራ ቁጥር 10 በቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቁ 14 (25.9%) በድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቁ 25 (48.1%) የሚሆኑ መላሾች አለመስማማታቸው በተራ ቁጥር ዘጠኝ ከሰጡት ምላሽጋር የሚስማማ ነው። ይህም አንብቦ ለመረዳት የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል።

በተራ ቁጥር አራት በቅድመ ትምህርት መጠይቁ ተማሪዎች የሰጡት የስምምነት ምላሽ 27 (51.9%) ሲሆን በድህረ ትምህርት መጠይቁ ደግሞ 37 (71.1%) ስምምነት መልስ ሰጥተዋል። ለተራ ቁጥር ስድስት በቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቁ መስማማታቸውን የገለጹት 19 (36.5%) በድህረ ትምህርት መጠይቁ 10 (19.2%) ናቸው።ይህም ከጥያቄ አራት መልስ ጋር ይስማማል። ምክንያቱም በቅድመ ትምህርት መጠይቁ የአንድን ጽሁፍ ዋና እና ዝርዝር ሀሳብ ለመረዳት ሲቸገሩ የነበሩ ተማሪዎች በድህረ ትምህርት መጠይቁ መሻሻል እንዳሳዩ ከሰጡት ምላሽ መገንዘብ ይቻላል።

በአጠቃላይ በቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቁ የተሰጠው የተማሪዎች ምላሽ በአብዛኛው አለመስማማትን የሚያሳይ ነው። የድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቁ ምላሽ ግን መስማማት ላይ ያዘነበለ ነበረ። ይህም የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት የተማሪዎችን የጽሁፍ አወቃቀር ግንዛቤ ያሻሻለ መሆኑን ያሳያል።በተጨማሪም በተለያየ የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጁ ምንባቦችን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማዳበር በኩል ሚና እንዳላቸው ጥናቱ አሳይቷል።

### 4.1.5.3 የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ በዳግም ልኬታ ናሙና ቲ- ቴስት

**ሰንጠረዥ፡- 10 የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ በዳግም ልኬታ ናሙና ቲ- ቴስት**

| የጥያቄ ዓይነት | የጥያቄ ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የነፃነት ደረጃ | የቲ-ዋጋ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ | 10 | 3.36 | 0.50718 | 9 | 1.738 | 0.001 |
| ድህረ ትምህርት | | 3.7 | 0.33731 | | | |

| የጽሁፍ መጠይቅ | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|

*P<0.05

የድህረ ፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (3.7) ከቅድመ ፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (3.36) የሚበልጥ ይመስላል። መደበኛ ልይይትንም በተመለከተ የቅድመ ጽሁፍ መጠይቅ መደበኛ ልይይት ከድህረ ጽሁፍ መጠይቅ መደበኛ ልይይት ያነሰ መሆኑን ከሰንጠረዥ 8 መገንዘብ ይቻላል። በሰንጠረዥ 8 የተመለከተውን በቅድመ ጽሁፍ መጠይቅና በድህረ ጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት መካከል ያለውን ልዩነት በስታትስቲክስ ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት (Repeated sample t-test) ተግባራዊ ሆኗል። በ9 የነፃነት ደረጃ (ቲ= 1.731 የፒ-ዋጋ (0.001) ከመቁረጫው ነጥብ (0.05) አንሶ በመገኘቱ በሁለቱ አማካዩች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን መረዳት ይቻላል። ይህ የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት የተማሪዎችን የጽሁፍ አወቃቀር ግንዛቤ እንደሚያጎለብት ያሳያል።

በአጠቃላይ ሲታይ የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያመለክተው የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ጉልህ ሚና አለው። በቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (26.27) በድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (33.25) መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት (p<0.05) ታይቷል። በተጨማሪም የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት የተማሪዎችን የጽሁፍ አወቃቀር ችሎታ ማሻሻሉን በትንተናው የተገኘው ውጤት አመላክቷል። በዚህም የቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (3.36) የድህረ ጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (3.7) መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት (p<0.05) መሆኑን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል ።

## 4.2 የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ትኩረት የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለውን ፋይዳ መመርመር ነው። ዝርዝር ዓላማዎቹም (1) የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ለውጥ ያመጣ እንደሆነ መመርመር (2) የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት የተማሪዎችን የጽሁፍ አወቃቀር ችሎታ ማሻሻሉን መፈተሽ የሚሉ ናቸው። የእነዚህን ዓላማዎች እውንነት ለማረጋገጥም በፈተና እና በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስና በገላጭ ዘዴ ተተንትነዋል።

በውጤት ትንተናው ሂደት በቅድሚያ የታየው ከቅድመ ትምህርት እና ከድህረ ትምህርት ፈተና የተገኘው መረጃ ነው። ከመረጃዎቹ የተገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ በመጀመሪያ የታየው የጥናቱ አላማ የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ለውጥ ያመጣ እንደሆነ መመርመር የሚለው ነው። በሰንጠረዥ 4 እንደተመለከተው የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (26.27) በልጦ የተገኘው የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (33.25) በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት ($p<0.05$) ሆኖ በመገኘቱ የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያሻሻለ መሆኑን አመላክቷል። በተዛማጅ ጽሁፉ 2.2 እንደተገለጸው ይህ ውጤት Meyer, Brandt and Bluth (1980)፣ Armbuster, Andessen and Ostertage (1987)፣ Piyonukool (2001) ጥናት ውጤት ጋር ይደጋገፋል።

በጥናቱ ውጤት መሰረት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ መሻሻል የታየው በ 2.4 እንደተገለጸው አንብቦ መረዳት በጽሁፍ ውስጥ የቀረቡ ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦችን መገንዘብን፣ የድርጊቶችን ቅደም ተከተል፣ አውዳዊ ፍቾዎችን መገንዘብን፣ የምክንያትና ውጤት ትስስርን መግለጽንና የመሳሰሉትን ያካትታል። ለዚህም በምክንያትና ውጤት፣ በገለጻ የጽሁፍ አወቃቀር ለማስተማሪያነት የቀረቡ ጽሁፎች የቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ ለመስጠት፣ ዋና እና ዝርዝር ሀሳብን ለመለየት አመቺ በመሆናቸው፣ ምክንያትና ውጤትን እንዲለዩ በማስቻላቸው የተለያዩ ምስል ከሳች ነገሮችን ለማውጣት ግልጽ በመሆናቸው ለዚህ ውጤት አብቅቷቸዋል ለማለት ያስችላል።

በተዛማጅ ጽሁፉ 2.4.3 የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በአንብቦ መረዳት ፈተና በሚያስመዘግቡት ውጤት ማወቅ እንደሚቻል በተለያዩ ምሁራን ተጠቅሷል። በሰንጠረዥ 7 የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያሳየው በቅድመ ትምህርት ፈተናው የተገኘው የተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት (0%) በጣም ዝቅተኛ ውጤት (67.31%) ነው። በድህረ ትምህርት ፈተናው የተገኘው ከፍተኛ ውጤት (3.85%) ሲሆን ዝቅተኛ ውጤት ደግሞ (19.23%) መሆኑ ተገጿል። በቅድመ ትምህርት ፈተናው ምንም ከፍተኛ ውጤት ያልተመዘገበ መሆኑን ሲያሳይ በርካታ ተማሪዎችም በጣም ዝቅተኛ ውጤት አስመዝግበዋል። ይህም በ2.3.1 እንደተገለጸው ብዙ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችግር እንዳለባቸው ያሳያል። የድህረ ትምህርት ፈተና ዝቅተኛ ውጤት ከቅድመ ትምህርት ፈተና ዝቅተኛ ውጤት ያነሰ ነው። ይህም በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ መሻሻል የታየው በ2.2 እንደተገለጸው

የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማሻሻል ለተማሪዎች ስለ የጽሁፍ አወቃቀር ግንዛቤ በመፈጠሩ ነው ። ይህም የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት ክሂሉን የማጎልበት ሚና እንዳለው ያሳያል።

ከጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች አንፃር በውጤት ትንተናው ሌላው ትኩረት የተደረገበት ጉዳይ የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት የተማሪዎችን የጽሁፍ አወቃቀር ችሎታ ማሻሻሉን የሚመለከት ነው። በሰንጠረዥ 8 እና 9 እንደሚታየው ከቅደመ ጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (3.36) በልጦ የተገኘው የድህረ ጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (3.7) በስታቲስቲክስ ጉልህ ልዩነት ($p<0.05$) እንዳለው ታይቷል። በመሆኑም በተዛማጅ ጽሁፉ በ2.3.1 ላይ የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት በተማሪዎች የጽሁፍ አወቃቀር ግንዛቤ ላይ ለውጥ ማምጣቱን ተገልጿል። ይህም የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት የጽሁፍ አወቃቀር አይነቶችን ለመለየት ያስችላል የሚል እንድምታ አለው። በ2.3.2 እንደተብራራው ተማሪዎች የጽሁፍ አዋቀርን ትምህርት ሲተገብሩ ጸሀፊው መረጃውን ለማደራጀት የተጠቀመበትን የጽሁፍ አወቃቀር እንዲለዩ ውይይት ማድረግ፣ ፍንጭ ሰጭ ቃላትንና ሀረጋትን በማስተዋወቅ፣ የጽሁፍ አወቃቀሩን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ መልመጃዎችን በማቅረብ ትምህርቱ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል። ለዚህም ለማስተማሪያነት የቀረቡ ጽሁፎች ፍንጭ ሰጭ ቃላትን የያዙና ተማሪዎች እንዲሳተፉ እድል የሰጡ በመሆኑ ነው፤ የሚል ማደማደሚያ ይኖረዋል። ይህ ውጤት በ2.3.1 Rapheel and Kirshner (1985) Garner and Gillingham (1987) ጥናት ውጤት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል።

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ውጤት የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት የአንብቦ መረዳት ችሎታን የማጎልበት፣ እንዲሁም ጽሁፉ የተደራጀበትን የጽሁፍ አወቃቀር የመገንዘብ፣ የመለየት ፋይዳ አለው የሚል አንድምታ ይኖረዋል። ይህም የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት የበለጠ ሆኖ በስታትስቲክስ ሲታይ ቲ= (7.009) ዋጋ (0.000) ከመቁረጫው ነጥብ (0.05) አንሶ በመገኘቱ በሁለቱ አማካዩች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አንድ አስረጂ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪ የድህረ ጽሁፍ መጠይቅ ከቅድመ ጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት የፒ-ዋጋ (0.001) ከመቁረጫው ነጥብ (0.05) አንሶ በመገኘቱ በሁለቱ አማካዩች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩ ተጨማሪ አስረጅ ሊሆን ይችላል። በአጠቃላይ አንብቦ መረዳትን ለማጎልበት የጽሁፍ አወቃቀር መገንዘብ በተመለከተ የነገሮችን ምክንያትና ውጤት መለየት፣ ፍንጭ ሰጪ ቃላትን መለየት፣ ምስል ከሳች የሆኑ ነገሮችን ማውጣት በምክንያትና ውጤት፣ በገለጻ የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጁ ጽሁፎችን በማስተማር

ጽሁፉ የተደራጀበትን የጽሁፍ አወቃቀር አይነት በመለየት የጽሁፍ አወቃቀሩን የተከተሉ ጥያቄዎች በማዘጋጀት ክሂሉን ማጎልበት ይቻላል።

# ምእራፍ አምስት

## ማጠቃለያና አስተያየት

### 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና መመርመር ነው። ዝርዝር ዓላማዎቹም የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ለውጥ ያመጣ እንደሆነ መመርመር፣ የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት የተማሪዎችን የጽሁፍ አወቃቀር ችሎታ ማሻሻሉን መፈተሽ የሚሉ ናቸው። እነዚህን አላማዎች ከግብ ለማድረስ ከፈተናና ከጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በገላጭና በድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ ተተንትነዋል።

በተሰበሰበው መረጃ መሰረት በመጀመሪያ ደረጃ የታየው የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ለውጥ ያመጣ እንደሆነ መመርመር የሚል ነበር። በፈተና አማካይነት የተሰበሰበውን መረጃ መሰረት በማድረግ የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ የማጎልበት ሚና እንዳለው ለማረጋገጥ መረጃዎች በዳግም ልኬታ ቲ-ቴስት ተተንትነዋል። በዚህም በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል በስታትስቲክስ ($P<0.05$) ጉልህ ልዩነት በመታየቱ የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ የማጎልበት ሚና እንዳለው በጥናቱ ተረጋግጧል።

በሁለተኛ ደረጃ የተፈተሸው የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት የተማሪዎችን የጽሁፍ አወቃቀር ችሎታ ማሻሻሉን መፈተሽ የሚል ነው። በቅድመና ድህረ የጽሁፍ መጠይቅ አማካዮች መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ($P< 0.05$) ልዩነት ታይቷል። በዚህም የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት በተማሪዎች በጽሁፍ አወቃቀር ችሎታ ላይ ለውጥ እንዳመጣ ለመረዳት ተችሏል።

በአጠቃላይ የጥናቱ ውጤት የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማጎልበትና የጽሁፍ አወቃቀር ችሎታ ለማሳደግ ለተማሪዎች የሚቀርቡት ጽሁፎች በአንባቢው አእምሮ ውስጥ ምስል የሚከስቱ፣ ምክንያትና ውጤትን የሚያሳዩ፣ በተለያየ የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጁ ቢሆን የተሻለ ውጤት ሊገኝ እንደሚችል አመላክቷል። የአንብቦ መረዳት ትምህርትም የጽሁፍ አወቃቀርን መሰረት አድርጎ ቢቀርብ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንደሚጎለብት ውጤቱ ይጠቁማል።

የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት አንብቦ መረዳትን በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና ምን እንደሆነ የጥናቱን ውጤት ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ መድረስ ተችሏል።

1. የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጎልበት የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር አስፈላጊ ነው። ይህም የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ይጠቁማል።
2. በተለያዩ የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጁ ጽሁፎችን ማስተማር የጽሁፍ አወቃቀር አይነቶችን ለመለየትና ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ያላቸውን ችሎታ ለማዳበር ይረዳል።

## 5.2 አስተያየት

ተማሪዎች ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ያላቸውን ችሎታ ለማሳደግና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማጎልበት ከጥናቱ ውጤት በመነሳት የሚከተሉት አስተያየቶች ተጠቁመዋል።

1 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ የማጎልበት ሚና እንዳለውና የጽሁፍ አወቃቀር አይነቶችን ለመለየት ጠቃሚ መሆኑን ተገንዝበው ጽሁፉ ለተደራጀበት የጽሁፍ አወቃቀር ትኩረት ቢሰጡ፣

2 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በንባብ ትምህርት ወቅት በተለያየ የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጁ ምንባቦችን በማቅረብ የተማሪዎችን የጽሁፍ አወቃቀር እውቀት ለማሻሻል ቢጥሩ፣

3 የመጽሀፍ አዘጋጆች በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚካተቱ ምንባቦች የጽሁፍ አወቃቀር አይነቶችን መሰረት ያደረጉ፣ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችም የጽሁፍ አወቃቀር እውቀትን የሚያጎለብቱ እንዲሆኑ አድርገው ቢያዘጋጁ፣

4 ይህ ጥናት ከጽሁፍ አወቃቀር አይነቶች ውስጥ በምክንያትና ውጤት እና በገለጻ ላይ ያተኮረ ነው። ከክሂሎች ደግሞ አንብቦ መረዳትን የተመለከተ በመሆኑ በቀጣይ ሌሎች አጥኚዎች ሁሉንም ጽሁፍ አወቃቀር አይነቶችና ክሂሎች ያካተተ ጥናት ቢካሄድ የተሻለ ግንዛቤ ሊገኝ ይችላል።

# ዋቢ ጽሁፎች

ሀዲስ አለማየሁ። (2000)። *ፍቅር እስከ መቃብር።* አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

ማረው አለሙ። (1998)። *የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ።* አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ማስተዋል ውበቱ። (1989)። "የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች አማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ። በአዲስ አበባ በሚገኙ በአራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ። (ያልታተመ)።

ሰለሞን ደኑ። (2003)። "ልቦለድን በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ። በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የዘጠነኛና አስረኛ ክፍሎች መማሪያ መጽሐፍት ማሳያነት።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ። (ያልታተመ)።

ትምህርት ሚኒስቴ። (1997)። *አማርኛ፣ የተማሪው መማሪያ መፅሀፍ 9ኛ ክፍል ።* አዲስ አበባ፣ በት.መ.ማ.ማ.ድ የታተመ ትምህርት ሚኒስቴር።

ትምህርት ሚኒስተር። (1992)። *አማርኛ፤ የተማሪው መማሪያ መፅሀፍ 10ኛ ክፍል*። አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

ትምህርት ሚኒስቴር። (2004)። *አማርኛ፤ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ 11ኛ ክፍል*። አዲስ አበባ፣ የአል-ጉሬርአሳታሚ ድርጅት።

ነብዩ ጋሹ። (2005)።" በግጥም አማካኝነት በአማርኛ የአንብቦ መረዳትና የጽህፈት ችሎታን ማዳበር ፤በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ። (ያልታተመ።)

አለም እሸቱ። (1991)። "ንባብን አንብቦ መረዳትና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አቀራረብ። " አዲሰ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የቋንቋ ጥናት ተቋም ለ10ኛ አመት የቋንቋ ጥናት ስንፖዚየም የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ።

አማረ ተሾመ። (2003)። "በስነ ጽሁፍ የንባብ ክሂልን የማስተማር አተገባበር (በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን በተመረጡ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአስረኛ ክፍል

ናሙናነት።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ። (ያልታተመ።)

አፀደ ውድነህ። (2000)። *ሩብ ጉዳይ*። አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም አሳታሚ ድርጅት።

የኔሰው ደሴ። (1990)።" በኦሮሞኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪ ሞዴልን በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋጽኦ።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ። (ያልታተመ)።

ያለው እንዳወቀ። (1998)። *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር*። አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚ ድርጅት።

ይስምአከ ወርቁ። (2009)። *ዩቶፒ*። አዲስ አበባ፣ ዴርቶጋዳ ማተሚያ ድርጅት።

ዳኛቸው ወርቁ። (1988)። *የጽሁፍ ጥበብ መመሪያ* ። አዲስ አበባ፤ ሜጋ ህትመት ኢንተርፕራይዝ።

ጌትነት አዲስ። (2001)። "በረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር ያለው ውጤታማነት በተመረጠ አንድ የምስራቅ ጎጃም ዞን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍሎች ላይ የተካሄደ ጥናት።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ። (ያልታተመ)።

Akhondi, M., Malayeri, F.A and samod, A.A. (2011). How To Teach Expository Text structure to faclitate Reading comprehension. *The Reading Teacher,* Vol. *64.* No. . Pp. *368-372*

Armbuster,B.B.. Andersen, H.T..and Ostertage,J. (1987). "Does text structure /Summarization/ Instruction Facilitate Learning from Expository Text*?" Reading Research Quarterly,* Vol. 22, No. Pp. 331-3464

Dole, J.A., Duffy, G.G., Roehler, L.R., and pearson. (1991). Moving from the old to the New: Research on Reading compherension In struction. "*Review of Educational research".* Vol. *61* No. *2* . Pp. *239-264*.

Dymock, S. (2005). "Comprehension strategy Instruction: Teaching narrative Text structure Awareness*" The reading teacher, Vol. 61. No. 2 .Pp.161- 167*

Frey.N and Lapp.D.(2008) "Shared Readings Modeling Comprehension Vocabulary. Text Structures and Text Features for Older Readers" *The Reading Teacher .*Vol. 61, No.7. Pp 548-550

Garner, Ruth and Gillingham, mark, G. (1987). *Students knowledge of Text structure*: *Journal of literacy Research* from http://jir.sagepub. com.10/02/2013

Gentry, J.L. (2006). "Comparison of the Effects of training in Expository text structure through Annotation text marking and training invocabulary development on reading comprehension of students Going in to fourth Grade Graduate school" /Theises and Dissertations from http://scholar commons.Usfl edu/'etd/253/.15/2/2013.

Grabe,B. (2002).Using Discourse patterns to improve Reading comprehension .

Australian *Review of Applied Linguistics*, {series S.No. 16} pp.9-17

Grellet, J. (1981). *Developing Reading Skills*. Cambridge: Cambridge: University

Press.

Harmer,J. (1991). *The practice of English language Teaching.* London: New York long man.

Hess Krin. (2006) Teaching and Assessing Understanding of Text *s*tructure Aroos Grades*. National Center and For The Improvement of Educational* Assessment.

Heydari, M., and Mustapha, G. (2009).Text structure Awarness. Another look at reading compherension strategy in L2 classes: *The journal ofInternational management studies,* Vol. 4. No. 2. Pp. 254-258

Hughes, D.M. (1997) A Longitudinal Study of the Development of Writing in 4-7 Year Old Children. University of Reading, PhD thesis. Unpublished

Lauterbach.SL. and Bender. W. N.(1995). Cognitive strategy instruction for reading comprehe nsion's success for high school fresh man. Retrieved 26/08/2012 from *http://www. Jstor.org/stable/40364744*

Madson.H.S. (1983). *Teaching in testing*. New York Oxford University press.

Mann, W.c and Thompson, S.A. (1987). "Rhetorical structure Theory: To wards a functional Theory of Text organization," *Text* 8(3) 243-281.

Meyer, B,J.F. Brandt. D. M. and Bluth G. J. (1980) "Use of top level Structure in text Key for Reading Comprehension of Ninth Grade Students. " *Reading Research Ouarterly.*Vol. 16.No. 1. Pp. 72-103

Meyer. B.J.F. and Ray. M.N. (2011*).* Structure Strategy Interventions. Increasing Reading Comprehension of Expository Text*. International Electronic Journal of Elementary Education.* Vol. 4. No. 1 Pp. 127-152.

Nikki,Y. (2010) "Understanding Reading Comprehension: Multiple and Focused Strategy Intervention for Struggling Adolescent Readers."AThesis in partial Fulfillment of the Requirement for the Degree of Master of Education. (unpublished).

Nuttal, C.(1982).*Teaching Reading skill in a foreign language.L*ondon:.Heinemann Educational Book

------- (1996).*Teaching reading skills in a foreign language*: oxford. Macmillan Publishers limited.

----------(2000).*Teaching reading skills in a foreign language*:/2nd ed./ Heinemann Educational Books.Orcutt,Kristi.n.d.Reading and writing consultant .from http://www.text.mapping.org/overview.htm/

Padua.Jennifer F.M (2008) *Effective Instructonal Strategies Series.* Text Structure: Cause and Effect.*Pacfic Resources* for Education and Learning. Honolul, Hawai'i. USA ‹

Piyonukool, S. (2001). "Effects of Teaching reading through Discussion of text structure." Dissertation prepared for the Degree of Doctor Ofphilosophy University of north Texas. (unpublished).

Rapheel, T.E., and kirshner, B.M. (1985). "The Effect of Instruction in compare /contrast text structure on sixth Grade students Reading compherension *and* writing products"*:* Michigan state university. (unpublished).

Shanehan.T.(2006). *The National Reading Panal. Report Practical Advice for Teachers.* Learning Point Associates. Chicago.

Sharp. A. (2002) "Chinese L1 School Children Reading in English. The Effects of Rhetorical Patterns". *Reading in a Foreign Language*. Volume 14.NO. 2. Pp 1-20

Smith, F. (1985). *Reading*. Great Britain Cambridge university press

Tinajero, J.V. (n.d). *comprehension Instruction for English language learners*: The university of Texas. www.hampton.brown.com. 11/8/2013

Yochum, N.(1991). Childern's learning from informational *Text*: The relation ship between prior knowledge and text structure: *Journals of Reading Behavior,* .Volume 23 .NO. 1. Pp 87-108

## አባሪ ሀ

## ቅድመ ትምህርት ፈተና

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

### የሂዩማኒቲስ፤ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

### የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍናፎክሎር ክፍለ ትምህርት

### ድኅረምረቃ መርሀግብር

ኮድ-----

ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ ቅድመ ትምህርት ፈተና (ከ60%)

የፈተናው መነሻ ሰዓት 2፡30ስዓት

ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ1፡30ስዓት

**አጠቃላይ መመሪያ**

*ውድተማሪዎች፤ የዚህ ፈተና ዋና አላማ የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር አንብቦ የመረዳትን ችሎታ በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ለመፈተሽ ለታሰበው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፤ ጥያቄዎቹ በምንባቡ መሠረት የሚመለሱ ሆነው ሶስት ንዑሳን ክፍሎች አሏቸው።*

የመጀመሪያው ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ለቃላት የሚስማማቸውን ፍቺ መምረጥ፣ ሁለተኛው ሀረጋት የሚያስተላልፉትን ሀሳብ መጻፍ፣ ሶስተኛው የምንባቡን ዋና ዋና ሀሳቦች ለይቶ ማውጣትና የምንባቡን መልዕክት መፃፍ ናቸው። ሁለት ምንባቦች ቀርበዋል። እያንዳንዱን ምንባብ መሰረት ያደረጉ አስራ አንድ አስራ አንድ በድምሩ 22 ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል። ስለዚህ የቀረቡትን ምንባቦች መሰረት በማድረግ ለጥያቄዎች መልስ ነው የምትለውን/ይውን ለመልስ መስጫ በተሰጠው ቦታ አስቀምጥ/ጭ

**ምንባብ 1**

ራሴን አስተዋልኩት። ልብሴ ከላየ ላይ ነትቧል። ሰውነቴ በቆሻሻ ጠቋቁሯል። ጥፍሮቼም የአውሬን ጥፍር ያክል አድገዋል። እግሮቼ ተሰነጣጥቀውና አባብጠው መድፍ አክለዋል። ከስሬ የሚፈሰው ወራጅ ውሃ ቁልቁል ስመለከተው ፀጉሬ ወደላይ መቆሙን ነገረኝ። በጎንና በጎን የፀጉሬን ስር ለማየት ያደረኩት ጥረት ግን አልተሳካም። በተባይ መወረሬን የሚነግሩኝ የጣቶቼ ጥፍሮች ናቸው። ስሩን ይገፎ ስመዝ በቅጫምና ቅማል ተሞልተው ይመጣሉ። ድንጋይ ላይ እያስቀመጥኩ እነሱን ስገድል ስንት ጊዜ አጥፍቼ ይሆን? እኔም እንደ እናቴ እንጃኔ ነው መልሴ።

መስኮቱን በቀስታ ከፍቼ አሻግሬ እመለከታለሁ። ያ ቆሻሻ ወንዝ ይታየኛል። ድልድዩ ስር ከቅራቅንቦ መሃል ደግሞ ወላጅ እናቴ ጉብ ብላ ትተክዛለች። ትለፈልፋለች። ነፍስ ካወቅኩ ጀምሮ እናቴ ልጆች እንጃኔ እያሉ የሚጠሯት ያበደች ሴት መሆኗን ከሰፈር ሰዎች ተረድቻለሁ። አሳዳጊዎቼ እስኪተኙ ጠብቄ የመስኮቱን መጋረጃ እገልጣለሁ። አንዴ ፀጉሯ የተንጨበረረውን ወይም ልብሷ የነተበውን እናቴን እይታዬ ውስጥ ካስገባሁ እስኪነጋ ወይም የአሳዳጊዎቼን ኮቴ እስክሰማ ድረስ አይኔን ከሷ መንቀል አልተቻለኝም። ዝም ብዬ ሳያት ታሳዝነኛለች። እሷ ተኮራምታ እኔ ብርድ ልብስ መልበስ አያሻኝም። የእሷን ያክል እንዲበርደኝ ሺ ጊዜ ፈልጌአለሁ ግን አልሆነም። እኔ ባሸበረቀ ቤት እርሷ ደግሞ ኡራዔል ካለው ድልድይ ስር።

ራስምታት ሆነኝ ግን መበረዱም ርሃቧም አደለም። አንድ ቀን ከትካዜዋ ነቃ አለችና "ልጆቼን፣ ልጆቼን አምጡ" እያለች ደጋግማ ጮኸች። አንጀቴ ተላወሰ። አለሁ እያየሁሽ እኮ ነው አልሁ በለሆሳስ። እናቴ በየጊዜው እንደምትወልድና ዋ ለነፍሴ ያለ አልያም ልጅ የሌለው ሰው እንደሚሰርቃት ሰምቻለሁ። የአንዱን ልጇን አድራሻ እንደምንም ፈልጌ አገኘሁት።

እሱን ለማግኘት ከሳምንት በላይ ተመላልሻለሁ አንድ ቀን ግን ተሳካልኝ። ኮምፒዩተሩ ላይ አፍጥጦ የነበረው ወጣት በወንበሩ ተሽከርክሮ ወደኔ ዞረና በመገረም አስተዋለኝ። እኔ ደግሞ ገፅታውን በአንዴ ሸመደድኩት። ጠይም ዓይኖቹ ጎላ ጎላ ያሉ፣ አፍንጫው ጎራዳ ከንፈሮቹ አበጥ አበጥ ያሉ ናቸው። ከእናቴ መልክ ጋር ለማዛመድ ሞከርኩ። ከፀጉሩ መከርደድና ከጠይምነቱ በቀር አይመስላትም።

ምን ልርዳሽ እሙ? እስኪ ለማንኛውም ቁጭ በዪ አለና ወንበሩን በእጁም በአገጩም አመለከተኝ። ረጋ ብዬ ወንበሩ ላይ ተቀመጥኩና አቀረቀርኩ። ዝምታ ሆነ። ህይወት እባላለሁ ልበለው። ፈራሁ። በተራው እያጠናኝ መሰለኝ። ፀጉሬ እንደሱ ከርዳዳ ነው፣ ቀለሜ ጠይም፣ ዓይኖቼ ትናንሽ፣ አፍንጫዬ ረዥም ከናፍሮቼ ስስ ናቸው። ከማን ጋ አዛምዶኝ ይሆን ብዬ አሰብኩ። እንደወንድሜ ሁሉ ፀጉሬና ቀለሜ ብቻ ነው የእሷ ሌላውስ እኔ እንጃ። እኔን ጨምሮ ማንም የእናቴን ስም የሚያውቅ የለም። የሚያያት ሁሉ እንጃኔ እያለ ነው የሚጠራት። (አፀደ ውድነህ፣ ሩብ ጉዳይ 2000)

**ትእዛዝ አንድ፡ -** ምንባቡን መሠረት በማድረግ ለቃላት የሚስማማቸውን ፍቺ በመምረጥ የመልሱን ፊደል ብቻ በተሰጠው ክፍት ቦታ ፃፍ/ፊ። (6%)

----------- 1. ነትቧል ሀ/ ጠቁሯል ለ/ቆሽሿል ሐ/አልቋል መ/ተቀዷል

----------- 2. መድፍ ሀ/ ሰፊ ለ/ ወፍራም ሐ/ ረጅም መ/ አስፈሪ

----------- 3. ዘነጋ ሀ/ እራሱን ሳተ ለ/ ብዙ ቆየ

ሐ/ በእድሜው ገፋ መ/ አላስታውስ አለ

**ትእዛዝ ሁለት** በምንባቡ መሰረት ሀረጋቱ የሚያስተላልፉትን ሀሳብ ግለጽ/ጪ (6%)

1. አንጀቴ ተላወሰ

---------------------------------------------------------------------------

-----------------------

2. እያጠናኝ መሰለኝ.

------------------------------------------------------------------------

----------------------

**ትዕዛዝ ሦስት ፡-** በምንባቡ መሠረት የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልስ በተሰጠው ክፍት ቦታ በጽሁፍ ግለጽ/ጭ። (18%)

1. ህይወት የአካሉን መጎሳቆል ያችው የት ሆና ነው? እንዴት አወቅህ/ሽ?

-------------------------------------------------------------------------------

---------

2. በምንባቡ ውስጥ በምእናብህ /ሽ የተከሰቱት ነገሮች ምን ምን ናቸው?

-------------------------------------------------------------------------------

---------

3. የህይወትን አካላዊ ገለጻ የሚያሳየው የትኛው አንቀጽ ነው?

-------------------------------------------------------------------------------

----------

4. የህይወትን እናት አካላዊ ገጽታ አጠር አድርገህ/ሽ ግለጽ/ጪ

-------------------------------------------------------------------------------

-------

5. የምንባቡን ዋና ሀሳብ በሶስት አረፍተ ነገር ጻፍ /ጻፊ

-------------------------------------------------------------------------------

-----

6. ምንባቡ የተደራጀው በየትኛው የጽሁፍ አወቃቀር ነው?

-------------------------------------------------------------------------------

----------

## ምንባብ 2

ከሰላሳ አመት በፊት የነበረው የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር 19 ሚሊዮን ነበር። የህዝቡ ቁጥር ከ1950ዎቹ ጀምሮ በ1.9 በመቶ አደገ፤ በ1980 መገባደጃ ወደ 3.0 በመቶ፣ ከ1986 ወዲህ ደግሞ ወደ 3.2 በመቶ አሻቀበ። በዚህ አካሄድ ከ20 ዓመታት በኋላም የዚህን እጥፍ ሊሆን እንደሚችል ባለሙያዎች ይናገራሉ።

የተገለጹት ቀደምት ቆጠራዎችና የመጪዎቹ ዓመታት ስሌቶች እንደሚጠቁሙት ከአስራ አምስት አመታት በታች ያሉት ታዳጊ ህፃናት በቁጥር የህዝቡን 50 በመቶ ይሆናሉ። እርግጥ ነው ህዝብ በህዝብነቱ ሀገር ያፈራውን ሁሉ ተካፍሎ ሊኖር ይገባዋል። ይህ ደግሞ ተግባራዊ እንዲሆን በሁሉም ዘርፍ ምጣኔ ያስፈልጋል፤ ዳሩ ይህን ምጣኔ የሚፈታተነው የመዋለድ

ፍጥነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄዱ ነው። ይህ ሽቅብ ጉዞ በአጠቃላዩ የእድገት ሂደት ላይ ጥገኝነትን ፈጥሮ ልማት እንዳይፋጠን በማድረግ የአገር ሀብትን ያቆረቁዛል።

የህዝብ ቁጥር መጨመር የፍጆታ ፍላጎትን ስለሚያሳድግ በቋሚ ልማት ላይ ሊውል የሚገባው መዋዕለ ንዋይ በአስተማማኝ ልማት ላይ ሳይሆን በምግብ አቅርቦት፣ በመጠለያ፣ በጤና፣ በትምህርት፣ ወዘተ ላይ ይውላል፤ ይህ ድግሞ ምርታማነትን በመቀነስ የህዝቡ ዓመታዊ የነብስ ወከፍ ገቢ እንዲያሽቆለቁል ያደርገዋል።

የህዝብ ቁጥር ጨምሮ ስራ ሊፈጥር የሚችል ኢኮኖሚ ሲታጣ፣ ሊያመርት የሚችልን ግን ደግሞ የሚያመርተውን ያጣ ህዝብ ያበዛል። ይህም የስራ አጡን ቁጥር ያበረክታል። ከዚሁ ጎን ለጎን ትምህርትን ስንመለከት ለመማር ፈላጊውን በየጊዜው ለማመን በሚያዳግት ሁኔታ እየበዛ ይመጣል። የተማሪዎች ቁጥር መጨመር ለትምህርት የሚወጣውን ገንዘብ ያበረክተዋል፤ የትምህርትንም ጥራት ያዘቅጠዋል። (የ9ኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መፅሀፍ፤ በሚያመች መልኩ ተስተካክሎ የተወሰደ1997)

**ትዕዛዝ አንድ፡ - ምንባቡን መሠረት በማድረግ ለቃላት የሚስማማቸውን ፍቺ በመምረጥ የመልሱን ፊደል ብቻ በተሰጠው ክፍት ቦታ ፃፍ/ፊ። (6%)**

-----------1. አሻቀበ ሀ/ ጨመረ ለ/ አዳገተ ሐ/ አንጋጠጠ መ/ አቀና

----------- 2. ነፍስ ወከፍ ሀ/ ጆምላ ለ/ ቡድን ሐ/ ጥንድ መ/ አንዳንድ

----------- 3. ሀገር ያፈራውን ሀ/ ከሀገር ያልወጣውን ለ/ ከሀገር የተወለደውን ሐ/ ከሀገር የተገኘውን መ/ ከሀገር የተሾመውን

**ትእዛዝ ሁለት** በምንባቡ መሰረት ሀረጋቱ የሚያስተላልፉትን ሀሳብ ግለጽ/ጪ(6%)

1. የሚያመርተው ያጣ ------------------------------------------------------------------------

2. የመጪው ዓመታት ስሌቶች -----------------------------------------------------------------

**ትእዛዝ ሶስት** በምንባቡ መሠረት የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልስ በተሰጠው ክፍት ቦታ በጽሁፍ ግለጽ/ጭ። (18%)

1. ልማት እንዳይፋጠን ያደረገው ምክንያት ምንድን ነው?--------------------------------
-----------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------

2. በህዝቡ ላይ የፍጆታ ፍላጎት መጨመር የሚያስከትለው ውጤት ምንድን ነው?----------
-----------------------------------------------------------------------------------
--------------------------

3. የአራተኛውን አንቀጽ ዝርዝር ሀሳብ ጻፍ/ጽፊ? -------------------------------------
-------------------------------------------------------------- --------------------
--------------------------------------

4. በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ ምክንያትና ውጤቶች በቅደምተከተል ግለጹ?------------------
-----------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------ምንባቡ የተደራጀው በየትኛው የጽሁፍ አወቃቀር ነው?--
-----------------------------------------------------------------------------------
-------------------------------------------------------------

6. የህዝብ ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ እንዲሄድ ያደረገው ምንድን ነው?-------------------
-----------------------------------------------------------------------------------
-------------------------------

# አባሪ ለ

# ድህረ ትምህርት ፈተና

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# የሂዩማኒቲስ፤ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
# የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት
# ድኅረምረቃ መርሀግብር

**ኮድ-----**

ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ ድህረ ትምህርት ፈተና (ከ60%)።

የፈተናው መነሻ ሰዓት 2፡30ሰዓት

ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ1፡30ሰዓት

**አጠቃላይ መመሪያ**

ውድተማሪዎች፤ የዚህ ፈተና ዋና አላማ የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር አንብቦ የመረዳትን ችሎታ በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ለመፈተሽ ለታሰበው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፤ ጥያቄዎቹ በምንባቡ መሠረት የሚመለሱ ሆነው ሶስት ንዑሳን ክፍሎች አሏቸው። የመጀመሪያው ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ለቃላት የሚስማማቸውን ፍቺ መምረጥ፣ ሁለተኛው ሀረጋት የሚያስተላልፉትን ሀሳብ መጻፍ፣ ሶስተኛው የምንባቡን ዋና ዋና ሀሳቦች ለይቶ ማውጣትና የምንባቡን መልዕክት መፃፍ ናቸው። ሁለት ምንባቦች ቀርበዋል። እያንዳንዱን ምንባብ መሰረት ያደረጉ አስራ አንድ አስራ አንድ በድምሩ 22 ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል። ስለዚህ የቀረቡትን ምንባቦች መሰረት በማድረግ ለጥያቄዎች መልስ ነው የምትለውን/ይውን ለመልስ መስጫ በተሰጠው ቦታ አስቀምጥ/ጭ

**ምንባብ አንድ**

ባለፉት አስርተ አመታት ከተሞች በፍጥነት እያደጉ እንደመጡ በርካታ ጥናቶች ይጠቁማሉ።በአሁኑ ወቅት 50% የሚሆነው የምድራችን ህዝብ በከተሞች ውስጥ ይኖራል። ለዚህም በርካታ ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል። አንደኛው በአስራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን በከተሞች ላይ የታየው የኢንዱስትሪ እድገት በርካታ የስራ እድሎችን ፈጥሯል። እነዚህ የስራ እድሎችም በሚያቀርቡት ያልተጨበጠ የወደፊት የተሻለ ቁሳዊ ህይወት በርካታውን የገጠር አካባቢ ነዋሪ ህዝብ ቀልብ መግዛት ቻሉ። በሁለተኛ ደረጃም በፋብሪካዎች አካባቢ የፋብሪካው ባለቤቶችና ሰራተኞች ልጆች ለማስተማር ሲባል በርካታ ትምህርት ቤቶች መገንባት ጀመሩ። ስለሆነም ልጆቻችን የተሻለ የትምህርት እድል ያገኛሉ በማለት በገጠር አካባቢ የሚኖሩ ወላጆች ቀያቸውን በመተው ወደ ከተማ እንዲፈልሱ ምክንያት

ሆነ።በመጨረሻም የከተሞች እድገት በጨመረ ቁጥር ሰዎች የትርፍ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉባቸውና የሚዝናኑባቸው ቦታዎች እንደ የስፖርት ስታዲዮም፣ ሲኒማ ቤት፣ ሙዚየምና ሌሎች የቅንጦት ቦታዎች መገንባት ጀመሩ። ለበርካታ ሰዎች እነዚህን የመሳሰሉ ፋሲሊቲዎች የከተማ ህይወትን ከገጠር ህይወት የተሻለ እንደሚያደርጉ ይሰማቸዋል። ስለሆነም ሰዎች የገጠር ኑሮአቸውን እርግፍ አድርገው በመተው ወደ ከተማ ይሰደዳሉ።

**ትዕዛዝ አንድ፤ - ምንባቡን መሠረት በማድረግ ለቃላት የሚስማማቸውን ፍቺ በመምረጥ የመልሱን ፊደል ብቻ በተሰጠው ክፍት ቦታ ፃፍ/ፊ።** (6%)

----------- 1. ፈለሰ ሀ. ተነቀለ ለ. ተፈነቀለ ሐ. ተመነገለ መ. ተሰደደ

---------2 ሙዚየም ሀ. ሲኒማዎችና ቲያትሮች የሚዘጋጁበት ቤት

ለ. ሲኒማዎችና ቲያትሮች ተዘጋጅተው ለህዝብ እይታ የሚቀርቡበት ቤት

ሐ. የተለያዩ ቅርሶች ተሰብስበው የሚቀመጡበትና ለህዝብ እይታ የሚቀርቡበት ቤት

መ. የተለያዩ ስፖርታዊ ትርኢቶች ለውድድር የሚቀርቡበት ቤት

----------- 3. ቅንጦት ሀ. ጩኸት ለ. ምቾት ሐ. ቀልድ መ. ጨዋታ

**ትእዛዝ ሁለት** በምንባቡ መሰረት ሀረጋቱ የሚያስተላልፉትን ሀሳብ ግለጽ/ጪ (6%)

1. ቀያቸውን በመተው
   ----------------------------------------------------------------------------
   --------
2. የተሻለ የትምህርት እድል ያገኛሉ
   --------------------------------------------------------------

**ትዕዛዝ ሦስት ፡- በምንባቡ መሠረት የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልስ በተሰጠው ክፍት ቦታ በጽሁፍ ግለጽ/ጭ።** (18%)

1. ምንባቡ የተደራጀው በየትኛው የጽሁፍ አወቃቀር ነው? ----------------------------
   ----------------------------------------------------------------------------
   ------------------------------

2. ትምህርት ቤቶችን መገንባት ያስፈለገው ለምንድን ነው ? መገንባቱስ ምን አስከተለ? -
----------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------
------------------------------------

3. ግማሽ የሚሆነውን የምድራችን ህዝብ በከተሞች እንዲኖር ያደረጉትን ምክንያቶች ዘርዝር/ሪ? ---------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------
-----------------------------------------------

4. የምንባቡን ዋና ሀሳብ በሁለት አረፍተ ነገር ጻፍ/ፊ --------------------------------
----------------------------------------------------------------------------
---------------------------------

5. በተለያየ ምክንያት የገጠር ኑሮቸውን በመተው ወደ ከተማ መሰደዳቸው ያስከተለው ውጤት ምንድን ነው? -------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------

6. ህዝቡ በከተማ ውስጥ እንዲኖር ካደረጉት ምክንያቶች በቀዳሚነት በተጠቀሰው ውስጥ ያለውን የምክንያትና የውጤት ትስስር ግለጽ/ጪ ---------------------------------
----------------------------------------------------------------------------
--------------------------

**ምንባብ ሁለት**

ጌራ የራስ ዳሸን ተራራ ጫፍ ላይ ቆሞ ቁልቁል ሲመለከት፣ ከባህር ጠለል በላይ 4620 ሜትር ከፍታ ላይ ሳይሆን ከሰባቱ ሰማያት ባንዱ ላይ የቆመ መሰለው። ከታች ባሉት ታናናሽ ተራሮች ጫፍ ላይ ጉም ይውጀመጀማል። አንዱ የጉም ሰራዊት አልፎ ሌላኛው ሲተካ በአውሮፕላን የሚጓዝ እንጂ ምድር ላይ የቆመ አልመስልህ አለው። በስተምስራቅ የምትወጣዋን ፍም የመሰለች ፀሀይ ተመለከተና በሰዎ ልጆችና በፈጣሪ መካከል የቆመ መልአክ የሆነ ያህል ተሰማው። በህልም አለሙ ብቻ ነው እንዲህ አይነት ተራራ ላይ ወጥቶ የሚያውቀው። ራሱን ሲያዞረው ለመቀመጥ ሞከረ። የተነደፈ ጥጥ በሚመስለው በዚህ በረዶ ላይ ቢቀመጥ ለዘላለም ተጣብቆ እንደሚቀር ተገነዘበ።

ጉሙ ካለፈ በኋላ ቁልቁል ሲመለከት በጎበዝ አናጢ የተጠረቡ የሚመስሉ የተራራ ሰንሰለቶች እጅ ለእጅ ተያይዘው ታላቁን ራስ ዳሽን ተራራን የሚማጸኑ ምእመናን ይመስላሉ። ከሩቅ የጭላዳ ዝንጀሮ መንጋ ይደባደባል። ገመሬው ገልመጥ ገልመጥ ሲል ደረቱ ላይ ያለው ቀይ ፊኛ በፍርድ አደባባይ የተሰየመ ዳኛ ያስመስለዋል። በወዲህ በኩል ደግሞ ቀንዱን ያርበኛ ጎራዴ ያስመሰለ ዋሊያ አይቤክስ ታላቅ ቋጥኝ ላይ ቆሞ በጸጥታ አለምን የሚታዘብ ፈላስፋ ይመስላል። ከወዲያ ማዶ ባሉት የተራሮች ሰንሰለት ስንጥቅ መሀል ቀጭን ረጂም ፏፏቴ እንደሻሽ ብን ብን እያለች ትወርዳለች።

የጌራ አእምሮ በሆኑ መናፍስት ሲወረር ተሰማው አንዳች የፍስሐ ህብረ ዝማሬ የሚያሰሙ የሚመስሉ መናፍስት። በሚያዬው የተፈጥሮ ድንግል ውበት አእምሮውን መቆጣጠር ስላቃተው ጮኸ። እንደገና ለዘላለም ዝም የሚል ይመስል ፀጥ ብሎ አይኖቹን ጨፈነ።

የሚያውደውን የሰሜን ተራራ ልዩ መአዛ ሲምግ ወደ ውስጡ ሲስብ አፍንጫውን የሚሰነጥቅ ብርድ ጦር የገባበት ያህል አስጓራው። የሰሜን ተራራ ጮቄ ብርድ እንደ እንጦርጦስ ጦር ሲወጋው የለበሰውን ከጥጥ የተሰራ ጥቁር ካፖርት እጅጌ ከአፍንጫው ላይ በመጫን ለመቋቋም ሞከረና ቁልቁል ተመለከተ። ሜሮዳና ሳዶፍ እየዳሁና ተራራውን እየቧጠጡ በመምጣት ላይ ነበሩ። (ይስምአከ፣ ዩቶድ 2009)

ትዕዛዝ አንድ፡ - ምንባቡን መሠረት በማድረግ ለቃላት የሚስማማቸውን ፍቺ በመምረጥ የመልሱን ፊደል ብቻ በተሰጠው ክፍት ቦታ ፃፍ/ፊ። (6%)

-----------1.አወደ ሀ.ጥሩ ጥሩ ሽተተ ለ. ቤተክርስቲያኑን አጠነ ሐ..የቤተክርስቲያኑን ዙሪያ ዞረ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

----------- 2. ቋጥኝ ሀ. ከተራራ ላይ የተደረበ ተራራ ለ. መሬት ላይ ጉብ ብሎ የሚገኝ ትልቅ ድንጋይ ሐ. በተቆለለ አፈር ለይ የበቀለ እፅዋት መ. በውሃ አካባቢ የሚገኝ ድንጋይ

----------- 3. ጮቄ ሀ. ቢነግሩት የማይገባው ለ. ገንዘብ የማይሰጥ ሐ. ጨቀጨቅ ያለበት መሬት መ. ከያዘ የማይለቅ

ትእዛዝ ሁለት በምንባቡ መሰረት ሀረጋቱ የሚያስተላልፉትን ሀሳብ ግለጽ/ጪ. (6%)

1. በህልም አለም

-------------------------------------------------------------------------

--------

2. ድንግል ውበት

-------------------------------------------------------------------------

-------------

**ትዕዛዝ ሶስት ፡- በምንባቡ መሠረት የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልስ በተሰጠው ክፍት ቦታ በጽሁፍ ግለጽ/ጭ።** (18%)

1. ምንባቡ የተደራጀው በየትኛው የጽሁፍ አወቃቀር ነው? ----------------------------
-------------------------------------------------------------------------
------------------------------
2. በምንባቡ ውስጥ በምናብህ /ሽ የተከሰቱት ነገሮች ምን ምን ናቸው? ----------------
-------------------------------------------------------------------------
-------------------------
3. የአራተኛውን አንቀጽ ዝርዝር ሀሳብ ጻፍ/ጽፊ? ---------------------------------
-------------------------------------------------------------------------
---------------------------------
4. በሰሜን ተራራ ምን ምን ነገሮች ይገኛሉ?---------------------------------------
-------------------------------------------------------------------------
--------------------------------
5. የጌራን አእምሮ የወረሩት መናፍስት ምን አይነት ስሜት ፈጠሩበት? ----------------
-------------------------------------------------------------------------
-------------------------
6. ጌራ ምድር ላይ የቆመ ያልመሰለው ለምንድን ነው? ------------------------------
-------------------------------------------------------------------------
------------------------------

# አባሪ ሐ

## ማስተማሪያ ጽሁፍ

### በማጐልበት ረገድ ያለው ሚና በሚል ርዕስ ለሚካሄደው ጥናት መረጃ እንዲያስገኝ ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ

የትምህርቱ ክፍለ ጊዜያት ማካሰኞና ሐሙስ /በቀን ለ1 ስአት/

የመማሪያ ክፍል የማጠናከሪያ ትምህርት መስጫ

ጠቅላላ የትምህርት ሰዓት፡ 10፡00 ሰዓት

**ትምህርት ሁለት**

የትምህርቱ ርዕሶች፡-

ምንባቡን አንብበው ምስል መፍጠር፣ የምንባቡን ሃሳብ በማስታወስ ለጥያቄዎች መልስ መስጠት፣ ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦችን መለየት

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ 2፡00

የትምህርቱ አላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

በምንባቡ ውስጥ በአእምሮ ውስጥ ምስል የሚፈጥሩ ነገሮችን ይገልጻሉ።

የምንባቡን ሃሳብ በማስታወስ ለጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ።

ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦችን ይለያሉ።

**ምንባብ**

ከስር መሬቱ እንደረመጥ ያቃጥላል። ከላይ የአየሩ ወበቅ እንደእሳት ላንቃ ይጋረፋል። ሳር ቅጠሉ ደርቋል። ዛፎቹ ከሰል መስለዋል። ወፎቹ ተሰደዋል። ጎድናቸው አንድ ሁለት ተብሎ የሚቆጠር በሞትና በህይወት መካከል የሚንገዳገዱ ጣዕረ ሞት የሚመስሉ የቤት እንስሳት

መጠለያና መኖ አጥተው በየሜዳው በቁም ያንቀላፋሉ። እረኞቻቸውም እንደነርሱ አጥንታቸው ወጥቶ ፊታቸው ገርጥቶ ሆዳቸው እንደከበሮ ተነፍቶ አይናቸው ጎድጉዶ እግሮቻቸው ቀጥነው የያዙትን ዘንግ መስለው- እንደሌላው ጊዜ ዋሽንት አይጫወቱም ከወንዝ ወዲያ ማዶ ሆነው የእረኛ ዘፈን አይቀባበሉም። እንደወንዞቹ ደርቀው፣ እንደከብቶቹ ከስተው በዝምታ የተፈጥሮን ልግስና ይጠባበቃሉ- በትግስት። በተስፋ የእግዚአብሄርን ምሕረትና ቸርነት ይጠባበቃሉ- ሌላ የሚደርስላቸው ኀይል አያውቁምና! ጉልበት ያለው ጎረምሳ እንደወፎች በጊዜ አገር ለቅቆ ወጥቷል- የዕለት ጉርስ ፍለጋ። አዝማሪዎች መሲንቆዎቻቸውን በባህር እጣን ማሚሸትና መቃኘት ከተዉ ቆይተዋል። ዘፈን የለም። ብር የለም። ጠጅ የለም።ከጠላ ቤቱ ደጅ የቆርቆሮ ጣሳ አይታይም። ከጠጅ ቤት ደጅ አንቡላ አይሸትም። ንቦች አይታዩም። እነሱም ካገር ወጥተዋል። በዛፉ ላይ የተሰቀሉት የማር ቀፎዎች ጭር ብለዋል። በእድሜ የገፉ ገበሬዎች በየደጃቸው እግርና እጃቸውን አጣምረው ከተፈጥሮ ጋር ያሸልባሉ- ያንቀላፋሉ-ያዛጋሉ። የሞት ፍርዱን የሚጠባበቅ እስረኛ ይመስላሉ። ተፈጥሮ ፊቷን አዙራለች። (ማረው፣ *የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ 1996)*

**ትእዛዝ አንድ**

የሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ ውስጥ የሚያስተላልፉትን ሀሳብ በቃል ግለጽ/ጪ

1. ጣእረ ሞት
2. በሞትና በህይውት መካከል
3. መኖ
4. አንቡላ

**ትእዛዝ ሁለት**

በምንባቡ ሀሳብ ላይ በመመስረት ቀጥሎ ለቀረቡት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ።

1. ወፎቹ ለምን የተሰደዱ ይመስልሀል/ሻል? ምክንያቱን? ግለጽ/ጭ
2. የከብቶቹንና የእረኞቹ ምስስል ግለጽ/ጪ
3. እረኞቹ የሚጠባበቁት ነገር ምንድን ነው? ለምንስ ይጠባበቁታል?
4. በጊዜ አገር ለቆ ወጥቶል ሲል ምን ማለቱ ነው?
5. በምንባቡ ከተገለጹት ውስጥ በበለጠ ምስል የፈጠሩብህን /ሽን ነገሮች በዝርዝር ጻፍ/ጻፊ/
6. በአካባቢያችሁ ስለምታዩት አንድ ነገር ምስል እንዲፈጥር በማድረግ አንድ አንቀጽ

ጻፍ/ጻፊ

7. ጸሀፊው በምንባቡ ሊያስተላለፍ የፈለገውን ዋና መልእክት በአንድ አረፍተ ነገር ጻፍ/ጻፊ
8. በአካባቢያችሁ በምንባቡ የቀረበውን ገለጻ የሚያሳይ ነገር አይታችሁ ታውቃላችሁ?
9. የሞት ፍርድ የሚጠባበቅ እስረኛ ምን ይመስላል? ምስል እንዲፈጥር አድርጋችሁ ግለጹት
10. ምንባቡ በውስጣችሁ ምን ፈጠረባችሁ? ጭንቀት፣ ሀዘን፣ ፍርሀት ወይስ ሌላ ምክንያቱን አብራሩ?

የትምህርት መረጃ፡- በገለጻ የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጀ ጽሁፍ

ግምገማ፡- የክፍል ስራ በመስጠት

የቃል ጥያቄ በማቅረብ

**ትምህርት ሶስት**

ለእያንዳንዱ ውጤት ምክንያት የሆኑትን ነገሮች መለየት፣ ቀጥሎየሚመጣን ሀሳብ መገመት፣ የምንባቡን ሀሳብ መሠረት በማድረግ ለቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ መስጠት፣ የምንባቡን ዋና ሃሳብ ለይቶ ማውጣት፣

- ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ 2፡00

የትምህርቱ አላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት ውጤቶች ምክንያታቸውን ይገልጻሉ።

ከቀደመው ሀሳብ ቀጥሎ የሚመጣውን ይገምታሉ፡

ለቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ።

የምንባቡን ዋና ሃሳብ ለይተው ያወጣሉ።

1.ስኬታማ መሆን የሚቻለው እንዴት ነው?

2.የስኬታማ ሰዎችን የህይወት ተሞክሮ የመመልከት ጥቅሙ ምንድን ነው?

**ምንባብ**

የአማርኛ ክፍል ቴክኒሺያኑና ፕሮግራም አስፈፃሚው የዜና ስዓት በመድረሱ ዝግጅት ማድረግ ጀምረዋል። ለወትሮው ቢሆን የዕለቱ ዜና አንባቢ ተገኝቶ ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ ነበረበት፤ ዛሬ ግን የዕለቱ ዜና አንባቢ በማይታወቅ ሁኔታ አልመጣም።

ይህ ክስተት ዕለት በዕለት የሚያጋጥም ባለመሆኑ ፣ ለክፉም ለደጉም ተብሎ ተጠባባቂ አልተመደበም። አገር ምድሩ ዜና እየጠበቀ እያለ ፤በአንባቢ መጥፋት ምክንያት ዜናው ሳይቀርብ ቢቀር አስገራሚ ነው የሚሆነው። ወይንም ደግሞ ፣ <<አድማጮቻችን ዛሬ ምሽት አንባቢው ባልታወቀ ምክንያት ስለቀረ ዜና ባለማቅረባችን ይቅርታ እንጠይቃለን!>> ሊባል? አይደረግም። አጋጣሚ ሆኖ፣አማርኛ ዜና ክፍል ዳይሬክተሩ ከዚህ ቀደም ስቱዲዮ ገብተው ዜና አንብበው አያውቁም። እና ጭንቀቱ ከወዲያ ወዲህ ያንጎራድዳቸው፤ ያቁነጠንጣቸው ጀመር።

በዚህ ጭንቀት ውስጥ እያሉ ነበር ፣ ድንገት ያ-ማታ ማታ ስቱዲዮ እየገባ ስለአስራሩ እንዲመለከት የተፈቀደለትን ተማሪ ልጅ ያዩት። ዜናው ደግሞ የግድ ለአየር መብቃት አለበት። ዳይሬክተሩ ጭንቀታቸው እየበረታ ሄደ።

<<ይሄ ልጅ ይግባ? ወይስ ራሴ ልግባ?>> ግራ ተጋብተው ሲንቆራጠጡ፣ ስዓቱ ደረሰ ፤አሁን ያላቸውን አማራጭ መጠቀም ካልቻሉ ችግር ሊሆን ነው። ወደ ልጁ ተጠጉና ሲፈሩ ሲቸሩ፣<ትሞክር!>> አሉት። ይሄ ጥያቄ ጋዜጠኛ ለመሆን ነፍሱ ለተራበች ልጅ ሀሴት ውስጥ የሚከት ነበር። ልጁ ምንም የጥርጣሬ ፊት ሳያሳይና ጨርሶ የፍርሃት ስሜት ዝር ሳይልበት በድፍረት ፣<አነባለሁ!>> አለ ። ዳይሬክተሩ <<ይኸ ልጅ ወይ እንደጀማሪ ፊደል ሲቆጥር ቢገኝ፣አሊያም እንደኮልታፋ ምላሱ ቢተሳሰር ፣ወይ ደግሞ የስቱዲዮው ቤት መቅደሳዊ ድባብ አስፈርቶት ከጥቂት መንተባተብ በኋላ ንባቡን ቢያቋርጥ፣ አልፎ ተርፎም ወረቀት እያንኮሻኮሸ ምን እየቀደዱ ነው ቢያስብል፣ የማን ያለህ ሊባል ነው?>> እያሉ አወጡ አወረዱ ። ነገር ግን ፣ከዚያ በላይ የማሰቢያ ጊዜ ሊኖራቸው አይችልም ።

| |
|---|
| ልጁ ካሳየው ድፍረትና ልበሙሉነት በመነሳት ዜናውን እንዲያቀርብ ቢፈቀድለት ፣ያለ ስህተት የሚያነበው ይመስልሃል/ሻል/? |

በጭንቀት ነፍሳቸው እንደተጠበበች በግዳቸው ዜናውን ሰጡትና አብረውት ወደስቱዲዮ ገቡ። ያ ልጅ ግን ስቱዲዮ ውስጥ መግባት ያለበት አንባቢ ብቻ እንደሆነ ሰሞኑን ካየው ነገር ተገንዝቧል። ስለዚህም ዳይሬክተሩ ያበላሸዋል ብለው እንደፈሩ ገብቶታል። ዳይሬክተሩ ፊት

ላይ ፍርሃት እየጎላ ሲታይ፣ ንባቡ እንዲቀጥል የሚጠቁመው የስቱዲዮ ቀይ መብራት ብልጭ አለ። ዜናው መነበብ ጀመረ።

< እንደምን አመሻችሁ? ዜና እናሰማለን ፤ ዜናውን የማቀርብላችሁ ታደሰ ሙሉነህ ነኝ ...>> ቅልጥ አድርጎ አነበበው ፣ያለ ስህተት ተወጣው። (ከ11ኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መፅሀፍ፤ በሚያመች መልኩ ተስተካክሎ የተወሰደ 2004)

**ትእዛዝ አንድ**

በምንባቡ ሀሳብ መሠረት ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በጥንድ በመሆን ከተወያያችሁ በኃላ የተስማማችሁበትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ

1. ዳይሬክተሩ እንደፈሩት ሳይሆን ልጁ ዜናውን በትክክል ማቅረብ የቻለው ለምን ይመስላችኋል?
2. ከዚህ ምንባብ ምን ተገነዘባችሁ?
3. **ምንባቡ በየትኛው የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጀ ነው?**

**ትእዛዝ ሁለት**

ከሚከተሉት ጥያቄዎች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቻቸውን ስጥ/ጪ።

1. በአንቀጽ ሶስት <<ጋዜጠኛ ለመሆን ነፍሱ ለተራበች ልጅ <u>ሀሴት</u> ውስጥ የሚከት ነበር።>> በሚለው ዓረፍተ ነገር ለተሰመረበት ቃል ፍቺ

   ሀ. ሀዘን ለ. ፍርሃት ሐ. ደስታ መ. ጭንቀት

2. በአንቀጽ አራት <<የስቱዲዮው <u>ቤተ መቅደሳዊ ድባብ</u> አስፈርቶት ከጥቂት መንተባተብ በኋላ ንባቡን ቢያቋርጥ...>>

   ሀ. የቤተመቅደሱ ጸጥታ አስደስቶት ሐ. የቤተመቅደሱ ዝምታ አስጨንቆት

   ለ. የቤተመቅደሱ ንጽህና አስገርሞት መ. የቤተመቅደሱ መጨለም አስፈርቶት

3. በመጨረሻው አንቀጽ <<እንደምን አመሻችሁ ? ዜና እናሰማለን፤ዜናውን የማቀርብላችሁ ታደሰ ሙሉነህ ነኝ...>> <u>ቅልጥ አድርጎ አነበበው</u>።

   ሀ. ቀልጠፍ ብሎ አነበበው ሐ. በደንብ አነበበው

   ለ. ተንተባትቦ አነበበው መ. አልፎ አልፎ አነበበው

**ትእዛዝ ሶስት**

በ <<ሀ>> ረድፍ ለተሰጡት ውጤቶች በ <<ለ>> ረድፍ ካሉት ምክንያታቸው ጋር አዛምድ/ጂ/

<u>ሀ</u> <u>ለ</u>

1. የአማርኛ ክፍል ቴክኒሽያንና ፕሮግራም ሀ. ዜና አንባቢው ባልታወቀ ምክንያት ሳይመጣ ቀረ። አስፈፃሚው ዝግጅት ማድረግ።
2. ለክፉም ለደጉም ተብሎ ሌላ ዜና አንባቢ ለ. የዜና ማንበቢያ ስዓት ደረሰ ። አለማዘጋጀት።
3. ዜናው ሳይቀርብ ሊቀር ነው። ሐ. ከዚህ ቀደም ዜና አንባቢው ቀርቶ አያውቅም
4. ዳይሬክተሩ ራሳቸው ዜናውን ለማንበብ መ. በልጁ አለመተማመን አልደፈሩም ።
5. ዳይሬክተሩ ከልጁ ጋር ወደስቲዲዮው ገቡ። ሠ. ስቲዲዮው ውስጥ ዜና አንብበው አያውቁም

ረ. ልጁ ሀሴት ውስጥ ገባ።

የትምህርት መረጃ፡- በምክንያትና ውጤት የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጀ ጽሁፍ

ግምገማ፡- የክፍል ስራ በመስጠት በማረም

በጥንድ ተወያይተው እንዲናገሩ በማድረግ

**ትምህርት አራት**

የትምህርቱ ርዕሶች፡-በገለጻ የተደራጀ የጽሁፍ አወቃቀርን መለየት፣ምስል ከሳች ቃላትን መለየት፣ የምንባቡን ሀሳብ መሠረት በማድረግ ለቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ መስጠት በምክንያትና ውጤት የተደራጀ የጽሁፍ አወቃቀርን መለየት

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ 2፡00

የትምህርቱ አላማ፡- በገለጻ የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጁ ምንባቦችን ይለያሉ።

ምስል ከሳች ቃላትን ያወጣሉ።

የምንባቡን ሀሳብ መሠረት በማድረግ ለቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ።

በምክንያትና ውጤት የተደራጀ የጽሁፍ አወቃቀርን ይለያሉ።

**ምንባብ 1**

ልክ በቀጠሮው ሰዓት በመድረሱ ደስ ብሎት ረጅም ቅልጥሙን አመሰገነ። በስንት ደጅ ጥናት ያገኘው ቀጠሮ ነበር።

«ቀጠሮ አለህ?» ብላ ጠየቀችው የቢሮው ፀሀፊዋ።

ሽቶዋ ያውዳል። ጡቶቿ ጠላት ላይ የተደገኑ ሮኬቶች ይመስላሉ። ጥቁር ሹራብ ለብሳለች የልብ ቅርፅ ያለው የአንገት ጌጣ ከጡቶቿ መሀል ተሸጉጦ ይታያል። ቶሎ ብሎ አይኑን ከጡቶቿ መሀል ነቀለ። ፈገግ አለች። ትኩስ የተቀቀለ በቆሎ እሸት የሚመስሉትን ጥርሶቹን አሳያትና «አወ ቀጠሮ አለኝ» አላት።

«ጠብቅ ይመጣሉ» አለችው፣የእጅ ቦርሳዋን እየከፈተች።

ረጃጅም እግሮቿ በጠረጴዛው ስር ይታያሉ። ቀይ ቀለም የተቀባው አውራ ጣቶቿ የሚያሾፉበት መሰለው። እንደገና አይን ለአይን ተጋጩ። ረጃጅም እጆቹን የሚያደርግበት ቦታ ጠፋው። ከት ብላ ሳቀች። ምን እንዳሳቃት አልገባውም፡፤ ጠይም ፊቱ አሸቦ መሰለ። ወዲያውኑ ቀጠሮ የሰጠው ባለስልጣን መጣ። ቁመናው አጭር ሆኖ ቦርጫም ነበር።

«ሌሎች ባለጉዳዮች ሳይመጡ ቶሎ ግባ» አለችው ፀሀፊዋ። የቢሮውን በር ቀስ ብሎ ከፍቶ ገባ። ሰውየው ቀደም ብሎ ከትልቁ ጠረጴዛ ኋላ ትልቅ ወንበር ላይ ተኮፍሷል። ያ ቅድም ሲገባ ያየው አጭር ሰው አሁን ግዙፍ መስሎ ታየው።

«ምን ኖሯል?» እንደ አንበሳ አጓራበት።

«ባለፈው ሳምንት ለዛሬ ቀጠሮ ሰጥተውኝ ነበር» አለው፣ እጆቹን ወደኋላ አድርጎ። ሳምንቱን ሙሉ ተስፋ የጣለበት ቀጠሮ ነበር።

«እኮ ጉዳይህ ምንድን ነው?»

«ስራ ፈልጌ ነበር።»

«ማን ነው የላከህ?»

«ማንም። እኔው ነኝ የመጣሁት።»

«የማን ልጅ ነህ?»

የማን ልጅ ነኝ ይበል መምሬ ሳህሌ፣ አምላካቸው ነፍሳቸውን ይማረውና፣ ማንም አልነበሩም። ማንም የማያውቃቸው ተራ ቄስ ነበሩ። ስራ ሊያስገኝ የሚችል የዘር ሀረግ ከየት አምጥቶ ይምዘዝ! ኢትዮጵያዊነት ብቻውን አይበቃም። ሳራ ፈላጊ ስራ ለማግኘት ያንድ የታወቀ ሰው ልጅ ዘር መሆን ያስፈልገዋል። ስራ ለማግኘት ከወረቀት ዲግሪ የተሸለ በመወለድ የሚገኝ የላቀ

ዲግሪ ኖሯል ለካ! ለዚህ አልታደለም። ምን ይበል (የ10ኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መፅሀፍ፤ በሚያመች መልኩ የተወሰደ1992)

**ትእዛዝ አንድ**

በምንባቡ ሀሳብ ላይ በመመስረት ቀጥሎ ለቀረቡት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች መልስ ስጡ

1 ረጃጅም እጆቹን የሚያገባበት ቦታ ጠፋው ሲል ምን ማለቱ ነው?

2. ሳምንቱን ሙሉ ተስፋ የጣለበት ቀጠሮ ነበር የሚለውን ሀሳብ አብራራ/ሪ

3. ባለ ታሪኩ የአባቱን ስም መናገር ያልፈለገው ለምን ይመስልሀል/ሻል?

**ትእዛዝ ሁለት**

ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሠረት አውዳዊ ፍቺ ስጥ/ጪ

1. በስንት ደጅ ጥናት ያገኘሁት ቀጠሮ ነበር።

2. ሽቶዋ ያውዳል።

3. ቶሎ ብሎ ከጡቶቿ ላይ አይኑን ነቀለ።

4. ጠይም ፊቱ አሸቦ መሰለ።

**ትእዛዝ ሶስት**

በምንባቡ ሀሳብ ላይ በመመስረት ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ስጥ/ጪ

1.በምንባቡ የሚገኙ ገጸ ባህሪያትን አካላዊ ገጽታ ምስል ከሳች በሆነ አቀራረብ ግለጽ/ጪ

**ምንባብ 2**

የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ ባትሪዎች የትም ሲጣሉ በአካባቢ ላይ ጉዳት ያስከትላሉ።ምክንያቱም እንዲወገዱ ካልተደረገ በጊዜ ብዛት ይሰነጠቃሉ። በውጤቱም በውስጣቸው የሚገኝ መርዛማ ንጥረ ነገር እየተንጠባጠበ በአካባቢው የሚገኝ ውሃ እና አፈር ይበክላል።ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ ባትሪዎች እንዲቃጠሉ ቢደረግ የአካባቢው አየር በመርዛማ ጭስ ይበከላል። ቃጠሎ አመድ ማትረፉ የተለመደ ክስተት ነው። ስለሆነም ባትሪዎች ተቃጥለው የሚገኘው አመድ መርዛማ ነገር ይገኝበታል። ከጊዜ ብዛትም ይህ መርዛማ ነገር የያዘ አመድ ከአፈር ጋር በማዋሃድ አካባቢውን ይበክላል።

ያረጁ የመኪና ባትሪዎችም በአግባቡ ካልተወገዱና ከተሰነጠቁ ጎጂዎች ናቸው። አንድ በየሰፈሩ ቆሻሻን የሚያስወግድ ሰው፣ ቆሻሻውን ለማስወገድ በሚሰበሰብበት ወቅት ያረጀ የመኪና ባትሪ

መንገድ ላይ ቢወድቅበትና ሳያስተውለው ቢቀር፣ በባትሪው ውስጥ የሚገኝ መርዛማ ነገር በህጻናትና ሌሎች ለማዳ የቤት እንሰሳት ጤንነት ላይ አደጋ ሊያስከትል ይችላል። ስለዚህም ያረጁና የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለቀ ባትሪዎች በተገቢው መንገድ በማስወገድ አካባቢን ከብክለትና ከሌላ ተመሳሳይ አደጋ መጠበቅ ይቻላል።

**ትእዛዝ አንድ**

ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሠረት አውዳዊ ፍቺ ስጥ/ጪ

1. አመድ ማትረፍ የተለመደ <u>ክስተት</u> ነው።
2. አካባቢን <u>ከብክለት</u> መጠበቅ ይቻላል።

**ትእዛዝ ሁለት**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልስ ስጥ/ጭ/

1. በአንቀጽአንድና በአንቀጽሁለት መካከል ያለውን የሀሳብ ትስስር ግለጹ
2. የምንባቡን ዋና ሀሳብ በአንድ አረፍተነገር ጻፍ
3. ባነበባችሁት ምንባብ ውስጥ የሚገኙ ምክንያትና ውጤት ዘርዝር/ሪ
4. የሁለቱ ምንባቦች ተመሳሳይነት ወይም ልዩነት በምክንያት በማስደገፍ ግለጽ/ጪ
5. የጽሁፍ አወቃቀሩን ለመለየት ፍንጭ የሰጡህ/ሽ የትኞቹ ናቸው?

የትምህርት መረጃ፡- በገለጻ እና በምክንያትና ውጤት የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጀ ጽሁፍ

ግምገማ፡- የክፍል ስራ በመስጠት

የቃል ጥያቄ በማቅረብ

**ትምህርት አምስት**

የትምህርቱ ርዕሶች፡-

በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ ምክንያትና ውጤት መለየት፣ የምንባቡን ሀሳብ መሠረት በማድረግ ለቀረቡት ቃላት ተስማሚ ፍቺ መስጠት፣ የምንባቡን ሃሳብ አሳጥሮ መፃፍ

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ 2፡00

የትምህርቱ አላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ ምክንያትና ውጤት ያወጣሉ።

የምንባቡን ሀሳብ መሠረት በማድረግ ለቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ።

የምንባቡን ሃሳብ አሳጥረው ይጽፋሉ።

**ቅድመ ንባብ ጥያቄ**

ልጆችን በአጓጉል ቦታ እንዲውሉ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው?

**ምንባብ 1**

ቤተሰብ ሲፈርስ፣ ልጆች ከእናት ወይ ከአባት ጋር እንዲኖሩ ወይም እንደቁሳቁስ በቁጥር ተለይተው ለእናትና ለአባት እኩል እኩል እንዲደርሱ ይደረገሰል። የየድርሻቸውን የተካፈሉም ሆኑ ሳይካፈሉ በአንዳቸው ሃላፊነት ብቻ እንዲያድጉ የሚስማሙ እናትና አባት አላማቸው የተመሳሰለ ነው፤ በጊዜያዊ መደለያ በማባበል የልጆቹን ፍቅር የየራሳቸው የብቻ አድርገው ለመኖር መታገል፣ በእናት ስር የሚተዳደሩ ከሆነ ወደአባት ዘንድ ለጉብኝት ሲሄዱ ከተገቢው በላይ መስተንግዶ ይቆያቸዋል። በአባት ስር የሚተዳደሩ ከሆነ እናት ዘንድ ሲሄዱ እንዲሁ የተለየ መስተንግዶ፣ አንዴ እናት ዘንድ አንዴ አባት ዘንድ፣ አባት ዘንድ እናት ዘንድ፣ እናት ዘንድ አባት ዘንድ፣ ልጆች የሚውሉበትንና የሚያመሹበትን ቦታ ሁኔታ መከታተል ያዳግታል። የሚደርጉትንና የተሰማሩበትን ተግባር ለማዎቅ ይቅርና የት ነበራችሁ ሲባሉ አባጋ ወይም እማየጋ፣ ምን ስታደርጉ ቆያችሁ ሲባሉ ከአባዬ ጋር ስጫወት፣ እማዬን ስራ ስረዳ- የማይሉት የማይፈጥሩት ምክንያት አይኖርም። ለቁጥጥር አመችነታቸው ይዳከማል፤ ቁጥጥር ይላላል። ከአጓጉል ጓደኞች ጋር መዋል በአጓጉል ቦታዎች መገኘት ይጀምራሉ። በሆነ ባልሆነው ምክንያት አንዴ ከአባት አንዴ ከእናት፣ ከዘመድ አዝማድ ገንዘብ እየተወሰደ፣ ፍላጎት እያደገ ይሄዳል፤ ገንዘብ እያጠረ፣ የህይወት ትርጉሙ እየጠፋ፣ መንፈስ እየተረበሸ፣ አይሰሩ ስራ እየተሰራ - ሞራላቸው እየላሸቀ። እንዲያም ብሎ ይባስ ሲል፣ ግዴለሽነትን፣ ሲጠናወት መዛዘንን፣ ሲረጋጋ ወመኔነትን፣ ሲለይለት ወፈፌነትን እያስከተለ… የቤሰብ መፍረስ፣ የመንፈስ መረበሽና የሞራል ውድቀትን፣ የወመኔነትና የወሮበላነትን፣ ግፋም ሲል የወንጀለኝነት መንስኤ ነው። (ዳኛቸው 1988)

**ትእዛዝ አንድ**

ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሠረት አውዳዊ ፍቺ የያዘውን ሆሄ ምረጥ/ጭ/ ።

1. እንደ <u>ቁሳቁስ</u> በቁጥር ተለይተው ሀ. ጌጣ ጌጥ ለ. የቤት እቃ ሐ. ጥሬ ገንዘብ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

2. ከአንጉል ጓደኛ ጋር መዋል ሀ. ያልተመጣጠነ ለ. ጥሩ ያልሆነ ሐ በመሀል የቀረ መ ያልተስተካከለ

3. እንዴውም ይባስ ብሎ ወፈፌነትን ያስከትላል ሀ. የአእምሮ በሽተኛ ያስከትላል ለ. የአእምሮ በሽተኛ ይሆናል ሐ. አልባሌ ቦታ ይውላል መ. ወዲያ ወዲህ ይላል

4. በአባት ስር የሚተዳደሩት እናት ዘንድ ሲሄዱ ሀ. አባታቸው የሚቆጣጠራቸው ለ. አባታቸው ጋር የሚኖሩ ሐ. አባታቸው የሚረዳቸው መ. አባታቸው የሚያዛቸው ትእዛዝ ሁለት

በምንባቡ ሀሳብ ላይ በመመስረት ቀጥሎ ለቀረቡት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ

1. በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የሚገኙ የምክንያትና ውጤት ትስስር ግለጽ/ጪ
2. ገንዘብ እያጠር አይሰሩ ስራ እየተሰራ ሲል ምን ማለቱ ነው
3. የቤተሰብ መፍረስ በልጆች ላይ የሚያስከትለው ውጤት ምንድን ነው
4. የምንባቡን ዋና ሀሳብ ግለጽ/ጪ

የትምህርት መረጃ፡- በምክንያትና ውጤት የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጀ ጽሁፍ

ግምገማ፡- የክፍል ስራ በመስጠ ማረም

የትምህርቱ ርዕሶች፡-

ምንባቡን አንብበው ምስል መፍጠር፣ የምንባቡን ሃሳብ በማስታወስ ለጥያቄዎች መልስ መስጠት፣ ለቃላት ተመሳሳይ ፍች መስጠት

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ 2፡00

የትምህርቱ አላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

ከምንባቡ በአእምሮ ውስጥ ምስል የሚፈጥሩ ነገሮችን ይገልጻሉ።

የምንባቡን ሃሳብ በማስታወስ ለጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ።

ለቃላት ተመሳሳይ ፍች ይሰጣሉ፡

1. በጸደይ ወቅት እጽዋት ምን ይመስላሉ?

## ምንባብ 2

ፍታውራሪ መሸሻ ግቢ በሚሉት ሰፊ ሜዳ ለድርቆሽ የሚያስጠብቁት ከሰርዶ፣ ካክርማ፣ ከጉዳይ፣ ከዋራት አንድ ላይ ተደባልቆ ያደገው ሳር ቀደም ብሎ የበቀለው አፍርቶ ዘግየት ብሎ የበቀለው ቢጫ ፣ሰማያዊ፣ነጭና ቀይ አበባ አብቦ ሰብለወንጌል ከተቀመጠችበት ዘቅዝቆ

ሲመለከቱት ያን ሰፊ ግቢ ለማስጌጥ ከዳር እስከዳር የተዘረጋ አምሮ የተሰራ ኸንጉርጉር ምንጣፍ ይመስል ነበር። ፀሐይ እየሞቀ በሄደ መጠን በዚያ ሰፊ ግቢ የተነጠፈው ሳርና በቤቶች አካባቢ የተተከሉ የፍሬ አትክልት አንድ ላይ ባየር ይነዙት የነበረ ገነታዊ መዓዛ ሽቱ በብዙው እንደተረፈረፈበት መዋኛ ከውስጡ መውጣት አያስመኝም ነበር። በወፍራምና በቀጭን አስማምተው እየዘመሩ ካበባ ወደአበባ ይዘዋወሩ የነበሩ ንቦችና አንድ ጊዜ በፍሬ ተክሎች ዙሪያ፣ ሌላ ጊዜ በሜዳው በተነጠፈው ያበባ ምንጣፍ ላይ በየጓዳቸው እየዞሩ ይጨፍሩ የነበሩ በፀደይ ብቻ የሚመጡ፣ ጌጠኛ ቢራቢሮዎች ሲታዩ ያ ከልምላሜና ከመአዛ፣ከውበትና ከለዛ ድርና ማግ የተሰራ ፀደይ ያ የክረምትን ቁርና የበጋን ሀሩር የማያሰማ ፀደይ፣ ባጭር ጊዜ የሚያልፍ መሆኑን በመረዳት ሳይልፍ እናጊጥበት፣ ሳያልፍ እንደሰትበት፣ሳያልፍ እንስራበት ብለው የሚጣድፉ ይመስሉ ነበር።

| |
|---|
| ከላይ ካነበብከው/ሽው/ አንቀጽ የተረዳህውን/ሽውን/ ዋና ዋና ነጥቦች ዘርዝር /ሪ? |

‹‹ወይ አንተ ግቢ! ምነው እንዲህ እንዳበብህ እንዲህ እንደተዋብህ የምትኖር ሆንህ! ምነው ይህ ውበትህ የበጋ ፀሐይ የማያደርቀው፣የክረምት ጭቃ የማያጨማልቀው በሆነ! ብቻ ይህ ውበትህ አሁን ያልፋል! ይህ አበባህ አሁን ይረግፋል! ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ እኒህ መዓዛህና ለዛህ ጠርቶዋቸው የሚጨፍሩት ቢራቢሮዎችና የሚዘምሩት ንቦች እዚህ አይኖሩም! ሌላ ያበባን የተዋበ ቦታ ፍለጋ ይሄዳሉ።›› አለች ሰብለወንጌል በዙሪያዋ የተዘረጋውን በአበባና በፍሬ ያጌጠ ግቢና በሱ የሚደሰቱትን ፍጥረት ዝም ብላ ስታስተውል ቆይታ። ወዲያው በሰው ህይወትና ከጊዜ ጋር በሚለዋወጡ ቁቃያዎች መሀከል ያለው ተመሳሳይነት ታሰባት። (ከሀዲስ አለማየሁ 11ኛ እትም 2000)

**ትእዛዝ አንድ ፡- ከሚከተሉት ጥያቄዎች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሃረጋት አውዳዊ ፍቻቸውን ስጥ/ጭ።**

1. ይነዙት   ሀ. ያሸቱት   ለ. ያለብሱት   ሐ. ያራምዱት   መ. ይናገሩት
2. የተዋበ   ሀ. ያማረ   ለ. ያጌጠ   ሐ. የተሸቀረቀረ   መ. ሁሉም
3. ድርና ማግ   ሀ. ተስማምተው   ለ. ተለያይተው   ሐ. ተዛምደው   መ. ተላምደው
4. በአንቀፅ አንድ ‹‹በወፍራምና በቀጭን <u>አስማምተው</u> እየዘመሩ ካበባ አበባ ይዘዋወሩ ነበር ።›› በሚለው ዓረፍተ ነገር የተሰመረበት ቃል ፍቺ

ሀ. አጣብቀው   ለ. አዋህደው   ሐ. አደላድለው መ. አደናግረው

5. በአንቀጽ ሁለት <<ይህ አበባህ አሁን ይረግፋል!>> በሚለው ዓረፍተ ነገር ለተሰመረበት ቃል ፍቺ

ሀ. ይደርቃል   ለ. ይጠወልጋል   ሐ. ያብባል   መ. ያቀጠቅጣል

**ትእዛዝ ሁለት ቀጥሎ የምንባቡን ዋና ዋና ሃሳቦች የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል። የምንባቡን ሃሳብ መሰረት በማድረግ የጥያቄዎቹ ትክክለኛውን መልስ ፃፍ/ፊ።**

1. የአንደኛውን አንቀጽ ዝርዝር ሀሳብ ግለጽ/ጪ
2. የሁለተኛውን አንቀጽ ዋና ሃሳብ ግለጽ/ጪ
3. ስለፍታውራሪ መሸሻ ግቢ የተነገረውን ገለፃ በማስመሰል አካባቢያችሁን ግለጹ
4. በሰው ልጅ ህይወትና በጊዜው በሚለዋወጡ ቡቃያዎች መካከል ምን ግንኙነት አለ? በምሳሌ አብራራ/ሪ።

የትምህርት መረጃ፡- በገለጻ የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጀ ጽሁፍ

ግምገማ፡- የክፍል ስራ በመስጠት   የቃል ጥያቄ

# አባሪ መ

# ለተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# የሂዩማኒቲስ፤ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ክፍለትምህርት ድኅረምረቃ መርሀግብር

# በተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ

**ኮድ---------**

## ውድ ተማሪዎች

ይህ መጠይቅ፣የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር አንብቦ የመረዳትን ችሎታ በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና በሚል ርዕስ ለሚጠና ጥናት መረጃ ለመሠብሰብ የተዘጋጀ ነው። የምትሰጡት መረጃ ለዚሁ አገልግሎት የሚውል ሲሆን፣ ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ ነው። የእናንተ ትክክለኛ ምላሽ የጥናቱን ውጤት ተቀባይነት እንዲኖረው ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል። ስለሆነም ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቀጥታ በመመለስ ትብብር እንድታደርጉልኝ እጠይቃለሁ። ስለትብብራችሁ በቅድሚያ አመሰግናለሁ።

**አባሪ ሁለት**

**ማሳሰቢያ**

1. በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም።
2. መጠይቁን በየግላችሁ መሙላት ይኖርባችኋል። ከሌላ ሰው ጋር የምትሞሉት ከሆነ በእናንተ ምላሽ ላይ የተመረኮዘው ጥናት ውጤቱ ሊዛባ ይችላል።

**መመሪያ** ከዚህ በታች የተሰጡት ጥያቄዎች እያንዳንዳቸው አራት አማራጮች አሏቸው ። እያንዳንዱን ጥያቄ በጥንቃቄ በማንበብ ከፊት ለፊት ከቀረቡት አራትአማራጮች መካከል በምትስማሙበት በአንዱ አማራጭ ትይዩ ይህን "x" ምልክት አድርጉ።

ከ1 እስከ4 ያሉት ቁጥሮች ውክልናም እንደሚከተለው ነው፤

1. በጣም አልስማማም፤ 2. አልስማማም፤3. እስማማለሁ፤4. በጣም እስማማለሁ፤

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ያለውን የሀሳብ ትስስር እለያለሁ። | | | | |
| 2 | የማነበውን ሁሉ ለመረዳት አልቸገርም። | | | | |
| 3 | የማነበው ጽሁፍ እንዲገባኝ የተለያዩ የማንበብ ብልሀቶችን እጠቀማለሁ፡ | | | | |
| 4 | የምንባቡን ሀሳብ አሳጥሬ መግለጽ እችላለሁ። | | | | |
| 5 | የማነበው ጽሁፍ እንዲገባኝ ጽሁፉ ለቀረበበት የጽሁፍ አወቃቀር ትኩረት እሰጣለሁ። | | | | |
| 6 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦችን ለመረዳት እቸገራለሁ። | | | | |
| 7 | አንብቦ ለመረዳት የጽሁፍ አወቃቀርን መረዳት አስፈላጊ መሆኑን አውቃለሁ ። | | | | |
| 8 | የማነበው ጽሁፍ የተደራጀበትን የጽሁፍ አወቃቀር መለየት | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | እችላለሁ። | | | | |
| 9 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ የማገኛቸውን ፍንጭ ሰጪ ቃላትና ሀረጋት የምንባቡን መልእክት ለመረዳት ያግዙኛል። | | | | |
| 10 | እንብቦ ለመረዳት የጽሁፉን አወቃቀር ማወቅ ጠቀሜታ አለው ብዬ አላስብም። | | | | |

# አባሪ ሠ

# ቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት

## ቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት

| ኮድ | የጥያቄዎች ተራ ቁጥር | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| 1 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 3 |
| 2 | 1 | 3 | 2 | 4 | 3 | 1 | 1 | 1 | 4 | 4 |
| 3 | 2 | 1 | 4 | 4 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 4 |
| 4 | 2 | 4 | 1 | 2 | 4 | 3 | 4 | 4 | 2 | 2 |
| 5 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 2 | 2 | 4 | 4 |
| 6 | 1 | 2 | 4 | 3 | 4 | 1 | 3 | 2 | 3 | 2 |
| 7 | 1 | 3 | 2 | 2 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 |
| 8 | 2 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 1 | 3 | 2 |
| 9 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 1 | 4 | 4 |
| 10 | 3 | 1 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 3 | 3 | 1 |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | 4 | 2 | 1 | 4 | 4 | 2 | 1 | 2 | 3 | 3 |
| 12 | 4 | 3 | 4 | 1 | 3 | 1 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| 13 | 2 | 3 | 2 | 1 | 3 | 1 | 3 | 4 | 2 | 3 |
| 14 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 2 | 2 | 2 | 4 |
| 15 | 2 | 4 | 1 | 2 | 3 | 3 | 4 | 1 | 3 | 4 |
| 16 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 2 | 2 | 1 |
| 17 | 2 | 2 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 |
| 18 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 1 | 2 | 2 | 2 | 4 |
| 19 | 2 | 2 | 4 | 3 | 1 | 4 | 2 | 1 | 4 | 2 |
| 20 | 2 | 1 | 2 | 1 | 3 | 4 | 1 | 1 | 3 | 4 |
| 21 | 1 | 3 | 4 | 4 | 1 | 4 | 2 | 1 | 3 | 4 |
| 22 | 2 | 3 | 1 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 4 | 3 |
| 23 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 4 |
| 24 | 4 | 4 | 2 | 2 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 25 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 3 | 2 | 2 | 1 | 3 |
| 26 | 2 | 4 | 1 | 2 | 3 | 2 | 4 | 4 | 3 | 1 |
| 27 | 2 | 3 | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 | 2 | 2 | 3 |
| 28 | 3 | 1 | 3 | 2 | 4 | 1 | 1 | 2 | 2 | 3 |
| 29 | 2 | 4 | 2 | 4 | 3 | 2 | 2 | 4 | 1 | 2 |
| 30 | 2 | 2 | 4 | 1 | 3 | 2 | 4 | 4 | 2 | 3 |
| 31 | 2 | 4 | 2 | 2 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| 32 | 1 | 2 | 2 | 2 | 4 | 2 | 3 | 4 | 4 | 3 |
| 33 | 2 | 4 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 4 |
| 34 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 4 | 4 |
| 35 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 1 |
| 36 | 2 | 4 | 1 | 3 | 3 | 2 | 2 | 4 | 1 | 4 |
| 37 | 2 | 3 | 2 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 38 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 1 | 1 | 2 | 3 | 1 |
| 39 | 2 | 2 | 3 | 2 | 4 | 3 | 2 | 2 | 4 | 4 |
| 40 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 2 | 3 | 1 | 4 | 3 |
| 41 | 2 | 4 | 4 | 4 | 3 | 1 | 2 | 2 | 3 | 4 |
| 42 | 2 | 1 | 3 | 3 | 4 | 2 | 4 | 1 | 3 | 4 |
| 43 | 2 | 3 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 |
| 44 | 3 | 2 | 4 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 4 |
| 45 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 1 | 2 | 2 | 2 | 3 |
| 46 | 2 | 4 | 2 | 4 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 | 4 |
| 47 | 1 | 3 | 2 | 4 | 2 | 1 | 4 | 4 | 4 | 3 |
| 48 | 2 | 4 | 1 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 4 | 3 |
| 49 | 2 | 4 | 2 | 2 | 2 | 1 | 3 | 3 | 3 | 1 |
| 50 | 1 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 3 | 1 | 1 |
| 51 | 2 | 4 | 3 | 4 | 4 | 1 | 2 | 2 | 4 | 4 |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 52 | 3 | 3 | 1 | 3 | 1 | 2 | 1 | 1 | 2 | 4 |

## ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ

| የጥያቄዎች ተራ ቁጥር | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኮድ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| 1 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 4 | 3 | 4 | 4 |
| 2 | 1 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 1 | 1 | 4 | 4 |
| 3 | 3 | 1 | 1 | 4 | 1 | 1 | 4 | 3 | 4 | 4 |
| 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 4 | 2 | 2 |
| 5 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| 6 | 1 | 1 | 4 | 4 | 3 | 1 | 1 | 4 | 3 | 1 |
| 7 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 |
| 8 | 2 | 3 | 4 | 4 | 2 | 3 | 4 | 3 | 4 | 1 |
| 9 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 1 | 4 | 3 | 4 | 1 |
| 10 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 3 | 1 |
| 11 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 2 | 4 | 4 | 3 | 3 |
| 12 | 4 | 3 | 4 | 1 | 1 | 2 | 1 | 4 | 4 | 4 |
| 13 | 3 | 4 | 1 | 4 | 2 | 2 | 3 | 4 | 4 | 3 |
| 14 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 1 | 4 | 3 | 4 | 1 |
| 15 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 | 1 | 1 | 4 | 4 | 4 |
| 16 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 2 | 3 | 4 | 2 | 1 |
| 17 | 2 | 2 | 4 | 1 | 3 | 4 | 3 | 4 | 1 | 3 |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 18 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| 19 | 2 | 2 | 1 | 4 | 1 | 2 | 4 | 3 | 4 | 2 |
| 20 | 2 | 1 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 3 | 3 | 4 |
| 21 | 2 | 3 | 4 | 1 | 1 | 4 | 3 | 4 | 1 | 4 |
| 22 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 | 1 | 4 | 3 | 4 | 1 |
| 23 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 4 | 2 | 4 | 4 |
| 24 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 1 | 1 |
| 25 | 4 | 2 | 4 | 1 | 3 | 2 | 4 | 2 | 3 | 3 |
| 26 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 3 |
| 27 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 |
| 28 | 3 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 3 | 3 | 1 | 1 |
| 29 | 2 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 4 | 4 | 1 | 2 |
| 30 | 2 | 2 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 | 4 | 4 |
| 31 | 2 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| 32 | 3 | 2 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 1 |
| 33 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 4 | 1 |
| 34 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 3 |
| 35 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 3 | 1 |
| 36 | 3 | 4 | 1 | 3 | 1 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| 37 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 1 |
| 38 | 2 | 2 | 3 | 2 | 4 | 1 | 4 | 3 | 3 | 1 |
| 39 | 2 | 2 | 3 | 2 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 |
| 40 | 4 | 3 | 2 | 4 | 3 | 1 | 4 | 3 | 4 | 1 |
| 41 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 1 | 2 | 4 | 4 | 4 |
| 42 | 2 | 1 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 3 | 1 |
| 43 | 3 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 4 | 4 |
| 44 | 3 | 2 | 4 | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 |
| 45 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 1 | 2 | 3 | 2 | 4 |
| 46 | 3 | 4 | 2 | 4 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 1 |
| 47 | 3 | 3 | 2 | 4 | 2 | 1 | 2 | 1 | 4 | 1 |
| 48 | 1 | 4 | 1 | 2 | 3 | 1 | 4 | 4 | 4 | 1 |
| 49 | 3 | 4 | 2 | 3 | 1 | 2 | 4 | 4 | 3 | 2 |
| 50 | 4 | 3 | 2 | 3 | 4 | 2 | 4 | 2 | 4 | 1 |
| 51 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 1 | 4 | 2 | 4 | 4 |
| 52 | 3 | 3 | 1 | 1 | 1 | 2 | 1 | 4 | 1 | 4 |

አባሪ ረ

## የቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት

## በሶስት አራሚዎች የታረመው የተማሪዎች የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት

| የቅድመ ፈተና ውጤት ከ(60%) | | | | | የድህረ ፈተና ውጤት ከ(60%) | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አራሚዎች | | | | | አራሚዎች | | | |
| ተ.ቁ | አራሚ 1 | አራሚ 2 | አራሚ 3 | አማካይ ውጤት | አራሚ 1 | አራሚ 2 | አራሚ 3 | አማካይ ውጤት |
| 1 | 28 | 24 | 26 | 26 | 40 | 44 | 48 | 44 |
| 2 | 32 | 32 | 30 | 31 | 38 | 36 | 30 | 35 |
| 3 | 22 | 18 | 24 | 21 | 28 | 32 | 32 | 30 |
| 4 | 22 | 21 | 18 | 20 | 30 | 34 | 26 | 30 |
| 5 | 34 | 30 | 26 | 30 | 36 | 35 | 34 | 35 |
| 6 | *32* | *34* | 36 | 34 | 33 | 35 | 35 | 35 |
| 7 | 36 | 40 | 42 | 39 | 51 | 53 | 52 | 52 |
| 8 | 26 | 30 | 28 | 28 | 34 | 30 | 26 | 30 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 9 | *16* | *18* | 20 | 18 | 31 | 33 | 33 | 32 |
| 10 | *24* | *28* | 25 | 26 | 34 | 30 | 32 | 32 |
| 11 | *20* | *23* | 23 | 22 | 23 | 20 | 22 | 22 |
| 12 | *28* | *26* | 30 | 28 | 37 | 38 | 38 | 38 |
| 13 | *32* | *34* | 36 | 34 | 33 | 28 | 29 | 30 |
| 14 | *28* | *30* | 26 | 28 | 29 | 29 | 27 | 28 |
| 15 | 23 | 20 | 23 | 22 | 30 | 30 | 26 | 30 |
| 16 | 20 | 22 | 26 | 23 | 32 | 33 | 34 | 34 |
| 17 | 22 | 23 | 21 | 22 | 48 | 52 | 50 | 50 |
| 18 | 19 | 18 | 18 | 18 | 27 | 31 | 26 | 28 |
| 19 | 22 | 18 | 20 | 20 | 40 | 44 | 42 | 42 |
| 20 | 17 | 14 | 18 | 16 | 37 | 38 | 33 | 36 |
| 21 | 38 | 39 | 34 | 37 | 33 | 33 | 35 | 34 |
| 22 | *17* | *17* | 15 | 16 | 28 | 30 | 28 | 28 |
| 23 | 18 | 16 | 20 | 18 | 21 | 22 | 22 | 22 |
| 24 | 26 | 24 | 22 | 24 | 36 | 36 | 34 | 36 |
| 25 | 36 | 38 | 34 | 36 | 40 | 40 | 40 | 40 |
| 26 | 26 | 30 | 32 | 29 | 40 | 38 | 36 | 38 |
| 27 | 31 | 33 | 29 | 31 | 30 | 30 | 28 | 30 |
| 28 | 40 | 37 | 37 | 38 | 36 | 38 | 34 | 36 |
| 29 | 10 | 11 | 13 | 12 | 20 | 24 | 20 | 22 |
| 30 | 21 | 22 | 18 | 20 | 32 | 30 | 33 | 32 |
| 31 | *23* | *23* | 26 | 24 | 36 | 34 | 22 | 34 |
| 32 | 23 | 20 | 23 | 22 | 30 | 28 | 30 | 30 |
| 33 | 30 | 26 | 28 | 28 | 44 | 46 | 44 | 45 |
| 34 | 23 | 23 | 20 | 22 | 19 | 17 | 18 | 18 |
| 35 | 19 | 18 | 18 | 18 | 27 | 26 | 26 | 26 |
| 36 | 40 | 42 | 38 | 40 | 37 | 36 | 34 | 36 |
| 37 | 23 | 27 | 25 | 25 | 34 | 30 | 30 | 32 |
| 38 | 26 | 24 | 22 | 24 | 36 | 32 | 34 | 34 |
| 39 | 28 | 30 | 32 | 30 | 43 | 40 | 44 | 42 |
| 40 | 27 | 27 | 29 | 28 | 35 | 35 | 37 | 36 |
| 41 | *32* | *34* | 36 | 34 | 33 | 28 | 29 | 30 |
| 42 | *23* | *23* | 26 | 24 | 36 | 36 | 34 | 36 |
| 43 | *32* | *30* | 28 | 30 | 28 | 28 | 26 | 28 |
| 44 | *41* | *39* | 41 | 40 | 37 | 35 | 36 | 36 |
| 45 | *28* | *26* | 30 | 28 | 37 | 38 | 33 | 36 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 46 | *32* | *35* | 31 | 33 | 28 | 29 | 33 | 30 |
| 47 | 28 | 32 | 30 | 30 | 38 | 40 | 42 | 40 |
| 48 | 26 | 30 | 28 | 28 | 34 | 37 | 36 | 36 |
| 49 | 26 | 27 | 30 | 28 | 30 | 29 | 31 | 30 |
| 50 | 34 | 30 | 26 | 30 | 33 | 33 | 31 | 32 |
| 51 | 15 | 13 | 14 | 14 | 28 | 28 | 29 | 28 |
| 52 | *22* | *21* | 18 | 20 | 30 | 34 | 26 | 30 |

# አባሪ ሰ
# በሙከራዊ ጥናቱ የተከናወኑ ተግባራት

የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለውን ሚና ለመመርመር በተካሄደው ጥናት የተከናወኑ ተግባራት ለተማሪዎች የቅድመና የድህረ ፈተናዎችን መስጠት እና የሙከራ ትምህርት ማስተማር ነበሩ። እነዚህ ተግባራት ከሚያዚያ 13/ 8/ 2009 እስከ ግንቦት 18/ 9/ 2009 ዓ.ም. ተከናውነዋል።

የቅድመ ፈተናው ዋና ጉዳይ ተማሪዎች ከትምህርቱ በፊት የነበራቸውን የቀደመ እውቀት ለመለካት ሲሆን ድህረ ፈተናው ደግሞ ተማሪዎች ትምህርቱን ከተማሩ በኋላ ያመጡትን ለውጥ ለመፈተሽ ነው።

የሙከራ ትምህርቱ ያስፈለገበት ዋና ጉዳይ በገለጻና በምክንያትና ውጤት የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጁ ጽሁፎችን በማስተማር ከትምህርቱ በኋላ የመጣ ለውጥ መኖሩን ወይም አለመኖሩን በመመርመር የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት አንብቦ ለመረዳት ያለውን ሚና ለማረጋገጥ ነው።

ከላይ በተቀመጠው ቀን የተከናወኑ ተግባራት ከዚህ በታች ቀርበዋል።

ቀን13/ 8/ 2004ዓ/ም.

ሰአት 4፡00

በዚህ እለት ቅድመ ፈተናውን ለመፈተን በተማሪዎች ቁጥር ልክ የጥያቄና የመልስ መስጫ ወረቀቶችን በመያዝ ወደ መፈተኛ ክፍል በማምራት ሁሉም ተማሪዎች መገኘታቸውን ከተረጋገጠ በኋላ በአንድ ጠረጴዛ ላይ ሁለት ሁለት ሆነው እንዲቀመጡ አጥኚዋ አድርጋለች። ለእያንዳንዱ ተማሪ የጥያቄ ወረቀቱን በማደል ፈተናውን በተሰጠው ጊዜ እና በትእዛዙን መሰረት መስራት እንዳለባቸው በመንገር እንዲሰሩ ተደርጓል።ጥቂት ተማሪዎች ፈተናው ሊጠናቀቅ ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሩ የመልስ መስጫ ወረቀቶችን በመስጠት ወጥተዋል። ቀሪዎቹ ተማሪዎች በተሰጠው ጊዜ ሰርተው በመጨረሳቸው የመልስ መስጫ ወረቀቶቹ ተሰብስበዋል።

ቀን 17/ 8/2009ዓ.ም.

ሰአት 3፡00

ትምህርት አንድ

የመጀመሪያውን የሙከራ ትምህርት ለመስጠት ለትምህርቱ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን በመያዝ ተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት ከሚሰጥበት ክፍል መኖራቸውን በማረጋገጥ ትምህርቱን መስጠት ተጀመረ። በትምህርቱ መግቢያ ተማሪዎች ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ያላቸውን የቀደመ እውቀት ለመቀስቀስ

1. የጽሁፍ አወቃቀር ማለት ምን ማለት ነው?

2. የጽሁፍ አወቃቀር አይነቶችን ግለጹ?

የሚሉ ጥያቄዎችን በማቅረብ ትምህርቱ ተጀመረ ተማሪዎችም እጃቸውን በማንሳት ይሆናል ያሉትን መልስ እንዲመልሱ አደረኩ። ከመልሶቻቸው መካከል የጽሁፍ አወቃቀር ማለት ሀሳብን በጽሁፍ ማስፈር ነው። የጽሁፍ አወቃቀር አይነቶች መግቢያ፣ መደምደሚያና ሀተታ ተራኪ፣ ገላጭ ወዘተ. የሚሉት ይገኙበታል። ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ማብራሪያ በመስጠት፣ ስለ ጽሁፍ አወቃቀር አይነቶች ምንነት ገለጻ በማድረግና የተለያዩ ምሳሌዎችን በመስጠት

ተማሪዎች ስለ ሁሉም የጽሁፍ አወቃቀሮች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ ትምህርቱ ቀርቧል። በመጀመሪያ ለማብራራት የተሞከረው ስለ ማነጻጸርና ማወዳደር የጽሁፍ አወቃቀር ሲሆን ለዚህም ለአስረጅነት የቀረበው ከቀድሞው የዘጠነኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ጥንታዊ ሴቶችንና ዘመናዊ ሴቶችን በማወዳደርና በማነጻጸር የቀረበውን ጽሁፍ በማንበብ ስለ አወቃቀሩ የቀረቡ ጥያቄዎችን በማሰራት ትምህርቱ ተሰጥቷል። የትምህርቱ ስአት በመጠናቀቁ ሌሎች የጽሁፍ አወቃቀሮች በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ እንደሚቀርቡ በመንገር ከክፍል ወጥቻለሁ

ቀን 19/ 8/ 2009 ዓ.ም.

ስአት 3፡00

የዕለቱ ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት የባለፈው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ምን እንደነበረና ምን ምን ተግባራትን እንዳከናወኑ በመጠየቅ እንዲነቃቁ ተደርጓል። በመቀጠልም የዕለቱን ትምህርት ባለፈው ክፍለ ጊዜ በቅደም ተከተልና በችግር መፍትሄ የጽሁፍ አደረጃጀት የተዋቀሩ ጽሁፎችን ለማስረማር ሚንጊ ነኝ እና ብረት የማምረት ሂደት በሚል ርእስ የቀረበ ጽሁፎችን ለማስተማሪያነት በማቅረብ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ የጽሁፍ አወቃቀሩን እንዲለዩ ለማድረግ ተሞክሯል።

1. የኩሉ ሆራ እናት ያጋጠማት ችግር ምንድን ነው?
2. የኩሉ ሆራ እናት ላጋጠማት ችግር የወሰደችው መፍትሄ ምንድን ነው?
3. ብረትን ለማምረት የሚያልፍባቸውን ሂደቶች ግለጹ?
4. ጽሁፎቹ የተደራጁት በየትኛው የጽሁፍ አወቃቀር ነው?

የሚሉ ጥያቄዎችን በጥቁር ሰሌዳው ላይ በመጻፍ መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል። ለአንደኛው ጥያቄ የልጇ ጥርስ ማብቀል፣ የሽማግሌዎች ወደ ቤቷ መምጣት፣ ለሁለተኛው ልጇን መደበቅ፣ ጥርሱን በቅጠል ማሸት፣ ለሶስተኛው ጥያቄ ብረት ማቅለጥ፣ ኦክሲጅን መጨመርና ማቀዝቀዝ ሚንጊ ነኝ የሚለው በችግር መፍትሄ፣ ብርት ማምረት በቅደም ተከተል የቀረበ ነው። በማለት መልስ ሰጥተዋል። አጥኚዋም ለጥያቄዎቹ ትክክለኛውን መልስ በመስጠት በዚህ ጥናት ትኩረት የሚሰጥባቸው የጽሁፍ አወቃቀሯች ገለጻ እና ምክንያትና ውጤት መሆናቸውን በመግለጽ ክፍለ ጊዜው ተጠናቋል።

ቀን 24/ 8 / 2009 ዓ.ም.

ስአት 8፡ 00

ትምህርት ሁለት

የእለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት የክፍሉ ተማሪዎች መገኘታቸውን ለማረጋገጥ ቁጥር ተጠርቷል ሁሉም ተማሪዎች መገኘታቸው በማረጋገጥ በየቡድናቸው እንዲቀመጡ አጥኚዋ አድርጋለች። ለእለቱ ትምህርት ማስተማሪያ የተዘጋጀው በገለጻ የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጀ ጽሁፍ ነበር። (አባሪ "ለ" ይመልከቱ) የትምህርቱ ይዘቶችም የጽሁፉን አወቃቀር መለየት ከምንባቡ ለወጡ ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍች መስጠት የጽሁፉን መልእክት መግለጽ የሚሉ ነበሩ። ጽሁፉም ለእያንዳንዱ ተማሪ ታድሏል። እያንዳንዱ ተማሪ ምንባቡን በለሆሳስ እንዲያነቡ ተደርጓል። በዚህ ወቅት ከተወሰኑ ተማሪዎች በስተቀር አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ጽሁፉን አንብበው መጨረሳቸውን ገልጸዋል ይሁን እንጅ ሁለህም ተማሪዎች አንብበው እስኪጨርሱ በመጠበቅ መጨረሳቸው ከተረጋገጠ በኋላ

1. ያነበባችሁት ጽሁፍ የተደራጀው በየትኛው የጽሁፍ አወቃቀር ነው? እንዴት ይህን ልትሉ ቻላችሁ?

የሚል ጥያቄ በአጥኚዋ ቀርቧል። ለጥያቄዎቹ የተለያ መልስ ሰጥተዋል። በማነጻጸርና በማወዳደር ብሎ መልስ የሰጠው ተማሪ ያቀረበው ምክንያት እረኞቹንና ከብቶችን ስላመሳሰለ የሚል ነው። ሌላው መልስ ሰጭ በምክንያትና ውጤት ነው። ምክንያቱም አገር ለቀው የሄዱት በድርቁ ምክንያት ነው የሚለው የአብዛኛዎቹ ተማሪዎች መልስ ሲሆን የተወሰኑ ተማሪዎች በገለጻ ነው ምክንያቱም ምስል ከሳች ነው። የሚሉ መልሶችን ሰጥተዋል። አጥኚዋም በገለጻ የጽሁፍ አወቃቀር እንደቀረበ ምክንያቱም ጽሁፉ በአእምሮ ውስጥ ምስል ከሳች መሆኑን በማስረዳት መልስ ሰጥታለች። በመቀጠል ከአነበቡት ምንባብ ሃሳብ በመነሳት ትእዛዝ አንድ ላይ የቀረቡ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ተደርጓል። ለእለቱ ትምህርት የተመደበው ስአት በማለቁ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ የተሰጣቸውን ምንባብ ትተው እንዳይመጡ በማሳሰብ ትምህርቱ ተጠናቋል።

ቀን 26/ 8/ 2009 ዓ .ም.

ስአት 8፡00

ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት የባለፈው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ምን እንደነበረና ምን ምን ተግባራትን እንዳከናወኑ በመጠየቅ እንዲነቃቁ ተደርጓል። በመቀጠልም የዕለቱን ትምህርት ለማከናወን ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተሰጣቸውን ምንባብ ይዘው መምጣታቸው ተጠይቀዋል አንድ ተማሪ ይዞ እንዳልመጣ ገልጿል። ሌላ ጊዜ ማምጣት እንዳለበት በመምከር አጥኚዋ እረስተው ሊመጡ ይችላሉ ብላ በመስጋት ለመጠባበቂያ ከያዘችው ሰጥታዋለች። በምንባቡ ግርጌ ላይ የሚገኙትን ከምንባቡ የወጡ የትእዛዝ ሁለትን ጥያቄዎች በግላቸው በክፍል ውስጥ እንዲሰሩ ትእዛዝ በማስተላለፍ እንዲሰሩ ተደርጓል። ጥንድ ጥንድ በመሆን እንዲጣመሩ ትዕዛዝ በመስጠት ተጣምረዋል። በሰጡት መልስ ላይ በጥንድ ተወያይተው ትክክለኛ መልስ ያሉትን ገልጻዋል። ወፎቹ የተሰደዱት ለምንድን ነው? ምክንያቱን? ግለጽ/ጪ ለሚለው ጥያቄ ስለ ራባቸው፣ እሚያርፉበት ዛፍ ስላጡ፣ የሚሉ መልሶችን ሰጥተዋል። ለሌሎቹ ጥያቄዎችም መስራታቸውን ከሰጡት መልስ ለማረጋገጥ ተችሏል።

ቀን 1/ 9/ 2009 ዓ.ም.

ሰአት 3፡ 00

ትምህርት ሶስት

የዕለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት አጥኚዋ ሁሉም ተማሪዎች መገኘታቸውን ለማረጋገጥ ቁጥር ጠርታለች በእለቱ ሁለት ተማሪዎች አለመገኘታቸውን አረጋግጣለች። ለእለቱ ትምህርት የቀረበው ጽሁፍ በምክንያትና ውጤት የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጀ ነበር ( አባሪ "ለ" ይመልከቱ) የክፍለ ትምህርት ሁለትን የትምህርት ርዕሶች በማስተዋወቅ ትምህርቱ ተጀምሯል። አጥኚዋ ምንባቡን ለእያንዳንዱ ተማሪ አድላለች። በመቀጠልም በቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን እንዲወያዩና ሃሳባቸውን እንዲገልጹ ተደርጓል።

1. ስኬታማ መሆን የሚቻለው እንዴት ነው?

2. የስኬታማ ሰዎችን የህይወት ተሞክሮ የመመልከት ጥቅሙ ምንድን ነው?

ስኬታማ መሆን የሚቻለው በመማርና ጠንክሮ በመስራት ሲሆን ለሁለተኛው ጥያቄ የስኬታማ ሰዎችን የህይወት ተሞክሮ የመመልከት ጥቅሙ እነሱ የሰሩትን ተግባር በማከናወን እንደነሱ ለመሆን ነው። የሚሉት የአብዛኛዎቹ ተማሪዎች መልስ ነበር። በመቀጠልም ምንባቡን እንዲያነ ተደርጓል። ሁሉም ተማሪዎች ምንባቡን ትኩረት በመስጠት ሲያነቡት ተስተውሏል። በንባብ ወቅት ለቀረበ ጥያቄ ልጁ ካሳየው ድፍረትና ልበ ሙሉነት በመነሳት ዜናውን እንዲያቀርብ ቢፈቀድለት ያለ ስህተት የሚያነበው ይመስልሃል/ሻል/? አንድ ተማሪ ልምምድ

ስላደረገ ሊያነብ ይችላል። በማለት ሲመልስ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ግን እሳሳታለሁ ብሎ ስለሚፈራ አያነበውም በማለት መልሰዋል። በድጋሚ ወደምንባቡ በመሄድ ንባባቸውን እንዲቀጥሉ ተደርጓል። በመጨረሻም በትእዛዝ አንድ ስር ለቀረቡ ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ ሁነው ከተወያዩ በኋላ ምላሽ በመቀበልና ትእዛዝ ሁለትና ሶስት የቤት ስራ ሰርተው እንዲመጡ በመስጠት የዕለቱ ትምህርት ተጠናቋል።

ቀን 3/ 9/ 2009 ዓ.ም.

ስአት 8፡00

ባለፈው ክፍለ ጊዜ ያነበቡት ምንባብ በምን አይነት የጽሁፍ አወቃቀር የተዋቀረ እንደነበረና ምን ላይ ያተኮረ እንደሆነ በመጠየቅ ያለፈውን ክፍለ ጊዜ ትምህርት በማስታወስ የእለቱ ትምህርት ተጀምሯል። የተሰጠውን የቤትሥራ መስራታቸውን ተጠይቀው ሁሉም ተማሪዎች እጃቸውን በማውጣት መስራታቸውን ገልፀዋል አጥኚዋም እየተዘዋወረች በመመልከት ማረጋገጥ ችላለች። የምርጫ ጥያቄዎ እንዳንዳቸው እጃቸውን በማውጣት እንዲመልሱ ተደርጓል። አብዛኛወቹ ተማሪዎች ትክክለኛውን መልስ የሰጡ ሲሆን ለአንደኛው ጥያቄ ሁለት ለአራተኛው ጥያቄ ስድስት ተማሪዎች የተሳሳተ ምላሽ ሰጥጠዋል። የአዛምድ ጥያቄዎች ላይ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ባለመስጠታቸው እንደገና ምንባቡን እንዲያነቡ ተደርጓል። እንደገና ጥያቄዎቹን በማቅረብ ትክክለኛውን መልስእንዲሰጡ በማድረግ የእለቱ ትምህርት ተጠናቋል።

ቀን 8 /9/ 2009 ዓ.ም.

ስአት 3፡00

ትምህርት አራት

ለትምህርት አራት በገለጻና በምክንያትና ውጤት የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጁ ጽሁፎችና ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች ለማስተማሪያነት ቀርበዋል።አባሪ "ለ" ይመልከቱ። የጽሁፍ አወቃቀር መለየት፣ ለቃላትና ለሀረጋት አውዳዊ ፍች መስጠት፣ የምንባቡን ዋና እና ዝርዝር ሀሳብ እንዲገልጹ ማድረግ፣ የእለቱ ትምህርት ይዘዞቶች ናቸው። ምንባቡና ጥያቄዎቹ ለእያንዳንዱ ተማሪ ታድሏል። ምንባቦቹን በለሆሳስ እንዲያነቡ ተደርጓል። ተማሪዎች ምንባቡን አንብበው መጨረሳቸው ከተረጋገጠ በኋላ 1. ጽሁፉ የተደራጀው በየትኛው የጽሁፍ አወቃቀር ነው? እንዴት መወቅ ቻልክ/ሽ? የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበው በቃል ተመልሰዋል። ካለፉት ክፍለ ጊዜያት በተሸለ የጽሁፍ አወቃቀሩን መለየት

እንደቻሉ ተስተውሏል። በሁለቱም ምንባቦች በትእዛዝ አንድ የቀረቡትን ጥያቄዎች የክፍል ስራ እንዲሰሩአጥኚዋ ትእዛዝ አስተላልፋለች። ሁሉም ተማሪዎች የክፍል ስራውን ሰርተው ሳያጠናቅቁ ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ በማለቁ ትእዛዝ ሁለትን የቤት ስራ እንዲሰሩ ተደርጓል።

ቀን 10/ 9/ 2009 ዓ.ም.

ሰአት 3፡00

የእለቱ ትምህርት የተጀመረው ባለፈው ክፍለ ጊዜ ምን ምን ተግባራት እንዳከናወኑ ምን እንደቀረ በመጠየቅ ነው። የተከናወኑ ተግባራትን በመግለጽ የክፍል ስራና የቤት ስራ እንደተሰጣቸው ገልጸዋል። የክፍል ስራውንም ሆነ የቤት ስራውን መስራታቸውን ገልጸዋል። በሰጡት መልስ ላይ በጋራ እንዲወያዩ በማድረግ ሁሉም ተማሪዎች በውይይቱ መሳተፋቸውን ለማረጋገጥ ተሞክሯል። ከውይይቱ በኋላ ለጥያቄዎቹ ከየቡድኑ መልስ ተሰጥቷል።የጽሁፍ አወቃቀሩን ለመለየት ፍንጭ የሰጡህ/ሽ የትኞቹ ናቸው? የጥፍሮቿ ርዝመት ቀይ ቀለም መቀባቱ የልጇ ቅልጥሞች ረጃጅም መሆን የሰውየው ውፍረት የተገለጸበትና የመሳሰሉት ምስል እንዲከስት ያደርጋሉ። የባትሪዎች በየቦታው መውደቅ የሚያስከትለው ጉዳት የተገለጸበት ሀሳብ የምክንያትና ውጤት ትስስሩን ያሳያሉ። በማለት መልሰዋል። ያልገባቸውን እንዲጠይቁ በማድረግና መልስ በመስጠት ክፍለ ጊዜው ተጠናቋል።

ቀን 15 /9/ 2009 ዓ.ም.

ሰአት 8፡00

ትምህርት አምስት

የዕለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት አጥኚዋ ሁሉም ተማሪዎች መገኘታቸውን ለማረጋገጥ ቁጥር ጠርታለች በዚህ ክፍለ ጊዜ በገለጻና በምክንያትና ውጤት የተዋቀሩ ጽሁፎችን መሠረት አድርጎ አንብቦ መረዳትን ለማስተማር የተደራጁ ምንባቦች ቀርበዋል።አባሪ "ለ" ይመልከቱ። አጥኝዋ ምንባቡን ለእያንዳንዱ ተማሪ አድላለች። በመቀጠልም በቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎች በቡድን በመሆን እንዲወያዩና ሃሳባቸውን እንዲገልጹ ተደርጓል።

1. ልጆችን በአጓጉል ቦታ እንዲውሉ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው?

2. በጸደይ ወቅት እጽዋት ምን ይመስላሉ?

በሱስ መጠመድ፣ ከመጥፎ ጓደኛ ጋር መዋል፣ የቤተሰብ ቁጥጥር ማነስ ለሁለተኛው ጥያቄ አረንጓዴ ይሆናሉ አዝእርት ያፈራሉ በማለት ተማሪዎች መልሰዋል። በመቀጠልም የተሰጣቸውን ሁለት ጽሁፍ በመጀመሪያ ምንባብ አንድን በመቀጠል ምንባብ ሁለትን በለሆሳስ እንዲያነቡ ተደርጓል። ሁሉም ተማሪዎች ምንባቡን ትኩረት በመስጠት ሲያነቡት ተስተውሏል። በንባብ ወቅት ለቀረበ ጥያቄ ከላይ ከቀረበው አንቀጽ የተረዳኸውን/ሽውን ዋና ሀሳብ ግለጽ/ጪ የፊውታራሪ ግቢ ያማረ መሆኑን፣ በጸደይ ወቅት የምድር ልምላሜ የሚማርክ መሆኑን ይገልጻል የሚሉ ምላሾችን ሰጥተዋል። በድጋሜ ወደምንባቡ በመሄድ ንባባቸውን እንዲቀጥሉ ተደርጓል። በመጨረሻም ጽሁፎቹ በየትኛው የጽሁፍ አወቃቀር የቀረቡ ናቸው የሚል ጥያቄ በማቅረብ እንዲመልሱ ተደርጓል። ምንባብ አንድ በምክንያትና ውጤት ምንባብ ሁለት በገለጻ እንደቀረበ ከነምክንያቱ ገልጸዋል። በዚህ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ያላቸው ግንዛቤ ካለፉት ክፍለ ጊዜያት የተሻለ መሆኑን ከሰጡት ምላሻ ማረጋገጥ ተችሏል። ከምንባቡ ጋር የተሰጣቸውን ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች የቤት ስራ ሰርተው እንዲመጡ በመስጠት የዕለቱ ትምህርት ተጠናቋል።

ቀን 17 /9/ 2009 ዓ.ም.

ስአት 8፡00

የእለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ተማሪዎች የሰሯቸው የቤት ስራዎች ታይቷል። በመቀጠል ባለፈው ክፍለ ጊዜ ያነበቡት ምንባብ በምን ላይ ያተኮረ እንደሆነ በመጠየቅ ተማሪዎች ምንባቡን እንዲያስታውሱ ተደርጓል። በሁለቱም ምንባቦች የቀረቡትን የምርጫ ጥያቄዎች ተማሪዎች እጃቸውን በማውጣት እንዲመልሱ ተደርጓል። የምንባቡን ዋና ሀሳብ ግለጽ/ጭ ለሚለው ጥያቄ እንዲመልሱ ተደርጓል። የቤተሰብ መፍረስ በልጆች ላይ ጉዳት ያስከትላል። ወላጆች ሲለያዩ ልጆች ከማን ጋር እንደሚሆኑ ለመወሰን ይቸገራሉ፤ በጸደይ ወቅት አበቦች ያብባሉ፣ በጸደይ በምድር ልምላሜ እንስሳትና ሰዎች ይደሰታሉ። የፊታውራሪ ግቢ በጸደይ ወቅት በጣም ያምራል። በጋ ለይ ይህ ሁሉ ውበቱ ይጠፋል። የሚሉ ምላሾችን ሰጥጠዋል። በትእዛዝ ሁለት ለቀረቡ ጥያቄወች በግላቸው የሰሩትን መልስ በየቡድናቸው እንዲወያዩ አዛለች። አጥኚዋም እየተዘዋወረች ተማሪዎች በንቃት ሲወያዩ አስተውላለች።በመጨረሻም እለቱ የትምህርቱ የመጨረሻ ቀን በመሆኑ በወሩ ውስጥ ስለተማሯቸው ትምህርቶች ምን እንደጨበጡ?፣ ምን ይመስል እንደ ነበር? ምን አይነት

ጥያቄዎች መስራት እንዳስቸገራቸው የሚሉ ጥያቄዎች በአጥኚዋ የቀረበላቸው ሲሆን ሥለ ጽሁፍ አወቃቀር ምንም ግንዛቤ እንዳልነበራቸውና አሁን ግንዛቤ እንዳገኙ ትምህርቱንም ያለ መሰልቸት እንደ ተማሩ መምህራን የአንብቦ መረዳት ትምህርት ሲያቀርቡ ተማሪዎች የጽሁፍ አወቃቀሩን እንዲለዩ በማድረግ ቢያስተምሩ ወይም ለተማሪዎች ግንዛቤ ቢፈጥሩ የሚሉ አስተያየቶችን ሰጥተዋል።

በአጠቃላይ ከሚያአዚያ 17/ 8/ 2009 ዓ.ም. -ግንቦት 17/ 9/ 2009 ዓ.ም. ለአምስት ሳምንታት የተከናወነው የመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ምንባቡ የተደራጀበትን የጽሁፍ አወቃቀር እንዲለዩ በአንድ ጽሁፍ ውስጥ የሚገኙ ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦችን እንዲለዩ ለቃላትና ለሀረጋት አውዳዊ ፍች እንዲሰጡ ሀሳባቸውን በተለያዩ የጽሁፍ አወቃቀሮችን በመጠቀም እንዲገልጹ የሚያስችሉ ነበሩ። በቀጣይ የተከናወነው ተግባር ድህረ ትምህርት ፈተናውን መፈተን ነው። የፈተናው ጥያቄዎች ከቅድመ ትምህርት ፈተናው ተመሳሳይ እንዲሆኑ በማድረግ ተዘጋጅተው ግንቦት 18/ 9/ 2009 ዓ.ም. ተሰጥቷል።

# አባሪዎች

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የእኔ መሆኑንና ለጥናቱ የተጠቀምኩባቸዉን ክለሳ ድርሳናትና መረጃዎች በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን በስሜና በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ሙሉገበያ ያለው

ፊርማ .........................

ቦታ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ቀን ነሀሴ 2009 ዓ.ም.